“ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እናሳካቸዋለን ብለን ካስቀመጥናቸው ግቦች አኳያ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥሩ ውጤት እያመጡ ነው“

ገጽ 9

መሬትን በተቀናጀና በተናበበ መንገድ ማስተዳደርና መምራት ያስፈለገበት ዘመን

ገጽ 18

የኢትዮጵያውያን መልክ የሚገለጥበት በአል - ጥምቀት

ገጽ 21


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 131 ጥር 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ በሚሊዮን ተስፋዬ

# “ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት በዓልን ስታከብር ለሕዝብ ሁሉ ሰላምና ፍቅር ትጸልያለች”

**- ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ**

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት በዓልን ስታከብር ለሕዝብ ሁሉ ሰላምና ፍቅር እንደምትጸልይ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ገለጹ።የጥምቀት ከተራ በዓል በአዲስ አበባ በድምቀት ተከብሯል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ዘንድ በትናንትናው ዕለት ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስን ጨምሮ ሊቃነጳጳሳት፤ በርካታ ምዕመናንና የውጪ ሀገር ጎብኚዎች በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት

ቤተክርስቲያን የጥምቀት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ኢራንቡቲ-
## የጥምቀቱ ድምቀት

ገጽ 4



# “የጀመርነው ጉዞ ጥቂት የሚመስል፤ ግን የሚበዛ፣ ሀገር የሚታደግና ስብራት የሚጠግን ጉዞ ነው”

**- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጀመርነው ጉዞ ጥቂት የሚመስል ፤ግን የሚበዛ፣ ሀገር የሚታደግና ስብራት የሚጠግን ጉዞ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለጥምቀት በዓል ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ የጀመርነው ጉዞ ጥቂት የሚመስል ፤ግን የሚበዛ፣ እዚህ የተወጠነ ግን ረዥም፣ ጥቂቶች የተረዱት፣ ነገ ግን ሕዝብ ሁሉ የሚከተለው፣ ሀገር የሚታደግና ስብራት የሚጠግን ጉዞ ነው ብለዋል።

እንደ ሀገር የምንሠራቸው ሥራዎች ሀገርን የማዳንና ለሌሎች መንገድ የማሳየት ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እዚህና እዚያ የጀመርናቸው ውጥኖች አንዱ ዓላማቸው ለሌሎች መንገድ ማሳየት ነው ብለዋል።

ስብራት እየጠገንን፣ ሀገር እየታደግን፣መንገድም እየከፈትን መጓዛችንን እንቀጥላለን ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

“የጀመርነው ጉዞ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# ‹‹ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን በማድረግ ረገድ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው››

**- በለጠ ሞላ (ዶ/ር)**
**የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር**

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን በማድረግ ረገድ የዲጅታል 2025 ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ በመደረጉ አበረታች

“ዲጂታል ኢትዮያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# የጀልባ ጉዞ የሚደረግበት የባቱ የከተራ በዓል በድምቀት ተከበረ

ሳሙኤል ወንደሰን



ባቱ፡- የጀልባ ጉዞ የሚደረግበት የባቱ የከተራ በዓል በትናንትናው እለት በድምቀት ተከብሯል።

በሥነሥርዓቱ ላይ የባቱ ከተማ የዝዋይ ሐመረ ኖህ ቅድስት ኪዳነ ምህረት ገዳም አስተዳዳሪ መልዓከ ፀሐይ ቆሞስ አባ የማነ ብርሃን ታደሰ ለኢፕድ እንደገለፁት፤ የጥምቀት በዓል ሰላምና ፍቅር የተገለጠበት በመሆኑ የተቸገሩትን በመርዳት ያዘኑትን በማረጋጋት ማክበር ይገባል።

መልዓከ ጸሃይ እንደገለጹት፤ የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ ከታላላቆቹ በዓላት አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ በዓል በየዓመቱ የሚከበር ሲሆን፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ፣ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀበትን ለማስታወስ የሚከናወን ታላቅ መንፈሳዊ በዓል ነው። የጥምቀት ከተራ በዓልን ስናከብር ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ባከበረ መልኩ ሊሆን እንደሚገባም ተናግረዋል።

በባቱ ከተማ የደብረ መድኃኒት መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ ሊቀ ስዩማን ቀሲስ ሰሎሞን አበበ በበኩላቸው፤ በባቱ የጥምቀት ከተራ በዓል አከባበር ድንቅ ተዐምር የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦቱ በጀልባ ከደሴቱ ተነስቶ በሚገርም የእግዚአብሔር ሥራ ወደ ሀይቁ ዳር ላይ በማደር በማግስቱ በእልልታና በታላቅ ዝማሬ ይመለሳሉ ብለዋል።

“ይህንን ድንቅ ተዐምር ከዝዋይ ከተማ ሀይቅ ዳር ወደ ደሴቱ በጀልባ የሚደረግ የውሃ ላይ ጉዞ ነው። ይህ በዓል በሰላም እንዲጠናቀቅ ከባቱ ከተማ አስተዳደር ጋር ተወያይተናል። በዚህም ከተማ አስተዳደሩ የሚጠበቅበትን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ገልጿል” ብለዋል።

በዓሉን ስናከብር የተቸገሩትን በመርዳት ያዘኑትን በማረጋጋት ማክበር ይገባል ያሉት ቆሞስ አባ የማነ ብርሃን ታደሰ እና ሊቀ ስዩማን ቀሲስ ሰሎሞን አበበ፤ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላምና በጤና አደረሳችሁ አደረሰን ብለዋል።

የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ አህመዲን እስማኤል በበኩላቸው፤ የባቱ ከተማ የጥምቀት በዓል አከባበር በሀይቅ ላይ መከበሩ እና ጥንታዊነቱ ጥምቀትን በባቱ ልዩ ያደርገዋል ብለዋል።

የደንበል ሀይቅ ላይ የሚገኙ ገዳማት እጅግ ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው እንዲሁም አካባቢው የስምጥ ሸለቆ መግቢያ ከመሆኑ እና በርካታ የመስህብ ባለቤት በመሆኑ ወደፊት ትልቅ የጥምቀት በዓል መዳረሻ ይሆናል ተብሎ ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል ነው ያሉት ከንቲባ አቶ አህመዲን።

እንደ ከንቲባ አቶ አህመዲን ገለፃ፤ የባቱ ከተማ እንግዳ ተቀባይነትን እና የከተማዋን የቱሪስት ቁጥር ለመጨመር እንዲሁም በአንድ ቀን በርካታ የህዝብ ቁጥር ማስተናገድ የሚችል የጥምቀት ማክበሪያ ስፍራን ለመገንባት ለህዝብ ቃል ገብተው ነበር።

ምክንያቱም የጥምቀት ማክበሪያን ስፍራ በአቧራ የተሞላ፣ የማይማርክና ከተማዋን የማይመጥን ነበር። ይህንንም ለማስተካከል ለህዝብ የገባነው ቃል በተግባር አሳክተናል ብለዋል።

አሁን ላይ ቦታው ከውጭ የሚመጡ ቱሪስቶችን እና በአንድ ቀን በርካታ የህዝብ ቁጥር ማስተናገድ በሚችል መልኩ ለምቷል ብለዋል።

የደምበል ሃይቅ ዳርቻ ፕሮጀክት የአደባባይ በዓላትን ለማክበር እና ማንኛውንም ሃይማኖታዊና መንግሥታዊ ትዕይንቶች ማስተናገድ የሚያስችል መሆኑን ጠቁመው፤ በብስክሌት አንድ ነጥብ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ማስጓዝ የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ የተሠራ ሲሆን፤ አብዛኛው የባቱ ከተማ ነዋሪም በብስክሌት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ፕሮጀክቱ ለከተማው ወሳኝ ነው ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ነዋሪዎች በሀይቁ ዳርቻ የእግር እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችሉበት እና ህፃናት የሚጫወቱበት ቦታም መሠራቱን ገልፀዋል።



# በማይጨው የሚከበረው በዓል የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ለማነቃቃት ይረዳል

ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በክልል ደረጃ በማይጨው ከተማ የሚከበረው የጥምቀት በዓል የትግራይን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ማነቃቃት እንደሚያስችል የትግራይ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አፅብሃ ገብረእግዚአብሔር (ዶ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልል ደረጃ የጥምቀት በዓል በማይጨው ከተማ በድምቀት እየተከበረ ይገኛል።

በዓሉ በክልሉ በነበረው ጦርነት ምክንያት ተቀዛቅዞ የነበረውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ዳግም ማነቃቃት እንደሚያስችል አመላክተው፤ የቱሪዝም እንቅስቃሴውን ለማነቃቃት የሚያስችሉ በርካታ ሁነቶች መዘጋጀታቸውን ጠቁመዋል።

ከሃይማኖታዊ ክዋኔዎች ጎን ለጎን የክልሉን የቱሪዝም መዳረሻዎች ሊያሳድጉ እንዲሁም ሊያስተዋውቁ የሚችሉ ተጨማሪ መርሃ- ግብሮች እየተከናወኑ መሆኑን አስረድተዋል።

ጎብኚዎች ወደ መስህብ ቦታዎች የሚሄዱባቸው የእግር ጎዞ መርሃ-ግብሮች፣ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች፣ ባህላዊ ጨዋታዎች፣ ሀገርኛ የእንግዳ አቀባበል ስነስርዓቶች እንዲሁም የተለያዩ የዕደ-ጥበብና ባህላዊ የፈጠራ ሥራዎች የሚቀርቡበት ኤግዚቢሽን እየተካሄደ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በዓሉ በክልሉ ያለውን የቱሪዝም ድባብ መቀየር በሚያስችል መልኩ ለማክበር ሲሰራ መቆየቱን ዶክተር አፅብሃ አስታውሰው፤ በዓሉ ለሰላምና ለመልሶ መቋቋም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ እሴቱን በሚያጎላና ማህበራዊ መስተጋብር በሚያጠናክር መልኩ እየተከበረ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

የጥምቀት በዓል ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ከሃይማኖት አባቶችና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር መሰራቱን ጠቁመው፤ የተጀመረውን የሰላም ጉዞ በሚያጠናክር መንገድ ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር እንደሚከበር አመላክተዋል።

በዓሉ የዜጎችን ማህበራዊና ባህላዊ መስተጋብሮች በማጠናከር ለሰላም ግንባታ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን አንስተው፤ ከሃይማኖታዊ ስርዓቶቹ ባለፈ የሚከናወኑ ዝግጅቶች ቱሪዝሙን ለማነቃቃት ዕድል ይፈጠራል ሲሉ አስረድተዋል።

የጥምቀት በዓል በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የሚፈቱበት ነው ያሉት ኃላፊው፤ ቱሪዝሙን በማነቃቃትና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም ሰፊ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል።

ለበዓሉ የሚሆን ሀብት የሚያሰባስብና በበዓሉ የተቸገሩትን ለመርዳት የተቋቋመ ኮሚቴ ተዋቅሮ ሲሰራ መቆየቱንም ዶክተር አፅብሃ ጠቁመዋል።

በዓሉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ የጸጥታና የመሰረተ ልማት ችግር እንዳያጋጥም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በጥምረት እየተሰራ እንደሆነ ኃላፊው ተናግረዋል።



# የከተራ በዓል በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በድምቀት ተከበረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ባህር ዳር፡- የከተራ በዓል በአማራ ክልል ባህር ዳር፣ ምዕራብ ጎንደር ዞን ገንዳ ውሃና ጎንደር ከተሞች ብዛት ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል።

በባህር ዳር ከተማ በተከበረው የከተራ በዓልም የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የባህር ዳር ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ አብርሃም፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሩ አመራር አባላት ታድመዋል።

ታቦታቱ በከተማዋ የሚገኙ ተቦታት ከየአድባሮቻቸው በመውጣት ወደ ባህረ ጥምቀት ማክበሪያ ቦታ አምርተዋል።

ከየአድባራቱ የመጡ ካህናትና አገልጋዮች ታቦታቱን በመዝሙርና በምስጋና በማጀብ ወደ ባህረ ጥምቀቱ አቅንተዋል።

በተመሳሳይ በምዕራብ ጎንደር ዞን ገንዳ ውሃ ከተማ የተለያዩ አድባራት የከተራ በዓል በድምቀት ተከብሯል።

የምዕራብ ጎንደር ዞን ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ መጋቢ ሚስጥር አፍሬም ማስረሻ፤ የከተራ በዓል በደመቀ ሁኔታ መከበሩን ገልጸዋል።

በሀገረ ስብከቱ ስር ያሉ አድባራት በሙሉ የከተራ በዓሉን ማክበራቸውንም አስታውቀዋል።

የገንዳ ውሃ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰጠኝ ፈቀደ በበኩላቸው፤ በዓሉ በሰላም እንዲጠናቀቅ ወጣቶች የማስተባበር ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን አመልክተዋል።

በጎንደር ከተማም እንዲሁ ከተለያዩ አድባራት የተነሱ ታቦታት በእምነቱ አባቶችና ምዕመናን ዝማሬና እልልታ ታጅበው ወደ ማደሪያቸው ባህረ ጥምቀት አምርተዋል።



ወይዘሮ ትእግስት፤



አቶ ሀይሉ አስፋው፤



ወይዘሮ እቴቱ ታደሰ፤



ወጣት ነብዩ ሳሙኤል፤

# የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ በአንድ ማዕከል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

**ዜና ሐተታ**

ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም ጋር በመንግሥት ደረጃ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ማድረግ ከጀመረች ብዙ ሺ ዓመታትን አሳልፋለች። ይህም የሀገሪቱን የዲፕሎማሲ ግንኙነት በአፍሪካ ካሉ ሀገራት ቀዳሚው ያደርገዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ1900 ዓ.ም በአጤ ምኒልክ ከተቋቋሙት ጥቂት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አንዱ ሲሆን፤ ዘንድሮም 116ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን አክብሯል፡፡ ይህም ሆኖ ይህ በኩራት ሊዘገብ የሚችልና በአመርቂ ውጤት ዘመናትን የተሻገረው ታሪኩ በአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዘንድ አይታወቅም።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመሆን በየዘመኑ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ያደረጉትን የዲፕሎማቲክ ተጋድሎ የሚዘክር አውደ ርዕይ አዘጋጅቶ እያስጎበኘ ይገኛል። አውደ ርዕዩን ሲጎበኙ ያነጋገርናቸው ታዳሚዎችም ይህንን አኩሪ ታሪክ ለማየት በመብቃታቸው የተሰማቸውን እርካታ በመግለፅ ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ ሊሰራ እንደሚገባ አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

በቅድሚያ ያነጋገርናቸው ከልጆቻቸው ጋር በባለሙያዎች ማብራሪያ ሲደረግላቸው ያገኘናቸውን ወይዘሮ ትእግስት በዙ ነው። ስለ አውደ ርዕዩ ስሰማ በዚህ ደረጃ ይሆናል ብዬ አልጠበኩም ነበር የሚሉት ወይዘሮ ትእግስት የተሰማቸውን እንዲህ አካፍለውናል።

«በእኔ ዘመን በታሪክ መጽሐፍና በሌሎች ትምህርቶችም ስለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ የማውቃቸው ነገሮች ነበሩ። እናም ስመጣ ዋና አላማዬ ልጆቼን ለማሳየት ነበር። በአውደ ርዕዩ የቀረቡት ነገሮች ግን ለልጆች ብቻ ሳይሆን ለእኛም በርካታ የማናውቃቸው መረጃዎች የተካተቱባቸው ናቸው። ለምሳሌ እኔ የአፍሪካ አንድነት የመመስረቻ ጽሁፍ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መሆኑን አላውቅም ነበር። ይህ ኢትዮጵያ በዘመኑ የነበራትን ኃያልነትና ተሰሚነት የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ ከሺ ዓመታት በላይ የነበረንን ጉዞ የምናይበትና የምናውቅበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ”።

አሁን ያለው ትውልድ ግን ሀገሩ ስለተጓዘችበት የዲፕሎማሲ መንገድ ብዙ ነገሮችን አያውቅም ያሉት ወይዘሮ ትዕግስት፤ እንዲህ አይነት አውደ ርዕይ ለዚህ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። ትውልዱ ሀገሩን እንዲወድ እኔስ ለሀገሬ ምን ላበረክት እችላለሁ የሚል ቁጭት እንዲፈጠርበትና የመስራት አቅም ያለው መሆኑንም የሚያሳይ ይሆናል። ለቀጣይም ከዚህ አውደ ርእይ በመማር እነዚህ ታሪኮች በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ቢካተቱ አልያም በቋሚነት የሚጎበኙበት ሁኔታ ቢመቻች እንደ ሀገር ብዙ የምናተርፍበት ይሆናል ብለዋል።

በተመሳሳይ አቶ ሀይሉ አስፋው ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ብቻ የተሰሩት ስራዎችም ራሱን የቻለ ሰፊ ታሪክ ያለው ነው ይላሉ። በየወቅቱ በተናጥል የምንሰማቸው ነገሮች ስለሀገራችን አንድ ትልቅ እይታ እንዲፈጠርልን አያስችሉንም። በእኔ በኩል ከዚህ ሁሉ የዓለም ክፍል ጋር በዚህ ደረጃ የጠነከረ ግንኙነት እንዳለን አላውቅም ነበር። በዚህ አውደ ርዕይ ግን በየዘመኑ የተሰሩ ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ እንድገነዘብ የሚያስችለኝን መረጃ አግኝቼአለሁ ሲሉ ገልጸዋል።

አቶ ሀይሉ እንዳሉት፤ እንደዚህ አይነት መድረኮች ስለ ሀገር ለማወቅ ትልቅ ፋይዳ አላቸው። ነገር ግን በአንድ ሰሞን እይታ ብቻ ትውልዱን ማስተማርም ሆነ አብዛኛውን ሰው ማዳረስ ስለማይቻል በቋሚነት የሚጎበኝበት አልያም አውደ ርዕዩ የሚደጋገምበት ሁኔታ ቢመቻች የበለጠ ጥሩ ይሆናል።

በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ከህዳሴው ግድብም ጋር ይሁን ከወደብ ጋር በተያያዘ ከመቼውም በበለጠ ጠንካራ ዲፕሎማሲ የሚያስፈልግበት ወቅት ነው ያሉት አቶ ሀይሉ፤ ይህንንም ከግብ ለማድረስ መንግሥት ከመደባቸው ዲፕሎማቶች ባልተናነሰ መላው ኢትዮጵያዊ ለሀገሩ ጥቅም ሲል ሊሰራ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሌላዋ አስተያየት ሰጪያችን ወይዘሮ እቴቱ ታደሰ ይባላሉ። የባቱ ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ ከ35 ዓመት በላይ በመምህርነት አገልግለዋል። በተለያዩ ጊዜያት በተጠናጥል ይሰሙት የነበረውን የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት ታሪክ በተቀናጀና በምስል በተደገፈ መልኩ ማየታቸው ሀገራቸውን የበለጠ እንዲረዱና እንዲወዱ እንዳደረጋቸው ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ ታሪክ የሠሩ ብቻ ሳይሆን ታሪክ እየሠሩ ያሉ ልጆችም አሏት ያሉት ወይዘሮ እቴቱ፤ በተለይም በሰላም ማስከበር ረገድ ለዘመናት የቆየው የሀገሪቱ ተሳትፎ መላውን ኢትዮጵያዊ የሚያኮራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ ላይ የደረሰውን የኢትዮጵያ ተሰሚነት ሁላችንንም የሚያኮራ ነው። የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ በርካታ ሀገራዊ ስራዎች ውጤታማ እየሆኑ ያሉት አሁንም ጠንካራ የውጪ ግንኙነት እንዳለን አመላካች ነው። ይህን እድል ጡረታ ሳልወጣ በመምህርነት እያገለገልኩ ባገኘው ኖሮ ለብዙዎች የማካፍለው ይሆን ነበር ብለዋል።

«ስለሀገሬ ብዙ ማወቅ እንደሚጠበቅብኝ ከአውደ ርዕዩ ተገንዝቤያለሁ» ያለን ደግሞ ወጣት ነብዩ ሳሙኤል ነው፡፡

አብዛኛው ነገር ለእኔ አዲስ ሆኖብኛል፤ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በዓለም መድረክም የነበራትን ተሰሚነት የሚያሳይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፤ ያለው ወጣት ነብዩ፤ ይህ ደግሞ የሁላችንም ታሪክ በመሆኑ አንድነታችንን የሚያጠነክር አብሮነታችንን የሚያጎለብት ነው። መድረኩ ሌሎች አፍሪካውያን ወንድሞቻችንም የነበራቸውን ታሪክ እንድንገነዘብ ይጠቅማል ብሏል።

ባጠቃላይም ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም እንድናውቅ በር የሚከፍትልንም ነው። ብዙ የሚያኮሩ ታላላቅ ስራዎች ያከናወኑ አባቶች እንደነበሩንም በመረጃ በተደገፈ ሁኔታ ለማየት በመቻሌ ትልቅ ደስታ ተሰምቶኛል ሲልም ተናግሯል።

# በ44 ታቦታት ተሞሻሪዋ አቃቂ

**ተስፋ ፈሩ**

**ዜና ሐተታ**

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ካሉት ከ70 በላይ የጥምቀት ማክበሪያ ስፍራዎች አንዱ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኘው አቃቂ ጥምቀተ ባህር ነው። ጥምቀተ ባህሩ ጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ፊት ለፊት አቃቂ ወንዝን ተንተርሶ በሀገር በቀል ዕጽዋት ተውቦ ይታያል፡፡

አቃቂ ጥምቀተ ባህር የሚያድሩ ታቦታት ከተራራቀ ስፍራ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን አቆራርጠው ስለሚመጡ እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በበዓሉ ይታደማል። ከቱሉ ዲምቱ እስከ ሳሪስ ወርቁ ሰፈር፤ ከሳሎ ጎራ እስከ ቂሊንጦና ፈጬ የሚገኙ አያሌ ነዋሪዎች የየአጥቢያቸውን ታቦት አጅበው ይሸኛሉ።

ዘንድሮ ከሃያ አድባራትና ገዳማት 44 ታቦታት በጥምቀት ባህሩ አርፈው ከተራን ጨምሮ ለተከታታይ አራት ቀናት በደማቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት በዓሉ ይከበራል።

አድባራትና ገዳማቱ በየዓመቱ ተራ በተራ ሙሉ ዝግጅቱን የመምራት ኃላፊነት ይወስዳሉ። የ2016 ዓ.ም. ባለተራ አሳዳሪ አቃቂ ስታዲየም አጠገብ የምትገኘው የጃቴ መካነ ህይወት ኪዳነምህረት ካቴድራል ቤተክርስቲያን ናት።

የጃቴ መካነ ህይወት ኪዳነምህረት ካቴድራል ቤተክርስቲያን ዋና አስተዳዳሪ መላከ ምህረት አበበ የሺህ ንጉስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአቃቂ ጥምቀተ ባህር ከሃያ አድባራትና ገዳማት የሚመጡ 44 ታቦታት በአንድነት ያድራሉ።



ከአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የተለያዩ ወረዳዎች በርካታ ሕዝብ ታቦታቱን አጅቦ እንደሚመጣ የሚናገሩት ዋና አስተዳዳሪው፤ አቃቂ ጥምቀተ ባህር የሕዝብ ማዕበል እንደሚያስተናግድ ይገልፃሉ።

"ጃንሜዳ የጥንት መሰረት ስለሆነ እንጂ በአቃቂ ጥምቀተ ባህር የሚያርፉት የታቦታት ብዛት ከጃንሜዳ በላይ ነው" ሲሉ በጥምቀተ ባህሩ የሚኖረውን የበዓሉን አከባበር ግዝፈት ያመላከቱት አባ መላከ ምህረት፤ በዓለ ጥምቀቱ ያማረና የደመቀ እንዲሆን ወጣቱ፣ ሰበካ ጉባዔው፣ ክፍለ ከተማውና ሌሎችም የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ከጎናችን ሆነው አይዟችሁ እያሉንና እየረዱን ከፍተኛ ዝግጅት አድርገናል ይላሉ፡፡

የአቃቂ መንበረ ህይወት መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ፍኖተ ብርሃን ሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋይና መምህር ወንድወሰን ተክሌ አቃቂ ወንዝ አጠገብ የሚገኝ ትልቅ ስፍራ ባለርስት የነበሩ ደገኛ አባት አሁን ጥምቀት የሚከበርበትን ቦታ ከርስታቸው ከፍለው ለታቦት ማደሪያነት እንዲውል በፈቃደኝነት ለወረዳው ቤተክህነት ደብዳቤ በመፃፍ ከ60 ዓመታት በፊት በስጦታ ማበርከታቸውንና አራት አድባራት በቦታው በዓለ ጥምቀትን ማክበር መጀመራቸውን ይናገራሉ።

በጥምቀተ ባህሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለ ጥምቀትን ያከበሩት ጥንታውያኑ አቢያተ ክርስቲያናት ሳሎ ደብረ ጸሐይ ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቱሉ ዲምቱ ደብረ ሰላም ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ አቃቂ መንበረ ህይወት መድኃኒዓለም እና ጃቴ መካነ ህይወት ኪዳነ ምህረት ካቴድራል ነበሩ የሚሉት መምህሩ፤ በየጊዜው እየሰፋ መጥቶ ዛሬ 20 አድባራትና ገዳማት መድረሳቸውን ይገልፃሉ።

አክለውም በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ ቤተክህነት ስር የሚገኙ 18 አድባራትና ገዳማት እንዲሁም በሸገር ከተማ ሀገረ ስብከት አቃቂ ወረዳ ቤተክህነት ስር ያሉ ሁለት አድባራት ተጨምረው በ2016 ዓ.ም. በድምሩ 20 አድባራትና ገዳማት በአንድነት እንደሚያከብሩ ጠቅሰው፤ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ 44 ታቦታት በአንድነት የሚያከብሩበት ሦስተኛው ቦታ አቃቂ ጥምቀተ ባህር ነው" ይላሉ።

መምህር ወንድወሰን እንደሚናገሩት፤ ቀደም ባለው ጊዜ ታቦታት ወደየመጡበት አጥቢያ ከተመለሱ በኋላ የቃና ዘገሊላ ዕለት ከአቃቂ ገበያ ወረድ ብሎ የቀድሞ ባቡር ጣቢያን ተሻግሮ በሚገኘው ሜዳ ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ታዳሚ የሚከታተለው የፈረስ ጉግስ ጨዋታ ይደረግ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህ ልማድ እየቀረ መጥቷል።



# ኢሬንቡቲ- የጥምቀቱ ድምቀት

**ዳግማዊት ግርማ**

**ዜና- ሀተታ**

ሕዝቡ ለክሩ አዳሪ ጌታውን አክባሪ ነው። የጀግንነቱን ያህል እግሩን ለአምላኩ ማንበርከክንም ያውቅበታል። በውብ ዘፈንና ጭፈራው ይታወቃል። ነገሩ ጠመዝማዛ አይደለም ፊትለፊት ይናገራል። መሬቱም እንደ ሕዝቡ ለጋስ ነው። ሀጫ ነጭ ጤፍ እስከ ቡና፣ ከስንዴ እስከ አትክልትና ፍራፍሬ፤ ሁሉንም በየአይነቱ ያለስስት ይሰጣል።

ታዲያ በዓላትን ማክበር የመላ ኢትዮጵያውያን መገለጫ ቢሆንም አንዳንድ ስፍራዎች ግን ደመቅ አድርገው ማክበርን ተክነውበታል። ከነዚህ አንዱ ታዲያ ምንጃር ሸንኮራ ነው።

ምንጃር ልቡ እንደ ምድር ቻይ ነው። እጁም ለሰጪነት አይታጠፍም። በምንጃሮቹ ቀዬ እንደዚያ ነው። ግጥሞቻቸው እንኳን ሥራን ይመለከታል። እዚያ ለነፍስ መክፈልት ለስጋ እንጀራ ይበላል። የውብ ወይዛዝርት መገኛም ነው።

ምንጃሬ ወገብና ክሩን አጥባቂ ነው። ባህሉና እምነቱን ጠባቂነትም የሱው። ስፍራው ከመዲናዋ አዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል። በሰሜን ሸዋ ዞን። ወረዳው ምንጃር ሸንኮራ ነው። ኢራንቡቲ ይባላል። በነሱ መንደር ክርስትና ሌላ መልክ አለው። ጥምቀት ድባቡ ይለያል። አምሳለ ኢየሩሳሌም ይሉታል። ከጥር 10 የጀመረው የበዓሉ ክብር እስከ 12 ይዘልቃል። ከ44 የሚልቁ ታቦታት በአንድ ስፍራ በሞገስ ይታያሉ።

ምዕመናን እልልታና ሆታ ይከባቸዋል። ካህናቱ ለምስጋና አፋቸው ይከፈታል። በሰማያዊው ሥርዓት ምድር ላይ ይዋባሉ። ሕዝቡም ታቦታቱን ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ይሸኛሉ። የቀዬው ነዋሪ ልቡ የሻተውን ታቦት የማጀብ መብቱ በእጁ ነው። ቢያሻው ሸንኮራ ዮሐንስን መሸኘት ይችላል። ባልጪ አማኑኤልም እዛው አለ።

የጉዞና ጉብኝት ጋዜጠኛው ሄኖክ ስዩም ይናገራል። በዓሉን በእልፍ ስፍራዎች የማክበር እድል ገጥሞታል፤ ጥምቀት፣ በርካታ ስፍራዎች ላይ ደማቅ አከባበር አለው። ሁሉም የየራሱ ቀለምና ውበት አለው ይላል። የኢራንቡቲው ጥምቀት ግን ይለያል ባይ ነው። በስፍራው ስለታዘባቸው እልፍ መልካም ነገሮች አትቷል። የኢራንቡቲው ጥምቀት ባህላዊም ሃይማኖታዊም አከባበር አለው። ሕዝቡ ለእምነቱ ወረብ ሲወርብ ለባህሉ ጭፈራውን ያቀልጣል።

የሸንኮራ ወንዝ ዳርቻ ላይ ነው ጥምቀቱ የሚከወነው። ሕዝቡ በዓሉ አከባበር ላይ የሚያመጣውን እህል ያዘጋጃል። በታቦታቱ ማለፊያ ጎዳናዎች ላይ ምርቱን ይዞ ያስባርካል። ለቀጣይ ዓመትም በቸር እንዲያደርሰው አምላኩን ይለማመናል። በየቤቱ ድግስ አለ። ያለውን ይዞ ሕዝብ ወደተሰበሰበበት ያመጣል። ለነዳያን ይለግሳል።

ወረዳው ምንጃር ኢራንቡቲ ቀበሌው ነው። ታቦታቱ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ወደ ማደሪያቸው ይተማሉ። ሕዝቡም ውብ የባህል ጭፈራውን ይጨፍራል። ኮበሌው አይኑ ያረፈባትን ኮረዳ ሊያማልል መከራውን ይፈጃል። በየጥምቀቱ ትዳር ይመሰረታል። እዛ የአባቶች ምርቃት ስፍራ አለው። እናቶች እልልታቸው ይደመጣል። ልጆች ከወላጆች እቅፍ ሳይወጡ መልካም መልካሙን ሲቀስሙ ያድጋሉ። አረጋውያን በጧሪዎቻቸው ታጅበው ይዋባሉ።

የጉዞ ጋዜጠኛው ሄኖክ ስለ ስፍራው በኩራት ይተርካል። ለሕዝበ ክርስቲያኑ ምክር አለው። በተለይ አዲስ አበባ ያለ ሰው የስፍራውን ቅርበት መጠቀም አለበት። ሸንኮራ ሄዶ ጥምቀትን ሊያከብር ይገባዋል ባይ ነው። ከተራን በአዲስ አበባ ያከበረ ለጥምቀት ሸንኮራ መገኘት ስለመቻሉ ጠቅሷል። ድንቅ ነገር የበዛው መሆኑን ይመሰክራል። ልዩ ልዩ ትዕይንቶች ከሚታይባቸው የሀገሬ የጥምቀት በዓል ቦታዎች አንዱ ነው ብሏል።

የሕዝቡ ሆታ የአርባ አራት ደብር አገልጋዮች ዝማሬ ልዩ መሆኑን ይጠቅሳል። የእልልታው ድምቀት አይረሳም። ኢራንቡቲን ይሄዱታል እንጂ አይሰሙትም ባይ ነው።

ወይዘሮ በየነች የድርሻወርቅ ይባላሉ። የምንጃር ሸንኮራ ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት የቅርስ ጥበቃና ቱሪዝም ልማት ቡድን መሪ ናቸው። ለእሳቸው ስፍራው ጥምቀት በድምቀት ከሚከበርባቸው መሀል ነው። የ622 ዕድሜ ባለፀጋው የኢራንቡቲ ጥምቀት። በርካታ ሕዝብ የሚያከብረውና የታቦታቱም ቁጥር 56 የሚደርሱበት ጊዜ ስለመኖሩም ተነግሮናል።

እንደ ቡድን መሪዋ ገለጻ፤ አስተሳሰብ ስፍራው የድምቀቱን ያህል አልታወቀም። ከዚህ በፊት ያልተሰሩ ስራዎች ዋጋ ስለማስከፈላቸው ይጠቅሳሉ። ለዘመናት ለስፍራው በተነፈገው ትኩረት ይቆጫሉ። የታሪኩን ያህል ሰዎች ጋር ባለመድረሱ ይተክዛሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስራዎች እየተሰሩ በመሆኑ ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች አሉ። ቀጣይም መፍካት የሚችል በዓል ነው። ምዕመናንም በየዓመቱ መጥታችሁ እኛ ጋር አክብሩ ብለዋል።

# ‹‹ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን በማድረግ ረገድ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ገለጹ።

ዶክተር በለጠ ሞላ፤ በዘርፉ እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎችን አስመልክተው ከመገናኛ ብዙኃን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለጹት፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ለግሉ ዘርፍ ክፍት የማድረግና መሰረተ ልማትን ማስፋፋት ላይ በትኩረት እየተሰራ ነው።

የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ዕውን መሆን እንደ ሀገር ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች የኢኖቬሽን ፣የቴክኖሎጂና የአይሲቲ ዲጅታላይዜሽን (አይ ሲ ቲ ) ዘርፍ አንዱ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥት የቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪውን ለግሉ ዘርፍ ክፍት በማድረጉ በቴሌኮሙኒኬሽን ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ ኦፕሬተር መፍጠር ተችሏል፤ ይህም ለዘርፉ ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው በተጨባጭ የሚያሳይ ነው ብለዋል።

በመሰረተ ልማት ግንባታው ረገድም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ በዚህም የብሮድባንድ ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር ከ35 ሚሊዮን በላይ እንዲሁም የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥርም ከ73 ሚሊዮን በላይ መድረሱን አመላክተዋል።

የክፍያ ሥርዓቱን ወደ ዲጂታል አሰራር የመቀየሩ ሂደት እየተፋጠነ በመሆኑ ብዙ ለውጦች እየታዩበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አሁን ዲጅታል አሠራር ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ በመሆኑ በትሪሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በዲጅታል የክፍያ ሥርዓት ውስጥ እየተዘዋወረ ነው ብለዋል።

የመንግሥት አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ለማድረግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ እስካሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ 528 አገልግሎቶች ዲጂታል መደረጋቸውን ጠቅሰዋል፤ በቀጣይም አገልግሎቶች የማዘመን ሂደቱ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ዕውን እንዲሆን መሰረት የሚጥሉ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው ያሉት ሚኒስትሩ፤ መሰረተ ልማትን ማስፋፋት፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ለግሉ ዘርፍ ክፍት የማድረግ እና የክፍያ ሥርዓቱን ወደ ዲጂታል አሰራር ማስገባት ተጠቃሽ መሆናቸውን አንስተዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ ፤ የዲጅታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ተቀርጾ ተግባራዊ ከሆነ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አስቆጥሯል። ስትራቴጂያዊ ግምገማ ተካሂዶ የታዩ ክፍተቶች እና የተገኙ ውጤቶች ተለይተዋል። የኢንተርኔት ብሮድባንድ ተጠቃሚ ቁጥር መብዛቱ ፣ የሞባይል ቁጥር እያደረ መምጣቱ፣ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ለግሉ ዘርፍ ክፍት መድረጉ እና የክፍያ ሥርዓቱ እያደገ መምጣቱ በዲጅታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ የተያዙ ግቦች እንዲሳኩ መልካም እድሎች ናቸው።

በቀሪ ጊዜያት በስትራቴጂ የታዩ ክፍተቶችን በማሟላት አዳዲስ ሃሳቦች ካሉ ከስትራቴጂው ጋር በማቀናጀት የተሻለ ሥራዎች ይሰራሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከአምስት ዓመቱ በፊት እንደሀገር የነበርንበት የዲጅታል ሥነምህዳር እጅግ የተሻለ ውጤት የሚታይበት ይሆናል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

ዲጅታል ኢትዮጵያ እውን በማድረግ ረገድ ተግዳሮቶች መኖራቸውን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ መሰረተ ልማት ግንባታ የሚጠይቅ ካፒታል ለሀገር ቀላል አለመሆኑ፣ የፋይናንስ አቅርቦት እና በፈጻሚው፣ በተጠቃሚው እና በአልሚውም የእውቀት ክፍተትና በዲጅታል ዘርፍ በቂ የተማረ ሀይል አለመኖር እንደሆኑ ገልጸዋል። በቀጣይም ያሉትን ክፍተቶች በመሙላት የስትራቴጂው አምስት ዓመት ሲጠናቀቅ ወደፊት የተራመደ ውጤት ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ አስረድተዋል።

## “ቤተ ክርስቲያን ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ዘኢትዮጵያ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማት በጃንሜዳ በተከበረው የጥምቀት ከተራ በዓል ላይ ተገኝተው እንደገለጹት፤ቤተ ክርስቲያን በዓሉን ስታከብር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና ፍቅር ትጸልያለች።

የጥምቀት ከተራ በዓል በአማረና በደመቀ መልኩ ተከብሯል ያሉት ፓትርያሪኩ፤ በዓሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ፍቅርና አንድነትን እንዲሰጥና ሰላም እንዲሰፍን እንጸልያለን ብለዋል።

በበዓሉ በሊቃውንቱና በመዘምራኑ የቀረበው መዝሙሩና ማህሌታዊው ዜማ ያማረና የተዋበ መሆኑን ጠቅሰው፤ ቤተ ክርስቲያን በዓሉን ስታከብር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና ፍቅር እንደምትጸልይ ነው የገለጹት።

የዘንድሮውን የጥምቀት በዓል የገነተ ኢየሱስና ማርያም ቤተክርስቲያን ተረኛ አዘጋጅ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ በጃንሜዳ በተካሄደው የጥምቀት ከተራ በዓል ከተለያዩ አድባራትና ገዳማት የመጡ ታቦታት በካህናት፣ በዲያቆናት፣ በዘማርያንና ምዕመናን ታጅበው ጃንሜዳ ጥምቀተ ባህር አርፈዋል።

በከተራ በዓል በተለያዩ የባህል አልባሳት ያሸበረቁ ምዕመናን፣ ጥንግ ድርብ የለበሱ ካህናት፣ ዲያቆናትና መዘምራን ታቦታቱን አጅበው ወደ ጥምቀተ ባህር አድርሰዋል። በዛሬው ዕለትም የጥምቀት በዓል በድምቀት የሚከበር ይሆናል።

የጥምቀት በዓል ትዕይንት በዓለም በማይዳሰሱ ቅርሶች ተርታ መመዝገቡ የሚታወስ ነው።

## “የጀመርነው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

“ኢትዮጵያ በብዙ ስብራቶች ውስጥ ያለፈች ሀገር ናት። ክርስቶስ ለአዳም እንዳዘነለት የሚያዝንላት ትፈልጋለች፣ ክርስቶስ ስለአዳም ሆኖ ሸክሙን እንደተሸከመለት ሸክሟን የሚሸከምላት ትፈልጋለች” ብለዋል።

ሀገር ለማዳን ስንሠራ በሀገር ላይ ተጨማሪ ቁስል ለማምጣት የሚሠሩ አሉ፤ ተሸንፈው መቅረታቸው ግን አይቀርም፣ ምክንያቱም ማጥፋት ማዳንን አያሸንፈውምና ብለዋል።

ሀገርን ለማዳን የሚሠሩ ሥራዎች ለሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ አይገለጡለትም፣ ሰዎች ሁሉ እስኪሰበሰቡ፤ እስኪረዱና እስኪተባበሩ ከጠበቅን ሀገር የማዳን ሥራችንን መሥራት አንችልም ሲሉ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳመለከቱት፤ ዛሬ የጥምቀት በዓል በሀገራችን ከ20ሺ በላይ በሆኑ ቦታዎች፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ወጥቶ ያከብረዋል። ዩኔስኮም በዓለም ቅርስነት መዝግቦታል። ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ክርስቶስ ሲጠመቅ ግን በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ብዙም የተወራለት፣ ብዙም የተነገረለት አልነበረም። የሀገርም ጉዳይ እንዲሁ ነው ብለዋል።

“ሀገርን ለማዳን የምንሠራቸው ሥራዎች ብርሃናቸው ቦግ ብሎ ዛሬ ላይበራ ይችላል ፤ ካለፈው የችግር ጊዜ እየወጣን መሆኑ፣ ወደ አዲስ ሀገራዊ ሁኔታ እየተሻገርን መሆኑ ለጊዜው ላይታወቅ ይችላል” ሲሉ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ትንሣኤና ሕዳሴ ለሁሉም ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል፤ ሀገርን የማዳን ሥራ የሀገርን የስብራት ጎዳና መከተልን ይፈልጋል ብለዋል በመልዕክታቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው፤ በእያንዳንዱ ምእራፍ ሀገር የወደቀችበትን እየፈለጉ ማንሣትን ይጠይቃል። ፍለጋውም፣ ጉዞውም ፈታኝ መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገር የማዳንም ተግባር እንደዚሁ ነው፤ ነገሩ በዛሬው ሚዛን አይመዘንም። በዛሬ ድጋፍና ተቃውሞ አይለካምና ሲሉ አመላክተዋል።

የጥምቀትን በዓል ስናከብር ከሃይማኖታዊና ባህላዊ ጉዳዮች በተጨማሪ እነዚህን ለሰው ልጆች ጉዞ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች እንድናስብ አደራ እላለሁ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክታቸውን አስፍረዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን አንግዳ

## «ጥምቀት ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስር የፍቅር ገመድ ነው»

*- መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ ፈንታሁን*

ስምስም መንግስቱ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ስፍራ ሰጥታ ከምታከብራቸው ሃይማኖታዊ በዓላት መካከል አንዱ የጥምቀት በዓል ነው። በዓሉ መከበር የሚጀምረው ጥር 10 ነው። ጥር 10 ከተራ ሲሆን፣ ጥር 11 ደግሞ ዋናው የጥምቀት በዓል ነው። በከተራ ወደ 40 ሺህ የሚሆኑ ታቦታት ከመንበረ ክብራቸው ወጥተው በጥምቀተ ባሕር ያድራሉ። ጥር 11 ቀን ደግሞ ከጥምቀተ ባሕር ወደ መንበረ ክብራቸው ይመለሳሉ።

ታቦታቱ ከማደሪያቸው ሲወጡም ሆነ ወደ ማደሪያቸው ሲመለሱ በሕዝበ ክርስቲያኑ ይታጀባሉ። በዚህ የጥምቀት በዓል ላይ በዋናነት የሚታደሙት የእምነቱ ተከታዮች ቢሆኑም ከእምነቱ ውጭ የሆኑ አንዳንድ የሌላ እምነት ተከታዮች አጋር በመሆንና በመሳተፍ ጭምር ይታደማሉ።

ጥምቀት ከተለያዩ ዓለም ሀገራት ጭምር የሚታደሙበት በዓል መሆኑም ይታወቃል። ከመንፈሳዊ ይዘቱ በተጨማሪ ሰዎች ማኅበራዊ ኩነቶችንም በማከናወን አብሮነታቸውን ያጠናክሩበታል። የጥምቀት በዓልን መነሻና ሥርዓት፣ እንዲሁም ለሰው ልጆች ሰላም፣ አብሮነትና አንድነት ያለውን አበርክቶ ከሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በተያያዘ መልስ እንዲሰጡን ከመልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ ፈንታሁን ጋር ቆይታ አድርገናል።

መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ ፈንታሁን በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት ደብረ ታቦር እየሱስ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው የተወለዱት። ዘመናዊ ትምህርት ተወልደው ባደጉበት አካባቢ በሚገኙ ዕድገት ፈለግ፣ ጻዲቁ ዮሐንስ፣ አሸዋ ሜዳ ትምህርት ቤቶች በመከታተል እስከ 10ኛ ክፍል ተምረዋል። በጎንደር ፖሊ ቴክኒክ የሙያ ማሰሠልጠኛ በቱሪዝም ዘርፍ በደረጃ ሦስት (በሌቨል ስሪ) ተመርቀዋል። ወደ መንፈሳዊው (የቤተ ክርስቲያን ትምህርት) በማዘንበል ዜማ፣ ቅኔ፣ ወደ ሰሜን ጎንደር በማቅናትም፤ አራቱ ጉባኤያት የሚባሉትን ትርጓሜ መጻሕፍት ጭምር ተምረዋል።

መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ በመንፈሳዊ ትምህርትና አገልግሎት ከቆዩ በኋላ ነው ወደ ሥራ የገቡት። ከ2006 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ደብረ ታቦር እየሱስ ቤተ ክርስቲያንን በማስተዳደር አገልግለዋል። ከ2011 ዓ.ም ታኅሣሥ ወር ጀምሮ ደግሞ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኘው በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል ኤዲቶሪያል ቦርድ አርትዖት ክፍል ውስጥ እያገለገሉ ይገኛሉ። በተጨማሪም በአዲስ አበባ ከተማ ሀገረ ስብከት በየረር መካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የአራት ጉባኤያት የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር ናቸው። አዲስ ዘመን ጋዜጣም በዓሉን ምክንያት በማድረግ ከመልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ ፈንታሁን ጋር ያደረገውን ቆይታ ታነቡ ዘንድ ይጋብዛል። መልክም ንባብ።



**አዲስ ዘመን ፡ የጥምቀት በዓል መነሻና ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ይግለጹልን?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** የጥምቀት በዓል መሠረቱ እየሱስ ክርስቶስ ነው። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ተነሥቶ ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመውረድ ወይንም በመሄድ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ። ይህን ቀን ለማሰብም ታቦታት ጥር ዐሥር ቀን ከማደሪያቸው ወጥተው በባሕረ ጥምቀት ያድራሉ። በእየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት የሚያምኑ የእምነቱ ተከታዮች በዓሉን የሚያከብሩት ለመጽደቅ ነው። በዓሉ የአደባባይ በመሆኑ ከእምነቱ ውጭ ያሉት በመዝናኛነት ሊወስዱት ይችላሉ።

**አዲስ ዘመን፡ ጥምቀት ከተራና ማግሥት አለው። የዚህ ምሳሌ ምንድን ነው? ወይንም ምንን ያሳያል?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** ከተራ ማለት ከበበ ማለት ነው። በዓለ ጥምቀትን ለማክበር ውኃ ያስፈልጋል። የሚመረጠው ወንዝ ነው። ወንዝ ከሌለ ግን ክብ ቅርጽ ባለው ነገር ውስጥ ውኃ ይዘጋጃል። በከተራ ከማደሪያቸው የሚወጡ ታቦታት በወንዝ ወይንም በተዘጋጀ የውኃ አካባቢ ያድራሉ። ይህም ክርስቶስ ከገሊላ ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ የመውረዱ ምሳሌ ነው። እያንዳንዱ ቤተ መቅደስ የሚመሰለው በገሊላ ነው።

ታቦታቱ የሚያድሩባቸው ሁሉ በዮርዳኖስ ነው የሚመሰሉት። ማኅሌቱ፣ ቅዳሴው አጠቃላይ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ስለሚከናወን ማደሪያዎቹ እንደ ቤተ ክርስቲያን ነው የሚቆጠሩት። ጥር 11 ቀን ከቅዱስ ሚካኤል ታቦት በስተቀር ሁሉም ታቦታት ወደ መንበረ ክብራቸው ማደሪያቸው ይመለሳሉ። የቅዱስ ሚካኤል ታቦት የሚቀረው በዓሉ በ12 በመሆኑ ነው።

በዓሉም ቃና ዘገሊላ በመባል ይታወቃል። ጥር ወር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ትልልቅ በዓላት የሚከበሩበት በመሆኑ እንደየአካባቢው የታቦታት ንግሥ ሥርዓት ይከናወናል። ለምሳሌ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ክብረ በዓል ጥር 21 ቀን ይከበራል። በተለይም በጎንደር አማኙ ሎዛ ማርያም ብሎ የሚጠራት ቤተ ክርስቲያን ጥር 21 ትልቅ ክብረ በዓል በመሆኑ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱም በዚያው ልክ ከፍ ያለ ነው።

ቅዱስ ሚካኤል የራሱ የሆነ ክብረ በዓል ስላለው ለብቻው በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር ሲባል ነው ከሌሎቹ ወደ ኋላ የሚቀረው። ይህም የሆነው በጥንት ሊቃውንት በመወሰኑ ነው። በዓፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በካሌንደር ዝግ ሆኖ ይከበር ነበር። በዓፄ ገብረ መስቀል ዘመን በነበረው ሥርዓት ታቦታት፣ ጥር 11 ቀን ከመንበራቸው ወጥተው በዕለቱ ተመልሰው ይገቡ ነበር። በቅዱስ ላልይበላ ዘመን ደግሞ በከተራ ጥምቀተ ባሕር አድረው በማግሥቱ ነበር የሚመለሱት። በዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ደግሞ ታቦታት ሁሉም አካባቢ በረከት ያግኝ ወይንም እንዲባርኩ በሚል ታቦታት በሄዱበት እንዳይመለሱ የሚል ሥርዓት ተሠራ።

በተለያየ ጊዜ የተለያየ ሥርዓት ቢወጣም ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ለማከናወን አንድ ቀን በቂ እንዳልሆነ ግንዛቤ በመያዙ፣ የአማኙም ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ፣ በታሪክ ሂደት ሁለት ቀን ሊሆን ችሏል። የታቦታቱ ተምሳሌት ለሚለውም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ታቦት የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይም ያለ ነው። ታቦትን ለመጀመሪያ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተቀበለው ደግሞ ነብዩ ሙሴ ሲሆን ታቦት የተቀበለባት ቦታ ደብረ ሲና ትባላለች።

ነብዩ ሙሴ ታቦቱን ለመቀበል 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾሟል። ታቦት ከመንበሩ ከማደሪያው ወጥቶ ጥምቀተ ባሕር የሚያድረው ለባዕለ ጥምቀት ብቻ ነው። ነገር ግን ሀገር አደጋ ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ ሊወጣ የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ለአብነትም ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያ በኃይል በወረረበት ጊዜ አባቶቻችን የአራዳ ጊዮርጊስን ታቦት ይዘው ነበር ዐድዋ የዘመቱት።

**አዲስ ዘመን፡ የጥምቀት በዓልን በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ ነው የሚታደመው። የዓደባባይ በዓል የተባለው ለዚህ ነው ወይንስ ሌላ ምክንያት አለው?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** መስከረም 17 ቀን የሚከበረው መስቀልና ባዕለ ጥምቀት የአደባባይ በዓላት ናቸው። ጥምቀት የአደባባይ በዓል የተባለው ታቦታት ከመንበረ ማደሪያቸው ወጥተው በባሕረ ጥምቀት በማደራቸው ነው። አደባባይ ስፋትን ያሳያል። በጥንት ጊዜ በአደባባይ ነጋሪት ይጎሰማል፣ የሀገር መሪ ዐዋጅ ያስነግራል፣ ልዩ ሀገራዊ መልእክትም ሆነ ብሔራዊ በዓላትም በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበሩት በዓደባባይ ነው። ሌላው ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚሳተፍበት በመሆኑ ከአደባባይ ውጭ በአሉን ማክበር አይቻልም።

**የጥምቀት በዓል መሠረቱ እየሱስ ክርስቶስ ነው። ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ተነሥቶ ለመጠመቅ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመውረድ ወይንም በመሄድ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ**

በዓሉ በዚህ ሁኔታ እንዲከበር ደግሞ ቅዱስ ያሬድ መሠረት ነው። የቅዱስ ያሬድ ዜማ ባይኖር፣ ሥርዓተ ማኅሌቱ፣ ጸናጽሉ፣ መቋሚያው እንዲሁም የአለባበስ ሥርዓቱ፣ ካባው፣ አናት ላይ የሚጠመጠመው ሻሽና ሌሎችም ለበዓሉ ደምቀት የሆኑ ነገሮች ባይኖሩ በዓሉ ደማቅ አይሆንም ነበር። በተጨማሪም የቅዱስ ያሬድን ትምህርት የተማሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የድጓ፣ የአቋቋም፣ የቅኔ፣ የዝማሬ፣ የቅዳሴ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን በዓሉ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር ያደርጋሉ። ከእምነቱ ተከታይ ውጭ ያሉትን ከሚስቡት ነገሮች አንዱ የሊቃውንቱ ሽብሸባ፣ በአንድ አይነት አልባሳት የሚደምቁት የማኅበረ ቅዱሳን አባላት፣ በእያንዳንዱ አጥቢያ የሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ መዘምራን እና መዘምራት፣ ምእመኑም ወንዱ በሆታ፣ ሴቱ በእልልታ የሚያደረጉት እጀባ ሁሉ ለበዓሉ ድምቀት ይሰጠዋል።

**አዲስ ዘመን፡ በዕለተ ጥምቀት የሃማኖት አባቶች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ የማኅበረ ቅዱሳን አባላት ከሚጠቀሙት አልባሳት በተጨማሪ ግዴታ የሆነ የአለባበስ ሥርዓት ካለ ከነምክንያቱ ቢያስረዱን?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** ሰው የሌለውን እንዲለብስ አይገደደም። ግን ደግሞ አልባሳቱ ነጭ ቢሆኑ ይመረጣል። ጥምቀት የደስታ፣ የፍቅርና የአንድነት ነው። ነጭ ደግሞ የእነዚህ መልካም ነገሮች መገለጫ ነው። ነጭ በመጽሐፍ ቅዱስ የደስታ፣ የድል ምልክት ነው። በዓለ ጥምቀት የቅድስት ሥላሴ አንድነት፣ ሦስትነት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ጥምቀት ኢትዮጵያውያንን...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

የተገለጠበት፣ የእየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ትሕትና፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ልዕልና የተገለጸበት፣ ዮርዳኖስ የተቀደሰበት፣ የእዳ ደብዳቤ የተቀደደበት፣ መንፈስ ቅዱስ በነጭ ርግብ አምሳል ወርዶ በእየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ ሲቀመጥ የታየበት ነው። እነዚህ ሁሉ የደስታ መገለጫዎች ናቸው።

በዓለማዊውም ‹‹ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ›› የሚል አባባል አለ። ይህም በዓለ ጥምቀቱ ንጹሕና ጸዐዳ በሆነ ሁኔታ መከበር እንዳለበት ያስገነዝባል። በዓለ ጥምቀት በአለባበስ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊውም ጭምር ጠንካራ መሆንን እንደሚገባ የሚያስገነዝብ በዓል ነው። ታቦት ከመንበረ ማደሪያው ወጥቶ ከመንፈሳዊ ነገር ውጭ ሌላ ነገር ሊታሰብ አይገባም።

**አዲስ ዘመን፡ በዓሉ መንፈሳዊ ቢሆንም ማኅበራዊ ዕሴትም አለው። አንድነቱና ልዩነቱ እንዴት ይገለጻል?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** በቤተ ክርስቲያን ልዩነት የሚባል ነገር የለም። ክርስቶስ ሰው የሆነው የተጣለውን ዓለም አንድ ለማድረግ ነው። ማኅበራዊ ወይንም ማኅበር አንድነትን ነው የሚያሳየው። የኢትዮጵያ ባህል ከሃይማኖቱ የሚቃረን አይደለም። በተለይ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ባህላቸው ከቤተ ክርስቲያን የወጣ አይደለም።

በበዓለ ጥምቀት የሚዘፈነው ዘፈን ማወደስ ስለሆነ እንደ ኃጢአት አይታይም። የዘፈናቸው ግጥም ከመንፈሳዊ ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ

« ሴቶች ስሚ ስንቅ ነው የእመቤቴ፤ ስሚ ስንቅ ነው የእመቤቴ፤ አንድ እንጀራ ሳልይዝ ስወጣ ከቤቴ... »

የሚሉት አንዱ ሲሆን፣ በሌላኛው ወገን ደግሞ አሞራው በሰማይ ሲያይህ ዋለ፣ አሞራው በሰማይ ሲያይህ ዋለ... እነዚህ ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው። መንፈሳዊ ይዘታቸውን የለቀቁ አይደሉም። በተለይ የገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል መንፈሳዊና ባህላዊ ዕሴቶችን ጠብቆ በማቆየት በኩል ይጠቀሳሉ።

ጥምቀት መተጫጫ ተድርጎም በማኅበረሰቡ የሚነገረው፤ ጥምቀት ላይ ብዙ ሕዝብ የሚታደምበት በመሆኑ እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች ይኖራሉ። አንድ ወንድ በበዓለ ጥምቀት ላይ አይቷት ለትዳር የፈቀዳትን ልጅ አካባቢዋን፣ ቤተሰቧን አጥንቶ ለወደ ፊት ለማመቻቸት እንጂ በዕለቱ የሚያደርገው ነገር የለም። አሁንም የገጠሩን ነው የማነሣው። ባህሉ በሚፈቅደው መሠረት ሽማግሌ ወደ ቤተሰቧ ልኮ ነው ጋብቻው ሕጋዊ የሚሆነው።

**አዲስ ዘመን፡ አንዳንድ ሀገሮችም የጥምቀት በዓልን ያከብራሉ። የኢትዮጵያ ግን በተለየ ሁኔታ ይታያል፤ ምክንያቱ ምንድን ነው?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** ከልደተ ክርስቶስ እስከ 451 ዓመተ ምሕረት ድረስ የክርስትና ሃይማኖት አንድ ነው የነበረው። ሁለትም፣ ሦስትም አልነበረም። ከ451 በኋላ ነው ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በሚል የተለየው። ከ1520 ዓመተ ምሕረት በኋላ ደግሞ ጀርመናዊው ሉተር ከካቶሊክ አፈንግጦ ወጣ። ስለዚህ ተለያየ። ስለዚህ የኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚባሉት የጥንቱን ይዘው ቀጠሉ። የጥንቱን ይዘው የቀጠሉት ጥምቀትን ያከብራሉ።

እነዚህም የግብጽ፣ የአርመን፣ የሶርያ፣ ሕንድ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን እና የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያን የሚባሉት ሩሲያ፣ ዩክሬን፣ ሮማኒያ፣ ቡልጋሪያ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ጆርጂያ፣ ሀገሮች በዓለ ጥምቅትን ያከብራሉ።

የኢትዮጵያ ግን ከእነዚህ ሁሉ ይለያል። ቅዱሳት በዓላት በደመቀ ሥርዓት እንዲከበሩ ያደረገው ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ ዜማውን ሲደርስ በዜማው አገልግሎቱን ሰፊ አደረገው። ሰፊ የሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጥባት ሀገር በዓለም ላይ ኢትዮጵያ ብቻ ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 24 ሰዓት ነው አገልግሎት የምትሰጠው። በሌላው ዓለም እንዲህ ያለ አገልግሎት የለም። ለዚህ ደግሞ ትልቁ ባለቤቱ መንፈስ ቅዱስ የገለጸለት ቅዱስ ያሬድ ነው። ቅዱስ ያሬድ ባይኖር ኖሮ አሁን ባለው መልኩ የጥምቀት በዓልን ማክበር አይቻልም ነበር። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ልዩ የሚያደርጋት ሥርዓተ ማኅሌት ስላለው ነው።

**አዲስ ዘመን፡ እንደ ጥምቀት ያሉ በዓላት፣**



**ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ያላቸው አበርክቶ እንዴት ይገለጻል?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** ማኅበራዊ ኑሮ ለመኖር መጀመሪያ ሰላም ያስፈልጋል። ሰላም ወደ ፍቅር ያመጣል። ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ደስታን መነጣጠል አይቻልም። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አጠቃላይ ይዘቱ ሁሉ መንፈሳዊ ነው። መንፈሳዊ ከሆነ ደግሞ ከሥጋዊ ነገር የራቀ ነው። ለምሳሌ ፀብ፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ምቀኝነት፣ አድመኝነት፣ ሌብነት፣ ተንኮል ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወት ቦታ የላቸውም። በዓለ ጥምቀት የማይተዋወቁትን በማስተዋወቅ፣ የተራራቁትን በማቀራረብ፣ የተጣሉ ቢኖሩ እንዲታረቁ በማድረግ ፋይዳው የጎላ ነው። አብሮ መጫወት፣ መብላት መጠጣቱም ልዩነትን ያርቃል። አብሮ የበላን ቅዱስ ዮሐንስ አይሸረውም የሚባለው ለዚህ ነው። ሰው አብሮ የሚሆንበት ቀን ደግሞ በዓለ ጥምቀት ነው። ስለዚህ በዚህ ወቅት ማኅበራዊ ትስስሩ የበለጠ ይጠናከራል። በሃይማኖታዊ ሥርዓቱም ቢሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚነገረው።

የተበደለ እንዲካስ፣ የተጣላ እንዲታረቅ፣ ሀገር ሰላም እንድትሆን ነው የሚጸለየው። መንፈሳዊ ነገር ሁሌም ጤና ነው። የሰውን አእምሮ ጤናማ የሚያደርገው ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በበዓለ ጥምቀቱ ታቦታት ጥንድ ድርብ በለበሱ ቀሳውስት፣ በሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን በብዙ ሕዝብ ታጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ሲሄዱ፣ ሲመለሱም ያለ እንከን መሆኑ በራሱ ሰላም ነው። በዓሉን ሊያከብር የወጣ ሰው ችግር ሊፈጥር ቀርቶ የጠፋ ዕቃ ቢያገኝ እንኳን ለባለቤቱ ነው መመለስ የሚጠበቅበት።

ከዚህ ውጭ ችግር የሚፈጥሩ ቢኖሩ በዓሉ በሰላም እንዲከበር የማይፈልጉ፣ ኢትዮጵያም ሰላም እንድትሆን ፍላጎት የሌላቸው ናቸው። ማኅበራዊ ዕሴቱ ከኢትዮጵያም አልፎ ዓለምን የሚያስተሳስር ነው ማለት ይቻላል። በዓለ ጥምቀትን ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት በርካታ ሰዎች ይመጣሉ። እንዲህ ዓለም በአድናቆት የሚያየውንና በበዓሉ ላይ ለመታደም በየዓመቱ ጓጉቶ የሚመጣ እያለ እኛ ለምንድን ነው እንቅፋት ለመሆን የምንሞክረው ? እንዲህ ማድረግ አግባብ አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡ በዓለ ጥምቀቱን የሰላም እና የፀጥታ ስጋት አድርጎ የማየቱ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተስተዋለ ነው። ይህ በሃይማኖቱም ሆነ በአማኙ ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ሲኖር ስለሚችል እዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ለሀገር አንድነት ስጋት የሚፈጥር ነገር ነው። ከላይ ያነሣናቸውን በዓሉ ከመንፈሳዊ ይዘት ባለፈ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕሴቶች ያለውን መልካም የሆነ ፋይዳዎች የሚንድ ነው። በዓላት የደስታ፣ የፍቅርና የሰላም ምንጭ እንጂ የስጋት ምልክት መሆን የለባቸውም። አንዳንዴ ለሀገር ሰላምና ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ሲባል በጥንቃቄ የሚያዙ ነገሮች አሉ። ፀረ ኦርቶዶክስና ኢትዮጵያ የሆኑ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች አሉ። በትክክል የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማኝ ከሆነ የተቀመጠን እንቅፋት ያነሣል እንጂ እንቅፋት አይሆንም። ነገር ግን መስሎ፣ ሰርጎ በመግባት ኢትዮጵያ ሰላም እንዳታገኝ፣ ወደ ልማት ፊቷን እንዳታዞር፣ የሀገሪቱም ፖለቲካ እንዳይረጋጋ ህዝቧም በሰላም ወጥቶ እንዳይገባ የሚያደርጉ በውስጥም በውጭም አሉ። ፈታኞቹ ግን በሀገር ውስጥ ያሉት ናቸው።

በተለይ ደግሞ ከመንግሥት አቅምም በላይ የሆኑት ማኅበራዊ ድረ ገጾች (ሶሻል ሚዲያዎች) በአካባቢ ላይ ያልተፈጠረን እንደተፈጠረ አድርጎ በማቅረብ፣ ችግር የመፍጠራቸው ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ነው። በተለይም ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸውን ቅዱሳት በዓላት ላይ ተጽዕኖ እየፈጠሩ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳን በዓላትን ስታከበር የሌላ እምነት ተከታዮች የሆኑ ከጎኗ ሆነው የሚተባበሩ መኖራቸው አይዘነጋም። እነዚህ ሊመሰገኑ ይገባል። ሁሉም እንዲህ ነው መሆን ያለበት። ኦርቶዶክስም ለሌላው እምነት ቀናኢ ናት።

ችግር የሚፈጥሩ አካላት ሥርዓት እንዲይዙ የሚያደርገው ሕግ ነው። ሕግ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል። ሕጉን በማስፈጸም መንግሥት ድርሻውን የሚወስድ ቢሆንም ለሰላም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘብ መቆም አለበት። በተለይ ደግሞ በዓለ ጥምቀቱ በሰላም እንዲከበር የማድረጉ ኃላፊነት የሁላችንም ነው። በመላ ሀገሪቱ ከ40 ሺህ በላይ ታቦታት ናቸው ከመንበረ ማደሪያቸው ወጥተው በባሕረ ጥምቀቱ የሚያድሩት። ለዚህ የፀጥታ ኃይል በመመደብ ብቻ ስጋቶችን ማስቀረት አይቻልም። መገንዘብ የሚገባን ነገር ሰላምን በማወክና በማደፍረስ የሚያስጨንቁት ጥቂቶች ናቸው። አንድነቱና መተባበሩ ካለ እነዚህን ጥቂቶች መከላከልና መቋቋም ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡ ጥምቀት የሰላም በዓል ነውና ሰለሀገራችን ሰላም ጥቂት ቢሉን ?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** በጣም በርካሽ ዋጋ ሲበዛም ደግሞ በነፃ የምናገኘው ውኃ ነው። ሰላም ንጹሕ ውኃ ነው። እንቅልፍ ነው። ሰላም ቅዱስ ተግባር ነው። ሰላም የቤተ ክርስቲያን የዘወትር ጸሎት ነው። ትምህርትም ይሰጣል። አዎ አሁን ላይ ሀገራችን ችግር አለ። ግን ችግሩ እንዴት ይፈታ ነው ዋናው ነገር መሆን ያለበት። በሀገራችን ብሂል ዕርቅ ደም ያደርቅ ይባላል። ተቀራርቦ መነጋገር ነው የሚያስፈልገው። ለዚህም ሦስት ነገሮች አሉ። እንደ ሃይማኖት ሰማያዊ፣ እንደ ዜግነት ኢትዮጵያዊ፣ እንደ ሰው ዓለም ዐቀፋዊ ናቸው። የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታው በእነዚህ ነው።

እዚህ ላይ የምሁራን ዕውቀት መፍትሔ ማምጣት መቻል አለበት። ለዚህ ሁሉ ቅንነትና እውነት ያስፈልጋሉ። እግዚአብሔር ልቦናቸው ቅን ለሆነ ለእስራኤል እጅግ ቸር ነው ይላል። ጠማማ ልብ ከ እግዚአብሔር ያርቃል። ሰው ከ እግዚአብሔር ጋር ነው መኖር ያለበት። ሰው ሰውን መውደድ ነው ያለበት። በሰዎች መካከል የሐሳብ ልዩነት አለ። አንድ እንዲሆንም አይጠበቅም። የሐሳብ ልዩነት ዕውቀትን የሚያፈልቅ እንጂ የሚያለያይ መሆን የለበትም። በሀገራችን የተፈጠረው አለመረጋጋት፣ ጦርነት፣ ድርቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም የሚስተዋለው ፈተና እጅግ ያሳስባል። ለእነዚህ ሁሉ ችግሮች ደግሞ ዋናው ተግዳሮት ዘረኝነት ነው። ሆኖም ግን ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ ማበጀት ይቻላል። ዋናው መሆን ያለበት ያለመሰልቸት መወያየት፣ መነጋገር ነው።

የችግሩን መንስኤ ከሥር መሠረቱ አውጥቶ መመርመር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያውያንን እያጣላ ያለው የቋንቋ ችግር ነው ? የቋንቋ ቅዱስም፣ እርኩስም የለውም። ቋንቋ አያጣላም። ጎሣም ቢሆን አያጣላም። ምክንያቱም ሰው ዘሩን ወይንም ጎሳውን መርጦ ስለማይወለድ። አንዱ የሌላውን ቋንቋ መናገር ቢችል ይመረጣል እንጂ አያጠላም። የሚገባው ለግጭት መንስኤ የሆነውን መለየት ነው። ብዙ ሀገሮች ችግሮቻቸውን የፈቱት በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት ነው።

**አዲስ ዘመን፡ የሐሳብ ልዩነቶች በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲፈቱ፣ ሀገራዊ ምክክር እንዲደረግም መንግሥት ጥረት እያደረገ ይገኛል። የመንግሥትን ጥረት በማገዝ በኩል ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምን ይጠበቃል?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** መንግሥት ብቻውን መፍትሔ ሊያመጣ ስለማይችል ምክክሩ አሳታፊ መሆን አለበት። ያገባኛል የሚሉ ወገኖች ሁሉ መሳተፍ ይኖርባቸዋል። የቤተ ክርስቲያን የዘወትር ጸሎቷ ስለሰላም፣ ስለሀገር ነው። ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ ለዓለም ጭምር ነው የምትጸልየው።

**አዲስ ዘመን፡ ጥምቀት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሳይንስ የባህልና ትምህርት ድርጅት (ዩኔስኮ) ተመዝግቧል። መመዝገቡ ያለውን ጠቀሜታ እንዴት ይገልጡታል ?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** ዩኔስኮ ትልቅ ተቋም ነው። በዚህ ድርጅት ጥምቀት መመዝገቡ ፋይዳው ብዙ ነው። አንድን ነገር ዓለም ሲያውቀው ከፍ እያለ ነው የሚሄደው። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ስሟ ሲነሣ ለሁላችንም ትልቅ ክብር ነው። በዚህ የጥምቀት ወቅት ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት ይመጣል። ቱሪስት በመምጣቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ በማጓጓዝ፣ ባለሆቴሎች በሚሰጡት አገልግሎት አትራፊ ይሆናሉ። አነስተኛ ሥራ ላይ የተሰማሩ ዜጎች ሳይቀሩ ይጠቀማሉ።

ዕውቅናው ጸንቶ እንዲቆይና ዘላቂ እንዲሆን በዓለ ጥምቀት ሥርዓቱ ተጠብቆ እንዲከበር ሁላችንም ድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል። ከውጭ ሀገራት የሚመጡ የመገናኛ ብዙኃን መልካሙን ገጽታውን ትተው በበዓለ ጥምቀት ሰው ተደበደበ፣ ሞተ በሚሉት ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የኢትዮጵያን ስም እንዳያጠፉ ማድረግ የምንችለው እኛ ነን።

**አዲስ ዘመን፡ እስከ አሁን ከተነጋገርነው ውጭ ያልተነሣ ነገር ካለ፣ እንዲሁም ተጨማሪ መልእክትም ካለዎት?**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** በቅድሚያ ለሁሉም የእምነቱ ተከታዮች እንኳን ለበዓለ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ ማለት እፈልጋለሁ። በዓሉ በሰላምና በደስታ እንዲከበር ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ውጭ የሆኑ ወገኖችም እንደ እስከ አሁኑ ተባባሪ እንዲሆኑ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡ መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ ፈንታሁን ለቃለ መጠይቅ ስለተባበሩን እናመሰግናለን።**

**መልአከ ታቦር ኃይለ እየሱስ፡** እኔም በዓለ ጥምቀትን በተመለከተ ሐሳብ እንድሰጥ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# ወቅታዊ

## " በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እናሳካቸዋለን ብለን ካስቀመጥናቸው ግቦች አኳያ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥሩ ውጤት እያመጡ ነው"

የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር)


ፎቶ ፡- ዳኜ አበራ

ወርቅነሽ ደምሰው

**የኢኖቬሽን እና የቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ በለጠ ሞላ ዶ/ር ከትናንት በስቲያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ዙሪያ ያለውን ሀገራዊ እውነታ ፤ ከጋዜጠኞች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርገዋል ፤ የቃለ መጠይቁን ሙሉ ቃል እንደሚከተለው አቅርበነዋል።**

**ጥያቄ፡- እንደ ሀገር ለቴክኖሎጂ የተሰጠው ትኩረት ምን ይመስላል?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** እንደ ሀገር ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች የኢኖቬሽን፣ የቴክኖሎጂና የአይሲቲ ዲጂታላይዜሽን ዘርፍ አንዱ ነው። ይህም በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ ውስጥ እንዲሁም በሀገር በቀል ኢኮኖሚው፣ በደንብ ተሰምሮበት የተቀመጠ ነው። በቀጣይ ለሚገነባው ሀገራዊ ኢኮኖሚ እንደምሰሶ ሆነው ይቆማል ተብለው ከተለዩ አምስት /የማዕድን፣ የግብርና፣ የማኑፋክቸሪንግ፣ ቱሪዝምና አይሲቲ / ዘርፍ አንዱ ነው። ይህም መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት እንደተሰጠው በተጨባጭ የሚያሳይ ነው።

በቅርብ ጊዜ ሁላችንም እንደምናውቀው መንግሥት ከወትሮ በተለየ ሁኔታ ዘርፉን ሊብራላይዝድ አድርጓል። ለዚህም የቴሌ ካም ኢንደስትሪው ማንሳት ይቻላል፣ ዘርፉ በሀገራችን ከመቶ ዓመት በላይ አንድ ለእናቱ ነበር። አሁን ሊብራላይዝድ ተደርጓል፤ ይህ በመንግሥት በኩል የተወሰደው ርምጃ በጣም ትልቅ ነው።

ከዚህም ሳፋሪኮም ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ገበያ ውስጥ እንዲሳተፍ ተደርጓል። አሁን በኢትዮጵያ በቴሌኮሙ ኢንዱስትሪ ውስጥ ሥራ እየሰራ ነው። ይሄ ዘርፉን ሊብራይዝድ በመንግሥት በኩል የተወሰደው ርምጃ በርግጥም መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት መስጠቱን የሚያሳይ አንድ ቀዳሚ ምሳሌ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው።

ሌላው የአይሲቲ መሠረተ ልማቶች ግንባታ ላይ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። መሠረተ ልማቶቹ አቅም በፈቀደ መልኩ እንዲስፋፉ እንዲገነቡ፤ የኮኔክቲቪቲ ተደራሽነት እንዲስፋፋ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። በዚህም በአጠቃላይ በሀገራችን 35 ነጥብ 1 ሚሊዮን ሕዝብ የብሮድባንድ ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ሆነዋል።

ይሄ ቀላል ቁጥር አይደለም። 35 ሚሊዮን ሕዝብ ማለት እኛ ዝቅ ብለን ስለጀመርን ብዙ ላይመስል ይችላል። ግን በጣም ትልቅ ነው ። 35 ሚሊዮን የሦስት የአራት የአፍሪካ ሕዝብ በአንድ ላይ ተደምረውን እንደ ማለት ነው። ይሄ በጣም ከፍተኛ እመርታ ነው። ከዚህም ባለፈ መረጃዎች እንደሚያሳዩት 73 ነጥብ1 ሚሊዮን ሕዝብ የሞባይል ተጠቃሚ ነው።

ሌላው የክፍያ ሥርዓቱን ካየን ፤ ጎልህ በሚባል መልኩ ብዙ ለውጦች እየታዩበት ነው። ባንኮቻችንን "ከአናሎግ" አሠራር እየወጡ አሁን ሙሉ ለሙሉ ወደ ዲጅታል አሠራር እየገቡ ነው። የክፍያ ሥርዓቶች ዲጂታላይዝድ ሆኗል። በዚህም በትሪሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ውስጥ እየተዘዋወረ ነው።

ይሄ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ተከትሎ የመጣ ውጤት ነው። በርግጥም ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑን በተጨባጭ መመልከት የተቻለበት ውጤት ነው።

**ጥያቄ፡- በዘርፉ እየተካሄደ ያለው የመሠረተ ልማት ግንባታ ከዘርፉ የአስር ዓመት ዕቅድ አንጻር ምን ያህል በዕቅድ ተጉዘናል የሚያስብል ነው ?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** በዘርፉ እየተካሄደ ያለው የመሠረተ ልማት ግንባታ በጥሩ ደረጃ ላይ ነው ማለት ይቻላል። ይሄ ማለት ተግዳሮት የለም ማለት አይደለም። የቴክኖሎጂና የአይሲቲ ጉዳይ እንደሚታወቀው ኮፒታል መሠረት ያደረገ ነው። በመንግሥትም በግሉም ዘርፍ በሚደረግ ጥረት ብቻ ሳይሆን ኢንቨስትመንት ከውጭ መሳብን የሚጠይቅ ነው።

በአስር ዓመቱ የልማት እቅድ ውስጥ እናሳካቸዋለን ብለን ካስቀመጥናቸው ግቦች አኳያ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ጥሩ ውጤት እያመጡ ነው። በቀጣይ የሚያጋጥሙንን ተግዳሮቶች እየፈተሽንና እየገመገምን ፤ በማስተካከያ ርምጃዎች እየወሰድን እና ክፍተቶቻችንን እየሞላን ከሄድን በዘርፉ ያስቀመጥነው የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ በሙሉ የሚሳካበት ዕድል አለ። ተግዳሮቶችም አሉ። እነሱን በቀጣይ መቋቋም እየቻሉ መሄድ ያስፈልጋል።

**ጥያቄ፡- እርስዎ ከሚመሩት ዘርፎች አንዱ ኢትዮጵያ ትልቅ ኢንቨስትመንት ያወጣችበት የአይ.ሲ.ቲ ፓርክ ተጠቃሽ ነው። ፓርኩ እስከ አሁን ድረስ በሙሉ አቅሙ እየሠራ አይደለም ። ፓርኩ በሙሉ አቅሙ እንዲሰራ ሚኒስቴሩ ምን እየሠራ ነው?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** የአይ.ሲ.ቲ ፓርክ ግዙፍ መሠረተ ልማት ነው። ከጎሮ አልፈን ወደ ደብረዘይት መንገድ ላይ የሚገኝ ፤ ወደ 200 ሄክታር ላይ ያረፈ ነው። ከተመሠረተ 15 ዓመት ሆኖታል። በእነዚህ ዓመታት የተለያዩ የመንግሥት ተቋማት እንዲያስተዳድሩት ተደርጓል። መጀመሪያ ሲመሠረት በኤምሲ አይቲ ስር ነበር። ለውጡን ተከትሎ ደግሞ የአይ.ፒ.ዲ.ሲ የኢንደስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን ወደምንለው ተላልፎ አምስት ዓመት በዚህ ሲመራ ቆይቷል።

እኛ ባለፈው ዓመት ከፍተኛ የሆነው የመንግሥት አካል ጠይቀን ፖሊሲና ስትራቴጂ እናወጣለን፤ እነዚህን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ለመፈፀም አስቻይ ከሆኑ መሠረተ ልማቶች አንዱ እንደዚህ ዓይነት የቴክኖሎጂና የአይሲቲ ፓርኮች መኖር ነው። በሚል ጥያቄ አቅርበን ወደ እኛ መጥቷል። ወደኛ ለማምጣት የነበረው ተግዳሮት ግን ቀላል አልነበረም።

ፓርኩ አንደኛ ሙሉ ለሙሉ እንዲለማ የተደረገ አይደለም፤ ከአንዱ ተቋም ወደ ሌላ ተቋም እንዲሸጋገር በተደረገው ውሳኔ መሠረት ከሞላ ጎደል ያለሥራ ቆይቷል። ስለዚህ ወደ እኛም ተቋም ሲመጣ ገና ግልፅ ያልተደረጉ፤ አሁንም ድረስ ብዙ ጥረት እየጠየቁን ያሉ የሰነዶች፤ የውሎች ፤ የአስተዳደር ጉዳዮች አሉ።

እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በጋራ እየሰራን ነው። ስለዚህ አሁን ላይ የቢዝነስ እቅዱን በመከለስ እዚያ የነበሩ፤ ግን የወጡ የግል ኩባንያዎች እንዲመለሱ፤ እዛ ያሉትም ተበራርተው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማድረግ እና አጠቃላይ የማደስ ሥራ እየተሰራ ነው።

በአሁኑ ወቅት የግሉ ዘርፍ እንደ አዲስ የሚሰብ የአሰራር ሥርዓት እንዲሁም ሥራዎች እየተሰሩ የግል ኩባንያዎች እየገቡ ነው። የብሬክ ሊዝ ያመለከቱ ኩባንያዎች እየገቡ ነው። እንደሚታወቀው ደግሞ ፓርኩ ሕንፃዎች አሉት፤ ሕንፃዎቹን ተከራይቶ ለመሥራት ጥያቄ አቅርበው የተቀበልናቸው አሉ፤ በቀጣይ በግምገማ የምንቀበላቸው አሉ።

ሌላው የኃይል አቅርቦት ጉዳይ ቁልፍ ችግር ነበር። እዚያ ውስጥ ትልልቅ የመረጃ /ዳታ ማዕከሎች፤ አገልግሎት የሚሰጡ የውጭ ኩባንያዎች ሀገር ውስጥ ገብተው ብዙ ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት አካሂደው መሠረተ ልማቶችን የገነቡ አሉ። ለምሳሌ ዊንጎ አፍሪካ የምንለው እነራክሲዩ፤ ሬድ ፎክስ፤ ሳፋሪ ኮም የመሳሰሉት በትልልቅ ካፒታል እየገነቡ ነው። ሌሎችም የግል ድርጅቶች እንዲገቡ እየጋበዝን ነው። እየገቡ ነው።

ወደ ሥራ ሲገባ የኃይል ጉዳይ አንዱ እጥረት ስለሚሆን ለዚህ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው። በፊት የነበረው ወደ 2 እስከ 3 ሜጋ የማይበልጥ ነበር። አሁን ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግረን 10 ሜጋ አድርሰናል። አሁን ላሉት በቂ ነው፤ ግን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ለምቶ እንደ‹ማይክሮሶፍት›፣ ‹አይቢኤም›፣ ‹ኦራክል› ያሉ ብዙ ታላላቅ ዓለም አቀፍ የግል ኩባንያዎች እንዲመጡ እየሠራን እንገኛለን።

ተሳክቶልን እነዚህ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ከመጡና ሀገር በቀል ድርጅቶችም ወደሥራው ሲገቡ ብዙ ኃይል ይፈልጋል። አሁን ላሉት አስሩ በቂ ቢሆንም በቀጣይ ወደ 200 ለማሳደግ ከአንድ የቻይና ኩባንያ ጋር በመነጋገር ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ስምምነት ተፈራርመዋል። የራሱን ማከፋፈያ ጣቢያ ገንብቶ ይህን ያህል ኃይል ለአይሲቲ ፓርኩ ማቅረብ የሚችልበት ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል። ይህ አንዱ ተግዳሮት ስለነበር መስመር ዘርግተን 10 አድርሰናል።

የኢንተርኔት ግንኙነት (ኮኔክሽን) ችግርም ነበር። ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ባደረግነው ምክክር የኢንተርኔት ግንኙነት ፍጥነቱ ከፍተኛ ፍጥነት ወዳለው (High Speed Connection) እንዲሸጋገር ተደርጓል። የውሃ አቅርቦት እና የካፍቴሪያ ችግሮችም ነበሩ። እነዚህን ችግሮች ደረጃ በደረጃ እየፈታን ጥሩ ውጤቶችን አይተናል። ነገር ግን ግዙፍ አቅም ያለው በመሆኑ፣ አቅሙን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም እየተከታተልንና እየሠራን እንቀጥላለን። ስፋቱ 200

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# “ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እናሳካቸዋለን ብለን ...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

ሄክታር ነው። ቀጣይ ሥራዎችን የሚጠይቁ ብዙ ተግባራት አሉብን።

**ጥያቄ፡- ስለሲበራላይዜሽን ሲነሳ በአንድ በኩል ‹‹መንግሥት ለብዙ ዓመታት ዝግ አድርጎ ያስቀመጣቸውን ተቋማትን አሳልፎ ለውጭ ሊሰጥ ነው›› የሚሉ ወገኖች ነበሩ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹ሊበራላይዜሽን ጥሩ ነው፤የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ ኢንቨስትመንት መስፋፋትና ዘርፉ ማደግ አለበት›› የሚል አቋም ያላቸው ወገኖች አሉ። በዚህ ረገድ የመንግሥት እንቅስቃሴና ጥንቃቄ ምን ይመስላል? ሌሎች ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉስ ምን እየተሰራ ነው?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** በመንግሥት ጥረት ብቻ ሀገር ሊያድግ አይችልም። ያደጉ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣ በአንዳንዶቹ መንግሥት የመሪነት ሚናውን ወስዶ የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ፣ በሌሎቹ ደግሞ የግሉ ዘርፍ መሪ ሆኖ መንግሥት የቁጥጥር ሥራውን በመሥራት እድገት አስመዝግበዋል። የኢትዮጵያ ተሞክሮ የሚያሳየው መንግሥት ብዙውን ነገር እንደሚመራና እንደሚቆጣጠር ነው። የግሉን ዘርፍ እያሳተፍን ቢሆንም አሁንም በቂ አይደለም።

የግሉ ዘርፍ አቅሙ ጎልብቶ የመሪነት ሚናውን እንዲወስድ ታስቦ እየሰራ ነው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነት የሊብራላይዜሽን ጉዳዮች ብዥታ መፍጠራቸው አይቀርም። ነገር ግን ሊብራላይዝ ከማድረግ ውጭ ያለው አካሄድ አዋጭ አይመስለኝም። አንዳንድ ተቋማት ለመንግሥት ሸክም የሚሆኑበት አጋጣሚ ይፈጠራል፤ መንግሥትም ሙሉ በሙሉ ድርሻውን ሳያጣ፣ የግሉ ዘርፍ የተወሰነውን ድርሻ እንዲይዝና ተቋማቱ የሕዝብን ተጠቃሚነት የበለጠ የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ መንግሥት የወሰደው ርምጃ ትክክለኛ ነው።

ሰዎች ስለሂደቱ ጥያቄ ቢያነሱ፣ እንረዳቸዋለን። የቴሌኮም ኢንደስትሪውን ካየን እንደውም የተሻለ ሆኗል። ተወዳዳሪ ሲመጣ ለሕዝቡ የተሻለ አፈፃፀም እያስመዘገበ እና የተሻለ አገልግሎትን እና አማራጮችን እየፈጠረ ነው። በአፍሪካ ቀዳሚ፤ በጣም ንቁ (ቫይብራንት) ሆኖ የቆመ የቴሌኮም ካምፓኒ እንዳለን በዚህ ሰዓት እያየን ነው። በጣም ተዓምር የሚባሉ ሥራዎችን እየሠራ ነው።

ይህ ውድድሩ የፈጠረበት መነቃቃት ነው ተብሎ ሊቀርብ ይችላል። የሚገባኝ በዛ መልኩ ነው። አገልግሎቶችን ከማስፋት አንፃር እና ተደራሽነትን ከማስፋት አንፃር፣ አዳዲስ አገልግሎቶችን ከማምጣት አንፃር፣ ለሕዝብ ከማቅረብ አንፃር፣ አማራጮችን ከማስፋት አንፃር በጣም ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው።

ሊብራላይዜሽን በአጠቃላይ ጥሩ ነገር ነው። ውድድርን ያመጣል። የተሻለ ምርት ለሕዝብ እንዲደርስ ያደርጋል፤ አማራጭ ያሰፋል፤ የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲፈጠር አስቻይ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው። እንዲህ ዓይነት የተለያዩ ነገሮች ሲመጡ፤ ዕድገትን ያፋጥናል፤ ጥራት ያለው ወይም የተሻለ የኑሮ ደረጃን እየጨመረ ይሄዳል። የሚገባኝ እንደዛ ነው።

**ጥያቄ፡- በፈጠራ ሳይ የሚደረጉ ምርምሮችን ማጠናከር ፤ በተለይ ተቋማት ያላቸውን አሠራር ዲጂታላይዝድ እንዲያደርጉ የተጀመረ ጥረት ነበር። ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል ?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** ምርምርን ከመደገፍ አንፃር ኃላፊነቱን ወስደናል። እንደ ኢኖቬሽን እና እንደምርምር እንደ ቴክኖሎጂ እንደ ዲጂታል ተቋም አጠቃላይ የኢትዮጵያን ሀገራዊ የምርምር ሥነ ምህዳር እንዲመራ ባለቤትነትን እንዲያረጋግጥ ኃላፊነት እና ሥልጣን ተሰጥቶታል።



ምርምሮች መደገፍ አለባቸው፤ የሚደገፉ ምርምሮችም ውጤታማ ሆነው በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ራሱን የቻለ አስተዋፅኦ መጫወት መቻል አለባቸው። እስከ ዛሬ ይህ ተቋም ምርምሮችን ይደግፍ ነበር። ነገር ግን አጠቃላይ የምርምር ሥርዓቱ መፈተሽ አለበት። የተበታነ ነገር አለ። እዚህ እና እዚያ የምርምር ጥረቶች አሉ።

ምርምርን በመደገፍ ጅምር ነገር አለ። እኛ አሁን ላይ እንደተቋም የግምገማ ሥራ እየሠራን ነው። ከአሁን በፊት ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ተቋም የተደገፉ የምርምር ሥራዎች ምን ላይ ደርሰዋል? ስንቶቹ ውጤታማ ሆኑ? ምን ዓይነት ውጤት አሳዩ? ስንቶቹስ ቀሩ ለምንስ ቀሩ? የሚሉትን ሥራ እየሠራን እና እየለየን ነው። በደንብ ከለየን በኋላ ወደ ድጋፍ ሥርዓቱ እንመጣለን። ይሄም ሆኖ ግን ከአጋሮች በሚደረግ ድጋፍ አሁንም እየደገፍን ነው።

ለምሳሌ በዚህ ግማሽ ዓመት ውስጥ ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (ከዩኤንዲፒ) በተገኘ ድጋፍ አስር ምርምሮችን ደግፈናል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ናይሮቢ ኬንያ ውስጥ ከሚገኝ ፤ አፍሪካ ውስጥ የሚደረጉ ምርምሮችን በገንዘብ ከሚደግፍ የቴክኖሎጂ ጥናት ማዕከል ጋር ባደረግነው ስምምነት ፤ ወደ ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ ዶላር ድጋፍ አግኝተን ስድስት ምርምሮችን እያካሄድን እንገኛለን።

በአጠቃላይ በጤና፣ በግብርና እና በኢንደስትሪ ዘርፎች ላይ የሚመራመሩ ሰዎችን አወዳድረን ለይተን ለእያንዳንዳቸው 35 ሺህ ዶላር ሰጥተናል። በዚህ ሰዓት እነዚህ ተመራማሪዎች ሥራ እየሠሩ ነው። ሌላው በተጠሪ ተቋሞቻችን የምርምር ማዕከላት ላብራቶሪዎች ተገንብተው ሥራ እየሠሩ ነው። ጥሩ ጥሩ ሥራዎች አሉ።

ከዲጂታላይዜሽን አንፃር እዚህም ላይ ጥሩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የመንግሥት ሥራዎችን በቴክኖሎጂ ታግዞ የመሥራት እና የኢንተርኔት አገልግሎት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በአጠቃላይ አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ እንዲሆኑ እየሠራን ነው። ወደ 528 የሚሆኑ በሀገር ደረጃ የለሙ የዲጂታል አገልግሎቶች አሉ።

**ከዲጂታላይዜሽን አንፃር እዚህም ላይ ጥሩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የመንግሥት ሥራዎችን በቴክኖሎጂ ታግዞ የመሥራት እና የኢንተርኔት አገልግሎት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በአጠቃላይ አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ እንዲሆኑ እየሠራን ነው። ወደ 528 የሚሆኑ በሀገር ደረጃ የለሙ የዲጂታል አገልግሎቶች አሉ**

ከእነዚህ ውስጥ 321 የሚሆኑት በእኛ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን የለሙ ሥራዎች ናቸው። ይህንን አጠናክረን መቀጠል አለብን። አጠቃላይ የአሠራር ሥርዓቱ ዲጂታላይዝድ እንዲሆን እንድናደርግ ለዘርፉ ኃላፊነት ተሰጥቷል። ስለዚህ እኛም እንደዘርፍ ሌሎችም የመንግሥት ተቋማትም በየድርሻቸው በሚመለከታቸው አገልግሎታቸውን እንዲያዘምኑ እኛ ድጋፍ እንሰጣለን፤ እየሰጠን ነው። ስለዚህ ጥሩ ነገር አለ። ነገር ግን ተግዳሮቶች አሉት።

ከሚለሙ ሥርዓቶች ሙሉ ለሙሉ ወደ ተግባር የማይገቡ አሉ። አንዳንዴ ግምገማ እናካሂዳለን። በሚለሙ ሥርዓቶች ድጋፍ ያደረግንላቸው በርግጥ ሥራ ላይ እየዋሉ ነው ወይ? ብለን ፍተሻ እናደርጋለን። ከዲጂታል አጠቃቀም ትምህርቱም አንፃር ዝቅተኛ እንደመሆኑ መጠን እዚህ ላይ በደንብ ግፊት መደረግ አለበት።

የለሙ ሥርዓቶች በሙሉ ጥቅም ላይ የማይውሉበት ሁኔታ እንዳለም ጭምር እናያለን። ነገር ግን ዞሮ ዞሮ ይሄ እንዲቀረፍ ከትምህርቱ ማለትም ከማንበብ እና ከመፃፉ ፤ ከትምህርት ሥርዓቱ ሆነ ከክህሎት አንፃር ስልጠናዎች በየወቅቱ እንዲሰጡ ፓኬጆችን እየቀረፅን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረግን ነው። በዚህም ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው።

**ጥያቄ፡- አዲስ አበባ ከተማን “ስማርት ሲቲ” የማድረግ እቅድ ነበር። እቅዱ ከምን ደረሰ?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** አዲስ አበባ ከተማን ስማርት ሲቲ የማድረግ እንቅስቃሴ እንደነበር፤ ለዚህም የከተማ አስተዳደሩ ስድስት ቦታዎችን ለይቶ “ስማርት አካባቢ”፣ “ስማርት ኢኮኖሚ”፣ “ስማርት ሞቢሊቲ ትራንስፖርት ሲስተም” ፣“ስማርት ሊቪንግ”፣ “ስማርት ፒውፐል” የሚሉ ኢኒሼቲቮች እንዳሉ እናውቃለን።

የኢኒሼቲቮቹ አላማ የነዋሪውን ሕይወት ምቹና ቀላል ለማድረግ ፤ጥራት ያለው ሕይወትን እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። በቴክኖሎጂ የታገዘ፣ በዲጂታል አይሲቲ “ፕሮቮክድ” የሆነ የሕይወት እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ነው። ከዚህ ውስጥ እኛ እንደ ተቋም “ስማርት ስቲ” የሚለውን ወስደን ወደ “ስታርትአፕ ሲቲ” ማዕቀፍ በመቅረጽ ፤ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክብርት ከንቲባዋ ጋር በቅርቡ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመናል።

ስምምነቱ “የስታርትአፕ ሲቲ” እንዲገነባ ነው። ከተማዋ “ቫይብራንት” የሆነ “የስታርትአፕ” ከተማ ሆና “ስታርትአፖች” እየተደገፉ፣ ካምፓኒ ሆነው የሚወጡበትና ኢኮኖሚውን የሚያግዙበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነው። “ስታርትአፕ” በተፈጥሮው ከከተማ ወደ ገጠር የሚሄድ በመሆኑ በቀጣይ ወደ ክልሎች የሚሰፋ ይሆናል።

ከተማ ላይ ጎልብቶ ውጤታማ ሲሆን፣ የሚገኙ ውጤቶች ተቀምረው ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ይወሰዳሉ። ይሄንን /በአዲስ አበባ ጀመርነውን/ ኢኒሼቲቭ ተግባራዊ ካደረግን በኋላ ወደ ክልል ከተሞች የምንሄድ ይሆናል።

**ጥያቄ፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ብዙ ቴክኖሎጂዎችን ለዓመታት ከውጭ ስንቀዳ ነው የቆየነው፤ ይህንን ከመቀየር አንጻር የሚሰሩ ሥራዎች ምን ይመስላሉ?**

**ዶ/ር በለጠ፡-** ከዚህ አንጻር እኛ “የኢንኩቤሽን” ማዕከላት እየገነባን እንገኛለን። በጥቂት ጊዜ ውስጥ የምናስመርቀው፤ በአይሲቲ ፓርክ ውስጥ የኮሪያ መንግሥት ድጋፍ አድርጎልን እስከ ሶስት ሚሊዮን ዶላር ወጪ የተደረገበት በጣም ዘመናዊ የሆነ “የኢንኩቤሽን” ማዕከል ገንብተን ጨርሰናል። ሃሳብ ያላቸው “ስታርትአፖች ” በማዕከሉ ልምምድ እንዲያደርጉና ጎልብተው እንዲወጡ ለማድረግ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እናሳካቸዋለን ብለን ...

ከ10ኛው ገጽ የዞረ




የሚያስችል ነው።

ሌላው የሳይንስ ካፌዎች በዘጠኝ ክልሎች በመገንባት ላይ ናቸው። በአማካሪዎች ፍተሻ እየተደረገላቸው ነው። ካፌዎቹ የሳይንስ እና ኢኖቬሽን ባህል እንዲስፋፋ ወጣቶችም እነዚህን ማዕከላት ተጠቅመው ፈጣሪ የሚሆኑበትና የሚለማመዱበት ነው። የታለንት ማዕከልም ገንበተናል።

በቴክኖሎጂ የተደገፈ ኢኮኖሚ እውን እንዲሆን ጥረቶች አሉ። ለዚህም ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በጋራ ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን። ከኛ ተጠሪ ተቋማት መካከል አንዱ ፤ የስፔስና ጂኦ ስፓሻል ኢንስቲትዩት ነው። ከእነርሱ ጋር በመሆን ከተሞች አድራሻ ሥርዓታቸውን ዲጂታላይዝ እንዲያደርጉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ፕሮጀክቱ በዓለም ባንክ የሚደገፍ እና በጅምር ያለ ነው። በቀጣይ እሱን ጨርሰን የተወሰኑ ከተሞች ቢያንስ ቢያንስ ዋና ዋና የምንላቸውን ከተሞች የአድራሻ ሥርዓታቸው ዲጂታላይዝድ እንዲሆን ሥራዎች እንሠራለን። ይሄ ሁሉ ተደምሮ ከኢኖቬሽንና ዲጂታላይዜሽን ጋር የሚያያዝ እንደመሆኑ መጠን በዚህ መንገድ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

**ጥያቄ - በቡራዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማዕከል ፍላጎቱ ያላቸው፣ አቅሙ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው የሚሰለጥኑበት አቅማቸው የበለጠ የሚጎለብትበት ለኢትዮጵያ ግብዓት እንዲያመጡ የሚጠበቅ ማዕከል ነው። ይሄ ማዕከል አሁን ያለበት ደረጃ ምን ይመስላል? ምን ምን ሥራዎች እየሠራ ነው?**

**ዶክተር በለጠ፡ -** በጣም ጥሩ! ስለራዕዩ ትንሽ ልበል፤ ቡራዩ ስንል ዝም ብሎ ትምህርት ቤት አይደለም። ቡራዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ማዕከል ወይም ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤት ስንለው እንደሌሎች ትምህርት ቤት አይደለም። ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው የኢትዮጵያ ልጆች ተሰጥዖአቸውን የሚያበለጽጉበትና የሚያዳብሩበት ዕድል በየቦታው የለም፤ መቸገር አለ። ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው አንደኛ በማህበረሰባቸው አንደርስታንድ አይደረጉም፤ ይህ ችግር አለ። ልዩ ተሰጥኦ አላቸው ማለት ትንሽ ወጣ ያለ ባህሪ ሊያሳዩ ይችላሉ።

እንደዛ ባይሆን እንኳን ልዩ ተሰጥኦ ካላቸው ያንን ወደ ውጤት መቀየር እንዲችሉ እንዲያዳብሩት ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ይፈልጋሉ። የባከነ ተሰጥኦ፣ የባከነ ክህሎት፣ የባከነ ዕውቀት እንዳይኖር ከማሰብ አንጻር ቡራዩ ታለንት ማዕከል መገንባት አለበት ተብሎ ታስቦ በዚህ ተቋም ተገንብቷል። በጣም ዘመናዊ ነው። አንድ ሺህ አልጋዎች አሉት፤ እስከ አንድ ሺህ ተማሪ ያስተናግዳል። ቀጣይ ታለንት ሥራዎች እየተሠሩ በሀገሪቱ ታለንት ያላቸው ልጆች መጥተው እንዲሰለጥኑ እንድንሠራ ነው።

እስካሁን በሶስት ዙር ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፣ ከስፔስ ሳይንስ ጋር በመተባበር እነዚህን ታለንት ያላቸውን አስገብተን እያሰለጠንን አውጥተናል። አሁን ላይ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ያሉ ታለንቶችን ደርሰን እዚህ መጥተው ሰልጥነው ክህሎታቸውን አዳብረው ምናልባትም ከተሳካላቸው ፕሮዳክት ይዘው ካምፓኒ መመስረት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንዲኖር የመለያ መስፈርት ጨርሰናል። ፕሮግራም እየሠራን ነው በአሁኑ ሰዓት በዓለም ባንክ አማካሪ ቀጥረን ይህን ሥራ እንዲረከብ እያደረግን ነው።

በአጠቃላይ ይሄ እንዳለ ሆኖ በጥቆማም እንቀበላለን። ከቤተሰቦች ሊሆን ይችላል። ከትምህርት ቤቶች ሊሆን ይችላል። ልዩ ክህሎትና ተሰጥኦ አለው ብለው የሚያስቡት ልጅ ካለ በጥቆማ እየመጣ እየፈተሽን የዚህ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እናደርጋለን። በቀጣይ ይፋ ጥሪዎች ይኖራሉ። በሚዲያ ማስታወቂያው ይገለጻል። ከየትም ቦታ ያሉ ኢትዮጵያውያን አመልክተው የዚህ ሥራዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሥራዎች ይሠራሉ። በዓለም ባንክ አማካሪ ቀጥረን ይህ ሥራ ተጀምሮ እንዲሠራ እዛ ላይ ነው ያለነው።

**ጥያቄ - ኢኖቬሽን በፈጠራ በቴክኖሎጂ የተሻለ ቦታ ለመድረስ የኢትዮጵያውያንን ሕይወት ለማሻሻል የዲጂታላይዜሽን ኢትዮጵያ 2025 ከተጀመረ ዓመታት ተቆጥረዋል። የዕቅዱ አመጣጠም ምን ይመስላል?**

**ዶክተር በለጠ፡-** መጀመሪያ ላይ ያልኩት ከዚህ ጋር ይያያዛል። ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 እስትራቴጂ ተቀርጾ ትግበራ ላይ ነው ያለው። ሶስት ዓመት ከስድስት ወር መጥተናል። 2012 ዓ.ም. ሰኔ አካባቢ ነው ወደ ሥራ ተገብቷል። የግማሽ ጊዜ ግምገማ አካሂደናል። ውጤቶችን አይተናል። እዛ ላይ የተገኙትን ውጤቶች ቆጥረናል። የታዩ ተግዳሮቶችንም ለይተናል። የኢንተርኔት ብሮድባንድ ተጠቃሚ መብዛቱ የሊብራላይዜሽኑ አሁን ላይ ሁለት ኦፕሬተሮች አሉን። የተገነቡ ኢንፍራስትራክቸሮች፣ መሠረተ ልማቶች የሞባይል ቁጥር ተጠቃሚ እያደገ መምጣቱ የክፍያ ሥርዓቱ እያደገ መምጣቱ ይሄ ሁሉ ዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂው ሲነደፍ አሳካቸዋለሁ ካላቸው ግቦች ውስጥ እየተሳኩ ያሉ ውጤታቸው ሊጠቀስ የሚችል ነው።

አሁን ላይ እንዳልኩት ገምግመናል አፈጻጸሙ ምን ይመስላል ብለናል። ክፍተቶችን አይተናል፤ የተገኙ ውጤቶችንም አይተናል። በቀሪ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ውስጥ ያየናቸውን ግምገማዎች መሠረት አድርጎ ክፍተቶችን ለመሙላት ሥራዎች ይሰራሉ።

በግምገማው ችግር ያለባቸውን ጥለን አዳዲስ ሃሳቦችም ካሉ እነርሱን ከስትራቴጂው አኳያ አያይዘን እንሄዳለን። በዚህም እንደ ሀገር የሚኖረን የዲጂታል ላንድ እስኬፕ ከቀደመው እጅጉን የተሻለ ውጤት የሚታይበት ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ጥሩ ነገሮች አሉ፤ ግን ይህ ሂደት ተግዳሮት ያልነበረው አይደለም። አንደኛ የመሠረተ ልማት ግንባታው ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል። ለሀገር ቀላል አይደለም። የግሉ ዘርፍ መጥቶ ከውጭም ኩባንያዎች ተጋብዘው የሚሠሩት ሥራ እንዳለ ሆኖ፤ ይህ በደንብ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። ቀጣይ ተግዳሮት ሊሆን ይችላል። የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነትም ራሱን የቻለ አንድ ሌላ ተግዳሮት ነው።

ሌላው የክህሎት ውስንነት ነው። በፈጻሚውም፣ በተጠቃሚውም፣ በአልሚውም የክህሎት ውስንነት ይታያል። ይህ ብቻም አይደለም፤ ከዲጂታል እውቀት ጋር በተያያዘም ውስንነቶች አሉ። ይህንን ለመሙላት አስፈላጊ የስልጠና ማዕቀፎች (ፓኬጆች) እየተቀረጹ ሥራዎች ይከናወናሉ።

ዲጂታል አካታችነትን ለማረጋገጥ ስትራቴጂ እየቀረጽን ነው። ስለዚህ ያሉትን ክፍተቶች እየሞላን የአምስት ዓመቱ የስትራቴጂ ዘመን ሲጠናቀቅ ከአምስት ዓመት በፊት የነበርንበት ሁኔታ ላይ እጅጉን ወደፊት የተራመደ ውጤት ይኖራል ብለን እንጠብቃለን።

**ጥያቄ፡- ዘርፉ ሕይወትን እንደሚያቀለው ሁሉ ብዙ አደጋዎች/ ስጋቶች ያሉበት ነው ፤ እነዚህን አደጋዎች ለመቋቋም ምን እየተሠራ ነው ?**

**ዶክተር በለጠ፡-** ሥጋቱ ሁሌም ሊኖር የሚችል ነው። አይደለም እኛ ገና ወደ እዚህ ዘርፍ እየገባን ያለነው ፤ በር እያንኳኳን የምንገኘውና ብዙ ርቀት መጓዝ ያለብን ሀገር ይቅርና ሙሉ ለሙሉ ዲጂታሉን የሚጠቀሙ ሀገራት እንኳን አደጋው ሊያጋጥማቸው ይችላል።

ከዚህ አንጻር በጣም የተጠናከረ የጥበቃ ሥራ፤ ተከታታይነት ያላቸው ፍተሻዎች ይደረጋሉ፤ የተሻለ ቴክኖሎጂዎች እየበለጸጉ የሥራ ሂደቶችን የሚያግዙበት ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ በአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ እናሳካቻዋለን ብለን...

ከ11ኛው ገጽ የዞረ



ሥጋቶች እንደ ሀገር ሁልጊዜ ይኖራሉ፤ ለዚህም ተብሎ የተቋቋመ ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም አለ። እኛም በተሰጠን ኃላፊነት ልክ እንሠራለን። የጥበቃ ሥራውም አንዱ ኃላፊነታችን ነውና እርሱንም ጨምረን እንሠራለን። ወደ ቴክኖሎጂው እየገባን እንደመሆናችን መጠን የሚጠበቅ ተግዳሮት ይኖራል።

አዳዲስ ባህል ሲገነባ ፈተና (resistance) እንደሚኖር ሁሉ፤ ያሉ ክፍተቶችን የሚጠቀም የማስተካከያ ተግባራት ይኖራሉ። እነሱን በቀጣይነት ወይም በወጥነት እየተከታተሉ የእርምት ርምጃ እየወሰዱ፤ ቴክኖሎጂው የተሻለ የሚቋቋም እንዲሆን ሥራ እየተሠራ ነው።

**ጥያቄ፡- እንደ ማህበረሰብ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ጉዳዮችን የመረዳት የግንዛቤያችን ምን ላይ ነው? ግንዛቤውን ለማሻሻል ምን ዓይነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ትሠራላችሁ ?**

**ዶክተር በለጠ፡-** የግንዛቤ ሥራ በሰፊው መሥራት ይጠበቅብናል። እንዳልኩት ያለነው በቴክኖሎጂ በበለጸገ ሀገር አይደለም። አብዛኛው ማህበረሰባችን በግብርና ላይ ተሰማራ (agrarian) ነው። ለቴክኖሎጂ ያለው ምልከታ ተግዳሮት ይኖራል።

የምናለማቸው የዲጂታል ሥርዓቶች በትልልቆቹ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ሳይቀር ችግር ያጋጥማቸዋል (resistance) በዚህ የተነሳም የለሙ ሥርዓቶች ወደ ሥራ ወዲያውኑ የማይገቡበት ሁኔታ አለ። እንደ ሀገር ደግሞ ስንወስደው አዲስ ነገርን ቶሎ ያለመቀበልና ያለመላመድ ባህል (retention culture) አለ።

በታሪክ እንደምናውቀው በፊትም የቀደሙ መሪዎች ቴክኖሎጂን ሲያስተዋውቁ ማህበረሰቡ እንደ ማህበረሰብ ቴክኖሎጂዎችን ለመላመድ እና ለመቀበል ጊዜ የሚወስድበት ሁኔታ ነበር። አሁንም እንደዚሁ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በገጠርና በከተማ ያለው ልዩነት ቀላል አይደለም። ከተሞች እየቀደሙ እየሄዱ ነው፤ ወደ ባህሉ ውስጥ እየገቡ ነው፤ እራሳቸውን ከዓለሙ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ለማስኬድ ጥረቶች አሉ።

ከተሞች እየቀደሙ እየሄዱ ነው። ገጠሩ ደግሞ ገና ያልተነካ ነው። ቴክኖሎጂውን በገጠሩ ተደራሽ ለማድረግ ብዙ ሥራ እየተሠራ እና ጥሩ ውጤትም እየተመዘገበ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን በገጠርና በከተማ ያለው ልዩነትና በዚህ ምክንያት እየተፈጠረ ያለው ተግዳሮት ሰፊ ነው። ይህንን ችግር ለመፍታትና ለማሻሻል የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት ብቻ አይደለም።

ስለ ቴክኖሎጂ፣ ዲጂታላይዜሽን ስናወራ ሁሉንም ይመለከታል። ሚኒስቴሩ እንደ መንገድ ጠራጊ (polish) እቅዱን ያዘጋጃል። ፖሊሲዎች እንዲቀረጹ ያደርጋል። ያንን መሬት ማውረድና ፖሊሲዎቹ በጠቆሙት ልክ ሥራ ላይ ማዋል የሁሉንም ጥረት የሚጠይቅ ነው።

የሚመለከታቸው ሁሉም የመንግሥት ተቋማት እንዲሁም የግል ዘርፉ በጋራ በምንሠራው ሥራ ነው ቴክኖሎጂን ለማወቅና ለመጠቀም ከፍተኛ ጉጉት ያለው (inspired) ማህበረሰብ መፍጠር የሚቻለው። ተግዳሮቱ አለ ፤ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ሰፊ ሥራ ይጠብቀናል። ሁላችንም ተረባርበን ውጤታማ ማድረግ አለብን።

**ጥያቄ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት ከሩሲያ መንግሥት ጋር የኒውክሌር ኃይልን ለሰላም ጥቅም ለማዋል የሚያስችል ስምምነት ተፈራርሟል። ይህ ስምምነት ከምን ደረሰ?**

**ዶክተር በለጠ፡-** እዚህም ላይ ብዥታው መጥራት አለበት። ኒውክሌር ሲባል የብዙ ሰው አይምሮ ላይ የሚመጣው የኒውክሌር የጦር መሳሪያ ነው። እንደዚያ አይደለም። ኢትዮጵያ ለመገንባት ስምምነት ላይ የደረሰችውና እቅዷም ኒውክሌርን ለሰላማዊ አላማና ለልማት ለማዋል ነው።

በዓለም ላይ በስፋት እየዋለ ያለውም ለዚሁ ነው። ኒውክሌር በሕክምና፣ በእርሻው በኢንዱስትሪው አለ። በብዙ ዘርፎች አለ። የጨረራ ሕክምና አለ። በራዲየሽን ቴክኖሎጂ አለ። እነዚህ ሁሉ በኒውክሌር ፓኬጅ ውስጥ ያሉ ናቸው።

ስለዚህ እኛ ለኃይል እና ለተለያዩ ሰላማዊ ተግባራት የሚውል የኒውክሌር ፓወር ግንባታ ከሩሲያ ጋር ተፈራርመናል። ከሩሲያ የኒውክሌር ዋና ተቋም/ ሮሳቶ ጋር ባለፈው ሐምሌ በቅዱስ ፒተርስፐርግ ከተማ የሮድ ማፕ ስምምነት አድርገናል። የኃይል አማራጭን ማስፋት ስለሚያስፈልገን ።

ኢነርጂ ከውሃ ፣ ከንፋስ ፣ ከጂኦተርማል ኢነርጂን ማልማት ያስፈልጋል። ልክ እንደነዚህም ኒውክሌር የሚሠጠውን የኢኮኖሚ ትሩፋትም መጠቀም ያስፈልጋል። ስለዚህ ከኒውክሌር ኃይል እንድናገኝ የኃይል አማራጮቻችንን ምንጮች በማስፋት በማቀድ ይህን ፋሲሊቲ ለመገንባት በማቀድ በአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥ ተካቷል።

በአሁኑ ወቅትም የአዋጭነት ጥናት እንዲጠና ለማድረግ የግዢ ፈቃድ የሚሠጥ አካል ፈቃድ እንዲሰጠን ሥራዎች እየሠራን ነው። እዚህ ላይ ነው ያለው። የአዋጭነት ጥናቱ ተጠንቶ በዓመታት ይህን ገንብተን እውን በማድረግ ሀገራችን ከዚህ ዘርፍ ማግኘት ያለባትን እድል እንድታገኝ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በሰው ሀብት ልማት ረገድ ሥራዎች እየሠራን ነው። አምስት ተማሪዎች ወደ ቻይና ሀገር ልከን በሁለተኛና በሶስተኛ ዲግሪ በኒውክሌር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ላይ ናቸው። ሩሲያም፣ ጣሊያንም እንደዚሁ ተማሪዎቹ አሉን።

ኒውክሌር ከተነሳ አይቀር ከዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጋር በቅርበት እንሠራለን። እነሱም የጨረር ሕክምና “የራዲየሽን ትሪትመንት” ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር በተለይ ዩኒቨርሲቲዎቻችንና ሆስፒታሎች ከዚህ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ባደረግነው ሥራ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች ተመርጠው፤ በአሁኑ ሰዓት በጥቁር አንበሳ ዩኒቨርሲቲ የካንሰር ትሪትመንት መስጠት የሚያስችል መሳሪያ ተተክሎ ሥራ ላይ ነው።

በቀጣይም ጅማ ፣ ጎንደር፣ ሀዋሳ ፣ አለማያ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች የካንሰር ትሪትመንት ፣ የራዲየሽን ትሪትመንት ማዕከል እንዲገነባ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ይህንንም የሚደግፈው የዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ነው። ይህም በኒውክሌር ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ ነው። ኒውክሌር ለሰላማዊ አላማ ይውላል ስንል ከጤናም አንፃር የሚታይ ስለሆነ ይህንን አጠናክረን የምንሄድበት ይሆናል ማለት ነው።

ከተሞች እየቀደሙ እየሄዱ ነው። ገጠሩ ደግሞ ገና ያልተነካ ነው። ቴክኖሎጂውን በገጠሩ ተደራሽ ለማድረግ ብዙ ሥራ እየተሠራ እና ጥሩ ውጤትም እየተመዘገበ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን በገጠርና በከተማ ያለው ልዩነትና በዚህ ምክንያት እየተፈጠረ ያለው ተግዳሮት ሰፊ ነው

**ጥያቄ፡- የስድስት ወር የሥራ አፈፃፀማችሁ ምን ይመስላል?**

**ዶክተር በለጠ፡-** እንደ አጋጣሚ ትላንትም ይሄንን በማኔጅመንት ገምግመናል። በመጀመሪያው ሩብ የእቅድ አፈጻጸም ጥሩ ውጤቶች ነበሩ። ቅድም ስገልጸው የነበረው በኛ ሆነ በተጠሪ ተቋማት በስድስት ወር አፈፃፀማችን ላይ የታዩ ናቸው። ጥሩ ሥራዎች አሉ ፤ በመሃል የገጠሙን ተግዳሮቶች አሉ፤ እነዚህን በአግባቡ ገምግማናል። በቀጣይ ስድስት ወር የግምገማ ውጤቶቻችንን ታሳቢ ባደረገ መንገድ ማሻሻያዎችን አድርገን የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችል አቅጣጫዎች አስቀምጠናል። በዚህ ላይ ነው ያለነው፤ ጥሩ ነው።

**ጥያቄ፡- ለሰጡን ጊዜ እጅግ በጣም እናመሰግናለን።**

**ዶክተር በለጠ፡-** እኔም እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ የሚታተም

# የሕጻናት፣ የእናቶችና የአፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት

**ኢያሱ መሰለ**

እንደምን ሰነበታችሁ ውድ የአምዳችን አንባቢዎች! የጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ በሚያቀርበው በዚህ ትምህርታዊ ዓምድ ሕብረተሰቡ ከጤና ጋር ተያይዞ ግንዛቤ መጨበጥ ይኖርበታል ባላቸው ወቅታዊና ትኩረት በሚያስፈልጋቸው የጤና ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ እየሰጠ ይገኛል። ባለፉት ሁለት ወራት ብቻ ባቀረባቸው ተከታታይ ጽሑፎችም ስለ ማሕጸን በር ካንሰር፣ ስለ ተዛማጅ በሽታዎች ቁጥጥር፣ ስለ ሥጋ ደዌ በሽታና ቅድመ ህክምናው አስፈላጊ የተባሉ መረጃዎችን አድርሷል።

በዛሬው ዝግጅቱም ስለ ሕጻናት እናቶችና አፍላ ወጣቶች የጤና ሁኔታ እያከናወናቸው ስላሉ ተግባራት ተከታዩን መረጃ አቅርቦልናል። መረጃ በመስጠት የተባበሩን እንግዳችን ዶክተር መሰረት ዘላለም ሲሆኑ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ሚኒስቴር የሕጻናት፣ የእናቶችና የአፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ናቸው።

እንደ ዶክተር መሰረት ገለጻ የህጻናት፣ የእናቶችና የአፍላ ወጣቶች ጤና አገልግሎት ዘርፍ በሥሩ አራት ዴስኮች አሉት ከነዚህ ውስጥ የሥነ ተዋልዶጤና፣ የቤተሰብ እቅድ፣ የወጣቶችና የአፍላ ወጣቶች ጤና አንዱ ነው። የሥነ-ተዋልዶ ጤና የቤተሰብ እቅድን እንዲሁም ከእናቶችና ሕጻናት ጋር ይያያዛል። በዋናነት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ጥራቱን በጠበቀ መንገድ ፍታዊ ተደራሽነቱን በማረጋገጥ የእናቶችና የጨቅላ ሕጻናትን ሞት መቀነስ የሚያስችል አዋጭ የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት እንደሆነ ዶክተር መሰረት ተናግረዋል።

የወጣቶችና አፍላ ወጣቶች ጤናንም ሁለንተናዊ በሆነ የጤና አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ አንዱ የጤና ሚኒስቴር ቁልፍ አጀንዳ ነው። ወጣቶችና



**ዶክተር መሰረት ዘላለም**

አፍላ ወጣቶች እንደ ህጻናት ፣ እናቶችና አዋቂዎች አይነት የጤና አገልግሎት ላይፈልጉ ስለሚችሉ እነርሱ በሚያስፈልጋቸው መንገድ የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል። ከአገልግሎት ባሻገርም በመረጃ ተደራሽ የማድረግ ሥራ ይሠራል። ለምሳሌ ከሱሰኝነት ፣ ከአደጋ ፣ ከሥነ ምግብ፣ ከስነ ተዋልዶ ፣ ኤች.አይ.ቪን ጨምሮ ተላላፊ እና ተላለፊ ካልሆኑ በሽታዎች ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመከላከል እንደሚሠራ ተናግረዋል። ሁሉን አቀፍ የአፍላ ወጣቶችና የወጣቶች ጤና አገልግሎትን በመረጃም ይሁን በአገልግሎት ተደራሽ የማድረጉ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ዶክተር መሰረት ገልጸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ የስምምነት ሰነድ ከተፈራረመችባቸው ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የእናቶች የጤና ጉዳይ አንዱ ነው። በተለይም የዘላቂ ልማት ግቦች ሲታሰቡ የእናቶችን ሞት መቀነስ ቁልፍ የሆነ ሀገራዊ አጀንዳ ነው ይላሉ ዶክተር መሰረት። በመሆኑም በቅድመ ወሊድ፣ በወሊድ ጊዜና በድህረ ወሊድ ተደራሽ የሚደረጉ መረጃዎችና አገልግሎቶች መኖራቸውን ያስረዳሉ። አብዛኛውን የሀገራችን ሕዝብ በገጠር የሚኖር እንደመሆኑ በተለይም በጤና ኤክስቴንሽን መርሃ-ግብር በኩል አገልግሎቱ ተደራሽ እየተደረገ እንደሚገኝ ይገልጻሉ።

እናቶች ከመውለዳቸው በፊት ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው የሶስት ዓመትና ከዚያ በታች ልጅ ካላቸውም ልጃቸውን ይዘው በአቅራቢያቸው ባለ ጤና ጣቢያ ቆይተው ክትትልና ድጋፍ ተደርጎላቸው፤ ምግባቸው ተሟልቶላቸው ጤናቸው ተጠብቀው ልጅ ወልደው እንዲሄዱ ይደረጋል። እናቶች ከጤና ኬላ ተነስተው ፣ ጤና ጣቢያ እንዲሁም ሆስፒታል ድረስ በሚያደርጉት የጤና ክትትል የግንኙነት መስመሩ የተመቻቸ እንዲሆን ተሠርቷል። በሙያው የተሻሉ የጤና ባለሙያዎች በአቅራቢያቸው በሚገኝ የጤና ተቋማት ተገኝተው ድጋፍ የሚያደርጉበት የአጥቢያ ዙሪያ ሜንተርሺፕ አሠራርም ተፈጥሯል።

ሌላው የጨቅላ ህጻናት እና የህጻናት ጤና ጉዳይ ነው። ይህም በማህበረሰብ የጤና አገልግሎት ፕሮግራም የሚሰጥ ነው። ከአመጋገብ ፣ ከክትባት ፣ ከንጽህና አጠባበቅ አንጻር ስለጨቅላ ሕጻናትና ስለ ሕጻናት ጤና ቤተሰብ፣ ወላጆች እና አሳዳጊዎች በቂ እውቀት እንዲኖራቸው በጤና ኬላ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ አሀድ የጤና አገልግሎት ወይም በማህበረሰብ አቀፍ የጨቅላ ሕጻናትና ሕጻናት ጤና አገልግሎት አማካኝነት ይከናወናል። ይህን አስመልክቶ በተሠሩ ሥራዎችም ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን ዶክተር መሰረት ተናግረዋል።

የጽኑ ጨቅላ ሕጻናት ህክምና ማዕከላትን ከማስፋፋት አንጻርም ለሰማኒያ ሆስፒታሎች 24 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የፈጀ የሁለተኛ ደረጃ እና የሶስተኛ ደረጃ ጽኑ የጨቅላ ሕጻናት ህክምና መስጫ ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ መቻሉን እና ለሙያተኞችም ስልጠና መሰጠቱን ገልጸዋል። ይህም ጨቅላ ሕጻናትን ለማዳን በሚደረገው ሀገራዊ ርብርብ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል ብለዋል።

በዚሁ በጨቅላ ህጻናት እና በሕጻናት ፕሮግራም ስር ትኩረት የተሰጠው ሌላው ጉዳይ ቀዳማይ የልጅነት እድገትና መዳበር (Early Childhood Development) ነው። በዚሁ መሰረት ሶስት ሴክተሮች ማለትም ጤና ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የተፈራረሙትን የፖሊሲ ማዕቀፎች መሰረት በማድረግ ከ2012 ዓ.ም ጀምሮ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኝ ገልጸዋል። ሕጻናት በእድገት ሂደታቸው በሥነ-ምግብ፣ በሥነ-አዕምሮ በሥነ ልቦና የሚስፈልጓቸውን ነገሮች አግኝተው እንዲያድጉና በብስለት የዳበሩ እንዲሆኑ ያስችላል። ይህም ሀገርን የሚያስቀጥል እና ራዕይዋን እውን የሚያደርግ ጤናማ ትውልድ ከማፍራት አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነ ተናግረዋል ።

በአራተኛ ደረጃ የሚነሳው የክትባት ፕሮግራም ነው። ክትባት እንደ ሀገር ከተጀመረ 43 ዓመታት ሆኖታል። ዛሬ በሀገራችን ኮሮናን ጨምሮ 13 የሚደርሱ ክትባቶች እንደሚሰጡ ዶክተር መሰረት ጠቅሰዋል ። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ብዙ ህጻናትን፣ ጨቅላ ህጻናትን እናቶችን፣ በአጠቃላይ ሰዎችን በክትባት ልንከላከላቸው ከምንችላቸው የአካል ጉድለት፣ ሞትና ሥቃይ መታደግ ተችሏል ይላሉ። እንደዋና ማሳያነትም ልጆችን ከልጅነት ልምሻ ፣ ከአካል ጉዳት፣ ከኩፍኝ ፣ ከሳንባ ምች ፣ ከቴታነስ፣ ከማሕጸን ጫፍ ካንሰር፣ ከኮሮና መከላከል የሚያስችሉ ክትባቶች ተሰጥተዋል። በቀጣይም በተለያዩ ምክንያቶች ክትባት ሳያገኙ የቀሩ ህጻናትን በዘመቻና በመደበኛ የክትባት ፕሮግራሞች ተደራሽ ለማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ዶክተር መሰረት ተናግረዋል።

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORA

ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን
ለ2016 የጥምቀት በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን በ10/90፣ በ20/80 እና 40/60 የቤት ልማት ፕሮግራሞች አማካኝነት ከ317 ሺ በላይ ቤቶችን በማስተላለፍ 1.6 ሚሊዮን የህብረተሰብ ክፍሎችን የቤት ባለቤት በማድረግ እንዲሁም ለበርካታ ዜጎች በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል መፍጠር ያስቻለ ስኬታማ ፕሮግራም ከመሆኑም በላይ በክረምትና በጋ የአቅመ ደካማ ቤቶችን በመገንባትም በማስገንባትም ማህበራዊ ድርሻውን እየተወጣ ያለ ተቋም ነው፡፡ በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም በተለያዩ ሳይቶች የተገነቡት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ለህብረተሰቡ የመኖሪያ ቤት ጥያቄ ተግባራዊ ምላሽ ከመስጠት በተጨማሪ የከተማችንንም ገፅታ በመቀየር ለስራ እና ለኑሮ ምቹ የሆነች ዘመናዊ ከተማ በመፍጠር የጎላ አስተዋፅዖ ማበርከቱ ይታወቃል፡፡

በቀጣይም የተለያዩ አማራጭ የቤቶች ልማት ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ህብረተሰቡ ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆንበት መንገድ የተመቻቸ መሆኑን ስንገልፅ በታላቅ ደስታና እስከዛሬ የተገኙ ስኬቶችን አጠናክረን ለማስቀጠልም ቃል በመግባት ጭምር ነው፡፡

**የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን**
**መልካም በዓል**

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ራስ ወዳድነት እየነገሰ ሰብአዊት እየኮሰሰ ይሆን?

**እዮሩስ ተስፋዬ**

አንድ በእድሜያቸው ጠና ያሉ አባት ታክሲ ለመያዝ ቢሯሯጡም ሊሳካላቸው አልቻለም። ወጣቱ እና ጉልበት አለኝ የሚለው ሁሉ እኚህን አባት ገፍትሮም ይሁን ያደገረውን አድርጎ ወደ ታክሲው ውስጥ ለመግባት ትንቅንቅ ላይ ነው። ጉልበተኞቹ ሁሉ ጥሏቸው ይሄዳሉ።ይህንን ሲያደርጉ ያለ አንዳች መሸማቀቅ እና ሀፍረት ነው። እኔም ላለመጋፋት ፈርቼ ከዳር ቆሜ መገፉን በመጎባ እየተመለከትኩ ነበር ያሉት ሲሄዱ ይቀላል ብዬ ተስፋ ባደርግም ቅዳሜ ስለነበር ይሁን በሌላ ምክንያት የሰው ብዛት እየጨመረ እንጂ እየቀነሰ አልሄደም። በዚሁ ሁኔታ ውስጥ ሆኘ እኚህ አባት ድንገት መሬት ላይ ወድቀው ተዘረሩ። ግማሹ ውሃ ለማምጣት፤ከወደቁበት አስፋልት ዳር ወደ አንድ ጥግ ለመውሰድ እና ሌሎችን ርዳታዎች ለማድረግ ይጣጣራል።

ምናልባት እኮ ቀድመው ተሳፍረው ቢሆን ላይወድቁ ይችሉ ነበር? አላውቅም! ግን ቀድሞ መረዳት ይቀል ነበር። ፀሀይ በጣም መቷቸው ይሆን የወደቁት? የስኳር በሽታ ነው ወይስ ግፊት?ብቻ ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ እኚህ አባት ነቁ። መልከመልካሙ አባት ልብሳቸው እንዳልነበር ሆኖ ቆሽሿል። የወደቁበት አቧራ ለፊታቸውም ደርሷል። ከንፈራቸው ትንሽ ደም ይታይበት ነበር። በኋላም አንድ ወጣት ልጅ ወዴት እንደሚሄዱ ጠይቆቋቸው ተጋፍቶ እና የታክሲ ከፍሎላቸው ከዳግም እንግልት ገላገላቸው።

አስከፊ የሚባሉ ነገሮች ሁሌም ከመሆናቸው በፊት መደረግ ያለበት ቢደረግ ችግሮችን መቀነስ የሚቻል ይመስለኛል።ብዙ ጊዜ ግን ከሆነ በኋላ ነው ትብብሩም፣ እርዳታውም እና ከንፈር መምጠጡ የሚስተዋለው። በየቦታው እኚህን መሰል በእድሜ የገፉ አረጋውያን ተመሳሳይ ችግር ያጋጥማቸዋል። በበዓላት ወቅት እና የትራንስፖርት እጥረት በሚስተዋልበት ጊዜ ምነው ከቤታቸው ባልወጡም ያስብላል።

በየቦታው ለታክሲ ተብለው የተዘጋጁ ሰልፎች ምንም እንኳን አሰልቺ ቢሆኑም አቅማቸው ደካማ ለሆኑ ሰዎች፣ለአካል ጉዳተኞች ፣በጀርባቸው ልጅ ለታቀፉ እናቶች እና ለነብሰ ጡር ሴቶች በሚገባ እፎይታን የሚሰጥ ነው። የሚገርመው ግን እኚህን ሰዎች ቀድሞ ለመግባት ሰልፍ የሚጥስ ግዴለሹ ሰው ቁጥሩ ቀላል እንዳልሆነ ያለ አንዳች ጥርጣሬ መግለጽ ይቻላል።

ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጣልቃ መግባትም ሆነ እኔን ብቻ አስቀድሙኝ የሚሉት ሰዎች ነገር ሁሌም እንዳስገረመኝ ነው። ድንገት ከኋላ መጥተው እነርሱ ብቻ እንዲገለገሉ የሚያጣድፉ ሰዎች ካለመሰልጠን እና ካለማስተዋል የመነጨ ችግር ካልሆነ ምን ሊባል ይችላል? ደግሞ ይቅርታ እንኳን አይጠይቁም።

አሁን አሁን ሁላችንም የባለ ብዙ ጉዳዮች ባለቤት ሆነናል።ስለራሳችን እንጂ ስለሌሎች እየገደደን አይመስልም። ምንም እንኳን አስቸኳይ ጉዳይ ያለው ሰው ላይ ፍርድ ለመስጠት ቢያስቸግርም ካፌ እና መሰል ቦታዎች ላይ ቁጭ ብሎ ጊዜውን ለማሳለፍ ከአቅመ ደካሞች ጋር የሚጋፋውን ስንመለከት ‹‹ትዝብት ነው ትርፉ›› ብሎ ከማለፍ ውጪ ምን ማለት ይቻለናል?

ዛሬ ላይ ብዙዎቻችን ልባችን ደንድኗል መሰለኝ። ሰው ሲደባደብ ጉዳት እንዳይደርስ ከመገላገል ይልቅ ገላጋይ ላይ ምን ሊመጣ እንደሚችል ቀድሞ በመረዳት ጎመን በጤና ብለን ምርጫችን ሽሽት ሲሆን ይታያል። መንገድ ላይ ወድቆ የተለመከትነው ሰው ቀርቦ ከመርዳት ይልቅ ፍርሃታችን ከሰብአዊነታችን ልቆ ዝምታን አስመርጦናል።አንድ ሰው እርዳታችንን ፈልጎ ሲጠይቅ ‹‹ከነገሩ ጾም እንደሩ።››ብለን ያለንን ከማዋጣት እንሸሻለን።ለመርዳትም ቅድመ ሁኔታዎችን እናስቀምጣለን።

በየቦታው የሚሠሩ እና የሚቆፋፈሩት መንገዶች አይደለም ለአካል ጉዳተኛው ለጉዳት አልባው ፈታኝ ናቸው። ልብ ብለን ካየን እንዲህ አይነቱን ችግር ዓይነ ስውራን እና ሌሎችንም በየዕለቱ ሲፈትናቸው እንመለከታለን። እነርሱ አስፋልት ለመሻገር ይሁን በሌላ ነገር ሲቸገሩ እያየን ዝምታን እንመርጣለን።


አንዳንድ ልምምዶች መጥፎ ናቸው። ሲባል ከሰማነው እና ሲሆን ከተመለከትነው ነገር በመነሳት መርዳት ያለብንን ሰዎች ሳንረዳ እንቀራለን። ከመርዳት ይልቅ ቢያጭበረብሩንስ ብለን እንድናስብ ብዙ ድርጊቶች ተፈጥረው ይሆናል። እንደ አሁኑ የራይድ ትራንስፖርት አገልግሎት ሳይስፋፋ በፊት የቤት መኪናም ይሁን ኮድ ሦስት ተሽከርካሪዎች ሰዎችን በተለይም አቅማቸው ደካማ የሆኑትን ይሸኙ ነበር። ዛሬ ግን የሥራ መኪና ሆነው ብር የሚያገኙበት ሥርዓት ተዘጋጅቶላቸው እንዲህ ዓይነቱን በጎ ሥራ ወደ ጎን አድርጎታል ማለት ይቻላል። ደግሞም አይፈረድባቸውም።አንዳንድ ከሠማው እና ከደረሰበት ተነስቶ በእድሜ የገፉትንም ይሁን ሌሎች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሰው ጭኜ ሌላ ችግር ቢደርስብኝስ ብሎ በመፍራት ራሱን ከበጎ ሥራ እንዲርቅ አድርጎታል።

ዛሬ ላይ ከሰብአዊነት የፍርሃት፣ የግዴለሽነት፣ የራስ ወዳድነት ሚዛን ከፍ ብሎ ይታያል።ከዚህ በፊት በከተማም ይሁን በገጠር የመሸበት ‹‹የእግዜር እንግዳ›› ውጭ አድሮ ክፉ እንዳይገጥመው ብሎ በማሰብ የማያውቀው ሰው ያለውን አብልቶ አጠጥቶ እና ተንከባክቦ ይሸኛል።በከተማ ላይ እንዲህ አይነቱ ነገር በስፋት አይታይም። ምክንያቱ ብዙ ሊሆን ይችላል። ባስጠጋው አንዳች ጉዳት ሊደርስብኝ ይችላል ብሎ በማሰብ እንዲህ አይነቱ ነገር አይደለም ማድረግ፤ ማሰብ እንኳን አይፈልግም።አንዳንዱ ደግሞ እንኳን ለሌላው ሊተርፍ ለራሱም መሆን አይቻለውም።ብቻ በእነዚህ እና በሌሎች ምክንያቶች ይመስለኛል አንዳንድ ሰዎች የከተሜ ሰው በሩን ዘግቶ ነው የሚበላ ብለው የሚያሙት።

የስነ ልቦና ባለሙያዎች ደጋግመው እንደሚሉት አንድ ሰው ራሱን መውደድ እንዳለበት ሲናገሩ ይደመጣል።ለምን ከተባለም? እርሱ ሌላውን ሊወድ የሚችለው ራሱን ሲወድ እንደሆነ ያስረዳሉ። ከሃሳቡ ጋር ተቃርኖ የለኝም። ግን ከመጠን በላይ የበዛ ራስን ወዳድነት፣ግዴለሽነት እና ለራስ የሚሰጥ የተጋነነ ግምት ሌላውን በመጉዳት እና በማኮሰስ ከሆነ ፍጹም ስህተት ነው።

ሰብአዊነት መርጦ መርዳት አይደለም። ማንም ከማን ሳይወግኑ መርዳት ማገዝ እና ማከፈልን ይጠይቃል። ያለምንም ክፍያ ሰውን የሚረዱ አቅመ ደካሞችን የሚደግፉትን ሰዎች በመመልከት ቢያንስ እንኳን የነሱን ያህል ማድረግ ባንችል እንኳን በጥቂቱ ተባባሪ እንሁን።

# ዓለም አቀፍ



## ሰሜን ኮሪያ 'የውሃ ውስጥ የኒውክሌር ጦር መሣሪያ' ሙከራ ማካሄዷ ተገለጸ

አሜሪካ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ጃፓን በጋራ ላካሄዱት ወታደራዊ ልምምዶች ምላሽ ለመስጠት በሚል ሰሜን ኮሪያ “የውሃ ውስጥ የኒውክሌር ጦር መሳሪያ” መሞከሯን የሀገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ዘገቡ። ሰሜን ኮሪያ ‘ሃኤል-5-23’ ስትል የሰየመችው ኒውክሌር መሸከም የሚችሉ የውሃ ውስጥ ድሮኖችን ሙከራ በምስራቃዊ የባሕር ዳርቻዋ አካሂዳለች።ኮሪያ ከዚህ ቀደም ተመሳሳይ ሙከራዎችን አድርጋለች።

ሰሜን ኮሪያ በአካባቢው ላይ “በማንኛውም ጊዜ ሊፈነዳ” ለሚችል ጦርነት ለመዘጋጀት ወታደራዊ አቅሟን እያጠናከረች መሆኑን ደጋግማ አስታውቃለች።መሪዋ ኪም ጆንግ ኡን በዚህ ሳምንት ከደቡብ ኮሪያ ጋር ዳግም የመዋሃድ ህልም ማብቃቱን ገልጸው፤ ደቡብ ኮሪያንን "ቀንደኛዋ ጠላት" በማለት ፈርጀዋት ነበር።የውሃ ውስጥን ጨምሮ የሀገራቸው ወታደራዊ እና የኒውክሌር አቅሞች በርካታ እድገቶችን ማስመዝገባቸውንም ጠቁመዋል።

ፒዮንግያንግ ባለፈው መስከረም የኒውክሌር ጦር መሳሪያ ማስወንጨፍ የሚችል የመጀመሪያው ሰርጓጅ መርከብ ነው ያለችውን መሣሪያ ይፋ አድርጋ ነበር። ከ2023 ጀምሮም ሃኤል የሚል መጠሪያ የተሰጣቸውን እና ኒውክሌር የታጠቁት የውሃ ውስጥ የሰው አልባ ድሮኖችን መሞከሯን ተናግራለች።

ስለእነዚህ መሳሪያዎች ወይም ውጤታማነታቸው ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም። ከሰሜን ኮሪያ የኒውክሌር ባሊስቲክ ሚሳኤሎች አንጻር ሚናቸው አነስተኛ መሆኑን ተንታኞች ይገልጻሉ።ሰሜን ኮሪያ ባለፉት ወራት በርካታ የረዥም ርቀት ሚሳኤሎችን ሞክራለች።ባለፈው የፈረንጆች ዓመት የስለላ ሳተላይት ወደ ህዋ ላይ እንዳመጠቀች እና በዚህ ዓመትም ተጨማሪ እንደምታመጥቅ ይፋ አድርጋለች።

የመከላከያ ሚኒስቴሩ የውሃ ውስጥ ድሮን መሞከሯን ገልጾ የሙከራው ዓላማ “የአሜሪካ እና አጋሮቿን የባሕር ኃይሎች ጠብ የሚያጭር ወታደራዊ ልምምድን ለመከላከል ያለመ” ስለማለቱ ኬሲኤንኤ ዘግቧል።ዋሽንግተን፣ ሴኡል እና ቶኪዮ አውሮፕላን ተሸካሚ መርከቦችን ጨምር በማሰለፍ በኮሪያ ባሕር ገብ አካባቢ የሦስት ቀናት የጋራ ልምምድ አድርገው እንደነበር ጠቅሶ ቢቢሲ ዘግቧል።

## የታይላንድን ዘውዳዊ ሥርዓት አንቋሿል የተባለው የ50 ዓመት እስር ተፈረደበት



የታይላንድ ፍርድ ቤት የሀገሪቱን ዘውዳዊ ሥርዓት ስም አጠልሽቷል በተባለው ግለሰብ ላይ የ50 ዓመት እስራት ፈርዶበታል። ውሳኔው በዘውዳዊው ሕግ ከፍተኛው ቅጣት ነው ተብሏል። የሠላሳ ዓመቱ ሞንግኮል ቲራኮት ከሦስት ዓመታት በፊት በፌስቡክ ላይ ባሰራጫቸው ጽሑፎች መጀመሪያ ላይ የ28 ዓመት እስራት ተፈርዶበት ነበር።

የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሐሙስ ዕለት በዋለው ችሎት ተጨማሪ 22 ዓመታትን ጨምሮበታል። በዘውዳዊው ሕግ መሠረት ማንኛውም ስለሀገሪቱ ንጉሣዊ ሥርዓት የሚሰጥ አሉታዊ አስተያየት በወንጀል ያስጠይቃል።ከ10 ዓመታት በኋላ ባለፈው ዓመት በታይላንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቪል መንግሥት በምርጫ ቢያሸንፍም ከፍተኛ ትችት የሚቀርብበት ሕግ አሁንም በሥራ ላይ ይገኛል።

ሐሙስ ዕለት በዋለው ችሎት ተከሳሹ ለሂደቱ ባሳየው ተባባሪነት ምክንያት ቅጣት በአንድ ሦስተኛ መቀነሳቸውን ዳኛው ገልጸዋል። መኖሪያውን በቺያንግ ራይ ግዛት በማድረግ በበይነ መረብ ልብስ በመሸጥ የሚተዳደረው ቲራኮት ከባድ ቅጣት ለምን እንደተላለፈበት በዝርዝር አልተገለጸም።

ዳኛው በፌስቡክ ላይ የተሰጡ በርካታ አስተያየቶችን ጠቅሰዋል። የታይላንድ ፍርድ ቤቶች በግለሰቦች ለሚሰጡ እያንዳንዳቸው አሉታዊ አስተያየቶች ተጨማሪ ቅጣት ያስተላልፋሉ። እአአ በ2019 ንጉሥ ቫጂራሎንግኮርን ወደ ዙፋኑ እንደመጡ ይህ ሕግ ለአጭር ጊዜ ታግዶ እንደነበር ይታወሳል።

ከሦስት ዓመታት በፊት ታይቶ የማይታውቅ የተባለለትን እና በተማሪዎች የተመራ ሕዝባዊ ተቃውሞን ተከትሎ ሕጉ እንደገና በሰፊው ጥቅም ላይ መዋሉን ቀጥሏል። ተቃውሞው በንጉሣዊው ሥርዓት ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ጥሪ ያቀረበ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለንጉሣዊው ሥርዓት ሕዝባዊ ውይይት የጠራው የማኅበረሰብ አንቂው እና የሕግ ባለሙያው አርኖን ናምፓ የእስር ጊዜም በአራት ዓመት ከፍ ተደርጓል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ!

በዛሬው እለት በመላ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የጥምቀት በዓል በልዩ ልዩ ዝግጅቶች በደማቅ ሥነሥርዓት ይከበራል። በዋዜማውም የጥምቀት ከተራ በዓል የየአድባራቱ ታቦታት አዳራቸውን ባደረጉባቸው ጥምቀተ ባህሮች በታላቅ መንፈሳዊ ሥነሥርዓት ተከብሯል።

መላ የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ በሰላም አደረሳችሁ! የጥምቀት በዓል በተለይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንና ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች በልዩ ልዩ ሥነሥርዓቶች ይከበራል።

እየሱስ ክርስቶስ በልደቱ በትህትና በከብቶች በረት እንደ ተወለደ ሁሉ በጥምቀቱም በዮርዳኖስ ወንዝ ተገኝቶ በሰው እጅ የተጠመቀበትና ለሰው ልጆች ሁሉ በድጋሚ ትህትናና ፍቅርን ያስተማረበት እንደመሆኑ፣ የእምነቱ ተከታዮችም ይህን ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ትውፊት በመከተል በትህትና፣ በመልካም ሰብእናና በፍቅር ፈጣሪን በማመስገን በደማቅ ሥነሥርዓት ያከብሩታል።

የጥምቀት በዓል አካል የሆነው ከተራ በመላ ሀገሪቱ በደማቅ ሥነሥርዓት እየተከበረ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ ከተማም በጃንሜዳ እና በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ በርካታ ጥምቀተ ባህሮች እየተከበረ ይገኛል። ልብሰ ተክህኖ የለበሱ የቤተክርስትያኗ አባቶች፣ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ የሰንበት ትምህርት ቤት ወጣቶች ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ዜማዎችን በማሰማት በወረብና በሽብሸባ ለፈጣሪ ምስጋና በማቅረብ የሚያከብሩት ሲሆን፤ የእምነቱ ተከታዮችም በልዩ ልዩ አልባሳት አምረውና ተውበው በየጥምቀተ ባህሩ በመገኘት ይህን ሃይማኖታዊ ሥርዓት በጽሞና በመከታተል፣ አብረውም በማዜም ለፈጠሪ ምስጋና በማቅረብ ያከብሩታል።

የጥምቀት በዓል ከመንፈሳዊ በዓልነቱ ባሻገርም ባህላዊና ማኅበራዊ እንዲሁም ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው። የእምነቱ ተከታዮች መንፈሳዊ ዜማዎችን ብቻ ሳይሆን ልዩ ልዩ ባህላዊ ዜማዎችን በማዜምና በመወዛወዝም ጭምር በዓሉን ይበልጥ አድምቀውት ይውላሉ። ለእዚህም ልዩ ዝግጅት አድርገው ነው የበዓሉን መድረስ ሲጠባበቁ የሚቆዩት። ለእዚህ ታላቅ ቀን የማያውሉት የክት ልብስ፣ የማያወጡት ገንዘብ የላቸውም። «ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ» የሚባለውም ከዚህ በመነጨ ነው።

ባህላዊና ማኅበራዊ ትውፊቶቹ ለሰዎች የእርስ በርስ ትስስር መጠናከር ሚናቸው ከፍተኛ ነው። ባህላዊ ዜማዎች ብቻ ሳይሆኑ ባህላዊ አልባሳትም የበዓሉ ታዳሚዎች መድመቂያ ናቸው። የባህላዊ አልባሳትና ባህላዊ ጨዋታዎች አይነት በስፋት የሚታይበት፣ በዓል እንደመሆኑም ለባህላዊ ትውፊት መጠበቅ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በበዓሉ የሚታደመው የኅብረተሰብ ክፍል በርካታ እንደመሆኑም፣ በዓሉ የእምነቱ ተከታዮች ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያውያን በዓልም ነው ያሰኛል። በዓሉ በድምቀትና በሰላም እንዲከበር በማድረግ በኩል ከእምነቱ ተከታዮች በተጨማሪ የተለያዩ እምነቶች ተከታዮች ታቦታት የሚጓዙባቸውን ጎዳናዎችና የሚያድሩባቸውን ስፍራዎች በአጠቃላይ በዓሉ የሚከበርባቸውን አካባቢዎች በማጽዳት የሚያደርጉት ርብርብ ይህንኑ ያመለክታል።

የጥምቀት በዓል በዓለም አቀፍ ደረጃም በዩኔስኮ ትልቅ ስፍራ የተሰጠው ነው። በድርጅቱ በዓለም የማይደሰስ ቅርስነት የተመዘገበ እንደመሆኑም የዓለም ሕዝብ በዓልም ጭምር ነው።

የጥምቀት በዓል ለምጣኔ ሀብት ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ አንጻር ሲታይም ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። ይህን በዓል ብለው በርካታ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች እና በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በዚህ ወቅት ወደ ሀገሪቱ ይተማሉ። የሀገር ውስጥ ቱሪዝም በከፍተኛ ደረጃ ከሚንቀሳቀስባቸው በዓላትና ወቅቶች መካከልም የጥምቀት በዓል ይጠቀሳል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትህትናና ፍቅር የተገለጸበትና የትህትናና ፍቅር ፋይዳ በሰፊው የሚሰበክበት እንደሁም በርካታ ፋይዳዎች ያሉት ይህ ታላቅ በዓል በድምቀትና በሰላም እንዲከበር ማድረግ ከምንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። በዓሉ በድምቀትና በሰላም እንዲከበር ቤተክርስቲያኗና የእምነቱ ተከታዮች እንዲሁም መንግሥት አስቀድመው ልዩ ዝግጅት አድርገውበታል።

ይህ የእምነቱ ታላቅ ሥነሥርዓት የሚካሄድበት፣ ከሕፃን እስከ አዋቂ መላ ቤተሰብ፣ የውጭ ሀገር ቱሪስቶችና በውጭ ሀገሮች የሚኖሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ መላ ዓለም በአንክሮ የሚከታተለው በዓል በድምቀትና በሰላም እንዲከበር ለማድረግ የእምነቱ ተከታዮች የቤተክርስቲያኗ እና የጸጥታ አካላት ጥረት ብቻውን አይበቃም። እንደተለመደው መላ ኢትዮጵያውያንም ለበዓሉ በሰላምና በድምቀት መከበር የበኩላቸውን ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

ከዚህ በዓል በሰላምና በድምቀት መከበር የሚያተርፉት የእምነቱ ተከታዮች ብቻ አይደሉም፤ መላ ኢትዮጵያውያንና. መንግሥትም ሀገርም ዓለምም ናቸው። ፍቅርና ትህትና በእጅጉ የሚሰበክበት፣ የኢትዮጵያውያን ወንድማማችነትና እህትማማችነት የተጠናከረ መሆኑ የሚመሰከርበት፣ የመንግሥትና ሕዝብ አንድነትና ጥንካሬም የሚታይበት ነው።

ስለሆነም መላ ኢትዮጵያውያን የከተራ በዓል በድምቀት እንዲከበር የበኩላችሁን ሚና እንደተጫወታችሁ ሁሉ የጥምቀት በዓል ተከብሮ እስከሚጠናቀቅ የሚጠበቅባችሁን መወጣታችሁን አጠናክራችሁ ቀጥሉ። በድጋሚ ለመላ የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## "ሀገር የማዳንም ተግባር በዛሬ ድጋፍና ተቃውሞ አይለካም፤ በዛሬ ወሬና አሉባልታ አይገመገምም፤ ጊዜ ይፈልጋል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የጥምቀት በዓልን አስመልክተው ያስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት ሙሉ ቃል**



ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደት እስከ ዕርገት የተጓዘው ጉዞ የአዳምን ውድቀት የተከተለ ነው። አዳም በተጓዘበት የውድቀት መንገድ ተጉዞ አዳምን ከውድቀት አነሣው። ይህ ጉዞ ሁለት ዓላማ ነበረው። አንድም ለሌሎች አርአያ ምሳሌ ለመሆን ነው። አንድም ደግሞ አዳምን በየውድቀቱ ምእራፍ ለማንሣት ነው።

በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀውም ለእነዚህ ሁለት ምክንያቶች ነበር።

ክርስቶስ እስከ ጥምቀቱ ድረስ ባደረገው ጉዞ ሐዋርያት አልነበሩትም። ያም ማለት ከ33 ዓመታት ውስጥ 30ውን ዓመት ሐዋርያት ሳይኖሩት ነው ያሳለፈው ማለት ነው። ቀደም ብለን ያነሣናቸውን ሁለቱን ዓላማዎች ሐዋርያት ከመኖራቸው በፊት ይሠራ ነበር። ሐዋርያት ከመጡ በኋላም ይሠራ ነበር።

እስከ ዕለተ ጥምቀቱ የሠራው ሥራ በይፋ የተደረገ አልነበረም። ከጥምቀቱ በኋላ የሠራቸው ሥራዎች ግን በይፋ፣ በመገለጥ የተሠሩ ሥራዎች ናቸው። የሁለቱ ልዩነት የዓላማና የተግባር አይደለም። በብዙ ሕዝብ በይፋ የመታወቅና ያለመታወቅ ጉዳይ እንጂ።

የጥምቀትን በዓል ስናከብር ከሃይማኖታዊና ባህላዊ ጉዳዮች በተጨማሪ እነዚህን ለሰው ልጆች ጉዞ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች እንድናስብ አደራ እላለሁ። እንደ ሀገር የምንሠራቸው ሥራዎች ሁለት ዓላማ ያላቸው ናቸው። ሀገርን የማዳንና ለሌሎች መንገድ የማሳየት። ኢትዮጵያ በብዙ ስብራቶች ውስጥ ያለፈች ሀገር ናት። ክርስቶስ ለአዳም እንዳዘነለት የሚያዝንላት ትፈልጋለች።

ክርስቶስ ስለ አዳም ሆኖ ሸክሙን እንደተሸከመለት ሸክሟን የሚሸከምላት ትፈልጋለች። ክርስቶስ አዳምን ለማዳን ሲሠራ፣ በአዳም ላይ ተጨማሪ ቁስል ለማምጣትም የሚሠሩ ነበሩ። የበፊቱ ቁስ አልበቃቸው ብሎ። ግን ተሸንፈው ቀርተዋል። ዛሬም ሀገር ለማዳን ስንሠራ በሀገር ላይ ተጨማሪ ቁስል ለማምጣት የሚሠሩ አሉ። ተሸንፈው መቅረታቸው ግን አይቀሬ ነው። ማጥፋት ማዳንን አያሸንፈውምና።

ሀገርን ለማዳን የሚሠሩ ሥራዎችን ለሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ አይገለጡለትም። ክርስቶስ ሲወለድ ሐዋርያት አልነበሩም፤ ሲሰደድ አልነበሩም። ሲጠመቅ አልነበሩም። ያ ማለት ግን ክርስቶስ አዳምን የማዳን ሥራውን አልሠራም ማለት አይደለም። ሰዎች ሁሉ እስኪሰበሰቡ፣ እስኪረዱና እስኪተባበሩ ከጠበቅን ሀገር የማዳን ሥራችንን መሥራት አንችልም። ነገሮች ለሁሉም የሚገለጡበት ጊዜ አለ። አስተርእዮ(መገለጥ) የሚሆንበት ጊዜ አለ። ሥራ ብቻ የሚሠራበትም ጊዜ አለ።

ክርስቶስ ከልደቱ እስከ ጥምቀቱ በተጓዘ ጊዜ የኦሪቱ መሥዋዕት አልቀረም፤ የኦሪቱ የበላይነት አልተወገደም። የቤተ መቅደሱ መጋረጃ አልተቀደደም። ምኩራብ አልተሻረችም፤ በሰማይና በምድር፣ በሰውና በመላእክት፣ በነፍስና በሥጋ መካከል የነበረው ጠላትነት ገና ሙሉ በሙሉ አልተሻረም። የሞት መውጊያ አልተሰበረም። በዚህም የተነሣ አብዛኛው ሰው ከጨለማው ዘመን እየወጣ፣ ከመከራው ዘመን እየተሻገረ፣ ከሞት ቀንበር እያመለጠ መሆኑን ገና አልተገነዘበም። ነገር ግን ቀንበሩ እየተሰበረ፣ ሞትም እየተሻረ፣ አዲስ ሕይወት እየተበሠረ፣ አዲስ መንገድም እየተጀመረ ነበር።

ሀገርን ለማዳን የምንሠራቸው ሥራዎች ብርሃናቸው ቦግ ብሎ ዛሬ ላይበራ ይችላል። ለሁሉም እኩል ላይታዩ ይችላሉ። ካለፈው የችግር ጊዜ እየወጣን መሆኑ፣ ወደ አዲስ ሀገራዊ ሁኔታ እየተሻገርን መሆኑ ለጊዜው ላይታወቅ ይችላል። ከጥምቀት በኋላ ለሁሉ እንደተገለጠው፣ የኢትዮጵያ ትንሣኤና ሕዳሴ ለሁሉም ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል።

ክርስቶስ የአዳምን የስብራት ጎዳና ተከትሎ በየወደቀበት ምእራፍ እንዳነሣው ሁሉ፤ ሀገርን የማዳን ሥራ የሀገርን የስብራት ጎዳና መከተልን ይፈልጋል።

በእያንዳንዱ ምእራፍ ሀገር የወደቀችበትን እየፈለጉ ማንሣትን ይጠይቃል። ፍሊጋውም፣ ጉዞውም ፈታኝ ነው። በዚህ ላይ የሄሮድስ ሰይፍ፣ የፈሪሳውያን ግብዝነት፣ የጻፎች ሤራ፣ የሮማውያን ሥጋት፣ የይሁዳ ክህደት፣ የቶማስ ጥርጣሬ፣ የአይሁድ የወሬ ዘመቻ በየአቅጣጫው አለ። ይሄም ሁሉ ሆኖ ግን መሥዋዕትነት ከፍለን ሀገራችንን እንታደጋታለን። ስብራቷን እንጠግናለን። የጥምቀት በዓል በሁለቱ ምእራፎች መካከል የሚገኝ ምእራፍ ነው።

ለብዙ ሕዝብ ባልተገለጠውና በተገለጠው መካከል የሚገኝ አስደናቂው ነገር ከ33ቱ የአገልግሎት ዓመታት ውስጥ፣ ለሕዝብ ከተገለጠው ይልቅ ያልተገለጠው የአገልግሎት ዘመን መብዛቱ ነው። ሌላው አስደናቂ ነገርም ለሕዝቡ ሁሉ በተገለጠ ጊዜ እንኳን ሁሉም ሕዝብ ተረድቶ በአንድነት አለመቆሙ ነው።

ይሄም የሚነግረን ታላቅ ትምህርት አለ። ትኩረታችን በዓላማችንና በዕቅዳችን ላይ መሆን እንዳለበት። አንዳንድ ነገሮች ወዲያው ግልጽ ይሆናሉ። አንዳንድ ነገሮች ዘግይተው ግልጽ ይሆናሉ። አንዳንድ ነገሮችም ከዘመናት በኋላ ግልጽ ይሆናሉ። በዓለም ላይ የመጡ ለውጦች ሁሉ የተጓዙት እንዲሁ ነው። መጀመሪያ ተቃዋሚዎቻቸው ይበዙ ነበር።

የሻማውም ብርሃን ጥቂት ነበር። ሲውል ሲያድር ግን ጨለማው እየተገፈፈ፣ ብርሃኑ እየተቀጣጠለ ሄዶ፣ ለሁላችንም ደረሰ።

ዛሬ ሁላችንም እንደዋዛ የምንጠቀምበት ስልክ ከመቶ ዓመታት በፊት ወደ ሀገራችን ሲገባ ብዙ ፈተና ነበረው። ተወግዞ ነበር፤ ሰይጣን ነው ተብሎ ነበር። ብዙ ተወርቶበት ነበር። በአጭር እንዲቀጭ ያልተፈነቀለ ድንጋይ አልነበረም። ያ ሁሉ ሲያልፍ ግን ዛሬ በእያንዳንዳችን ቤት ብቻ ሳይሆን በእያንዳንዳችን ኪስ ገብቷል። ሀገር የማዳንም ተግባር እንደዚሁ ነው። ነገሩ በዛሬው ሚዛን አይመዘንም። በዛሬ ድጋፍና ተቃውሞ አይለካም። በዛሬ ወሬና አሉባልታ አይገመገምም። ጊዜ ይፈልጋል።

ዛሬ የጥምቀት በዓል በሀገራችን ከ20ሺ በላይ በሆኑ ቦታዎች፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ወጥቶ ያከብረዋል። ዩኔስኮ በዓለም ቅርስነት መዝግቦታል። ከ2000 ዓመታት በፊት ክርስቶስ ሲጠመቅ ግን በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ ነበሩ። ብዙም የተወራለት፣ ብዙም የተነገረለት አልነበረም።በዙሪያው በነበሩ ከተሞች የሚኖሩ ብዙ ሰዎችም ምን እየተከናወነ እንደሆነ አልተረዱም ነበር። ጥቂቶች ብቻ በዕለቱ የተደረገውን ተአምር አይተው ክርስቶስን ተከትለውታል። ይሄው ነበር ታሪኩ።

የጀመርነው ጉዞ ጥቂት የሚመስል ግን የሚበዛ፤ እዚህ የተወጠነ ግን ረዥም፣ ጥቂቶች የተረዱት፣ ነገ ግን ሕዝብ ሁሉ የሚከተለው፣ ሀገር የሚታደግና ስብራት የሚጠግን ጉዞ ነው። እዚህና እዚያ የጀመርናቸው ውጥኖች አንዱ ዓላማቸው ለሌሎች መንገድ ማሳየት ነው። ስብራት እየጠገንን፣ ሀገር, እየታደግን፣መንገድም እየከፈትን መጓዛችንን እንቀጥላለን። ጅማሬው ታናሽ ቢሆንም፣ ፍጻሜው ታላቅ ስለሚሆን፣ ከጥምቀቱ የተማርነው ይሄንን ነውና።

**መልካም የከተራና የጥምቀት በዓል ይሁን።**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ጥር 10፣ 2016 ዓ.ም**

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፋታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታተሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# ስለ ሕይወት፤ ከሊባኖስ - አዲስ አበባ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

**የሊባኖሱ ልጅ ...**

አካባቢው ለም ነው። ሥፍራው ክረምት ከበጋ ያበቅላል። ገጠር ነውና አራሽ ጎልጓዩ ብዙ ነው። በተንጣለለው መስክ ከብቶች የሚያግዱ፣ ሮጠው የሚቦርቁ ሕፃናት አይጠፉም። ከፍ ያሉቱ ለወላጆች ይታዘዛሉ። እነሱ ሁሌም ውሎ ማምሻቸው ከሌሎች ይለያል። አቅም ጉልበታቸውን አይሰስቱም። ወዛቸውን አበርክተው ምርቃትን ይወስዳሉ።

በሊባኖስ ቀበሌ ይህን መሰሉ ሕይወት ብርቅ አይደለም። ሥፍራው ከደብረ ማርቆስ ከተማ በአጭር ርቀት የሚገኝ ገጠር ነው። በአካባቢው ለመኖር ሲባል መሥራት፣ ጉልበት ከፍሎ ማደር አይሸሹት ግዴታ ነው። ሁሉም በአቅሙ ሰርቶ በሚያድርበት መንደር ገበሬዎች ሥራ አይፈቱም፤ በሬ ጠምደው ሲያርሱ፣ ሲያዘምሩ ይውላሉ።

ትንሹ አለሽኝ በሊባኖስ መንደር ተወልዶ አድጓል። መልኩ የሚያሳሳ፣ ልጅነቱ የሚያጓጓ ብላቴና ነው። የቤቱ ትንሽ እሱ ነውና ሁሉም በስስት ያዩታል። ወላጆቹ አርሶ አዳሪ ገበሬዎች ናቸው። ቤታቸው የቆመው በግብርናው ከሚገኝ በረከት ነው። እነሱም እንደ ሀገሬው ከዓመት ዓመት የመሬታቸውን ፍሬ ይጠብቃሉ።

አለሽኝ ልጅነቱን ያሳለፈው እንደ ዕድሜ እኩዮቹ ነው። ከብት እያገደ ከሜዳው ቦርቋል። በልጅነት ጨዋታ ስቆ አልቅሷል። ወድቆ ተነስቷል። ዕድሜው ከፍ ሲል ወላጆቹ ዕድል አልነፈጉትም። ቀለም ቆጥሮ፣ ፊደል እንዲለይ ወደ ትምህርት ቤት ላኩት። ትንሹ ልጅ የልቡ ሞላ፣ የሃሳቡ ደረሰ። እርሳስ ደብተር አስገዝቶ “ሀሁ...ን” ለየ፤ ዕውቀት ገበየ።

አሁን አለሽኝ አስራ አንድ ዓመቱ ነው። ደስታን ከሀዘን፣ ክፉን ከደግ ለይቷል። ከፍ እያለ ሲሄድ ብዙ ማሰብ ያዘ። ነገ በትምህርቱ ማደግ፣ በዕውቀቱ መለወጥን ይሻል። በታሪክ እንደሚያውቃቸው አንዳንድ ምሁሮች ታዋቂ መሆን ፍላጎቱ ነው። ይህ እንዲሆን መሠረቱ ትምህርት መሆኑ ገብቶታል። ለዚህ ዓላማው ልዩ ትኩረት አለው። ልጅ ቢሆንም በትምህርቱ አይቀልድም። ሁሌም እየወደደው ይማራል፤ እየፈቀደው ከተማሪ ቤት ይውላል።

**የእግር ነገር...**

ውሎ አድሮ አለሽኝ አንድ እግሩ ማበጥ ያዘ። ነገ ‹‹ይጎድላል፣ ይሻለዋል›› ያሉ ወላጆች ቀን እያዩ ጠበቁ። ዕብጠቱ አልጎደለም። ይህ አጋጣሚ ለእሱ መሰል ታዳጊ ትርጉሙ ብዙ ነው። ባያመውም ለመማር ፈተና ሊሆንበት ይችላል። ከፍ ሲል ለትምህርት ከአካባቢው፣ ሰፈሩ ይርቃል። እንዲህ ከሆነ ችግር ነው።

ለእሱ እግሮቹ የልጅነት ኃይሉ ናቸው። ካሻው ይሮጥባቸዋል፣ ይዘልባቸዋል። መታመም ከያዘ ግን የልቡ አይደርስም፤ የፍላጎቱ አይሞላም። እንደዋዛ ቀናት ተቆጠሩ። አሁንም የአለሽኝ ቀኝ እግር ከእብጠቱ አልጎደለም። ሁኔታውን ያስተዋሉ አንዳንዶች ሃሳብ፣ አስተያየታቸው በዛ። ከነዚህ ብዙዎቹ ከራሳቸው ግምት ደረሱ። ውሎ አድሮ ግን ሚዛኑ ወደ ሕክምናው አደላ።

የሊባኖስ ጤና ጣቢያ አለሽኝን ተቀብሎ ተገቢውን ምርመራ አደረገ። የልጁ እግር አሁንም እንዳበጠ ነው። እንዲያም ሆኖ ህመም ይሉት ነገር የለውም። ሐኪሞቹ ጨነቃቸው። የሕክምና ምርመራው እንዳበቃ ይበጃል የተባለው መድኃኒትና መርፌ ታዘዘለት።

አለሽኝ የታዘዘለትን መርፌ ሳያቋርጥ እየተመላለሰ መወጋቱን ያዘ። መርፌውን በጀመረ ሰሞን እሱን ጨምሮ ብዙዎች መዳኑን አስበው ለውጡን ጠበቁ። ጉዳዩ እንደታሰበው አልሆነም። ይባስ ብሎ ዕብጠቱ ጎልቶ መታየት ጀመረ።

ሁኔታው ያሳሰባቸው ወላጆች የልጃቸውን እግር እየዳሰሱ ችግሩን ፈተሹ። እግሩ ከማበጥ አልፎ ውስጡ ጠንክሯል። ይህን ሲያውቁ መልሰው ከጤና ጣቢያው ወሰዱት። የጤና ባለሙያዎቹ ዳግም ሕመሙን መርምረው ከውሳኔ ደረሱ። ሕክምናው በጤና ጣቢያው አቅም የሚቻል አልሆነም። አለሽኝ ለተሻለ



**ወጣት አለሽኝ ቢተው**

ሕክምና ወደ ደብረማርቆስ ሆስፒታል ተላከ።

ከሆስፒታሉ ሲደርስ ሕክምናው ቀጠለ። የላብራቶሪ ምርመራና ተጨማሪ እገዛዎችን አገኘ። እንደታሰበው ሆኖ በደርሶ መልስ ሕክምና ቤቱ አልተመለሰም። ምርመራው በሐኪሞች ዓይን ትኩረት አግኝቶ ተኝቶ እንዲታከም ተወሰነ።

አለሽኝ በሆስፒታሉ ለቀናት አልጋ ይዞ ታከመ። አሁንም እግሩ ከዕብጠቱ አልተፋታም። ዛሬም እንደተወጠረ እንዳስጨነቀው ነው። ሕክምናው በቀላሉ አላበቃም። በየቀኑ የሚጎበኙት ሐኪሞች በትኩረት አልጋውን ከበው ይወያዩበት ያዙ።

አንድ ቀን የሐኪሞቹ ውሳኔ አዲስ ሃሳብን አስከተለ። አለሽኝ አሁንም ለተሻለ ሕክምና ወደ ባህርዳር መሄድ እንዳለበት ተወሰነ። ጊዜ አልባከነም። የአለሽኝ ወላጆች ውለው ሳያድሩ ልጃቸውን ባህርዳር ሆስፒታል አደረሱት። ከሆስፒታሉ ሕክምናውን የጀመረው ታዳጊ ተጨማሪ ምርመራ ተደርጎለት አልጋ ይዞ መታከም ጀመረ።

ከቀናት በኋላ የታዳጊውን የሕመም ዓይነት የደረሱበት ሐኪሞች ውጤቱን ለእሱና ለወላጆቹ አሳወቁ። አለሽኝ እስከዛሬ በእግሩ ዕብጠት ሲቸገርበት የቆየው ጉዳይ ካንሰር መሆኑን አረጋግጠዋል። በወቅቱ አለሽኝን ጨምሮ መላው ቤተሰብ ስለካንሰር ምንነት አንዳች አያውቁም። የተባሉትን ሰምተው ቀጣዩን ውሳኔ ለማድመጥ ቃል ጠበቁ።

የሐኪሞች ቦርድ አሁንም ለተሻለና ለከፍተኛ ሕክምና አለሽኝ ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንዳለበት አስታውቋል። ይህ እውነት ከትንሽዋ ገጠር መንደር ወጥተው ለማያውቁት ቤተሰቦች ቀላል የሚባል አልሆነም።

**የሊባኖስ እንግዶች**

የአስራ አንድ ዓመቱ ልጅ አለሽኝ በእግሩ ላይ የተገኘበት ካንሰር አዲስ አበባ አድርሶታል። በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተጀመረው ምርመራ በአንድ ጊዜ የሚቋጭ አልሆነም። ልዩ ክትትል የሚያስፈልገው ሕመም በተለያዩ ቀጠሮዎች የሚያመላልሰው ነበር። የመጀመሪያውን ክትትል አጠናቆ ሀገሩ የተመለሰው ታዳጊ ከሁለት ሳምንት በኋላ አልጋ ይዞ መታከም ጀመረ።

የተጀመረለት የኬሞ ቴራፒ ሕክምና ቀላል ይሉት አልነበረም። ኬሞ ለካንሰር ሕሙማን የሚታዘዝ ሕክምና ነው። ሕክምናው ሲጀመር አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ለውጥ መኖሩ አይቀርም። ሰውነት ይጎዳል፣ ጸጉር ይረግፋል። ማቅለሽለሽ፣ ማስመለሱ፣ መበሳጨት መቆዘሙ ውስጥን ይጎዳል።

አሁን አለሽኝ በእነዚህ አይመቼ መንገዶች ሊያልፍ፣ ሊመላለስ ግድ ብሎታል። ባልጸና አካሉ፣ ባልበረታ ማንነቱ ሊቀበለው የጀመረው ሕይወት አንድም ለብርታት፣ ሌላም ለነገ ዓላማው ጽናት ሆኖታል። የጉዞ መስመሩ ሻካራው ቢበዛም ይቅር ብሎ አልተወውም። ሕክምናውን ተቀብሎ ግዴታውን ሊወጣ ራሱን አዘጋጀ።

በአጋጣሚ አዲስ አበባ የደረሰ እንግዳ ጉዳዩ ብዙ ነው። ሀገሩን ተላምዶ ማረፊያና ምግብ ማግኘት ቀላል አይደለም። ውጣውረዱ፣ ትራንስፖርቱ፣ ሰው መግባባቱ ይፈትናል። በተለይ ታማሚ ላለበት እንግዳ ነገሮች የዋዛ አይሆኑም። ጎዶሎን የሚሞላ፣ ሃሳብን የሚካፈል ወዳጅ ዘመድ ያስፈልጋል።

**ቤት ለእንግዳ ...**

በአዲስ አበባ የአለሽኝ ወላጆች አንድ ሁለት ብለው የሚቆጥሩት ቤተሰብ የለም። ‹‹እከሌ›› የሚሉት ሁነኛ ዘመድን አያውቁም። ልጃቸውን ይዘው አዲስ አበባ የገቡት አባት የሰው ሀገር ሰው ናቸው። ከቀናት በአንዱ ግን ከአንድ ሰው ዘንድ ስልክ አስደውሉ።

ይህ ሰው አዲስ አበባ እንደሚኖር የተነገራቸው ዘመድ ነበር። ለሰውየው ችግራቸውን ዘርዝረው ማረፊያ እንደሚሹ ነገሩት። ታሪኩን የሰማው ሰው ከልቡ አዘነ። በዝምታ አልጨከነባቸውም። ገንዘብ መርዳት፣ ማገዝ ባይችል ማረፊያና ምግብ እንደማይነፍጋቸው ነግሮ ‹‹ቤት ለእንግዳ›› አላቸው።

አለሽኝና አባቱ ከሕክምና መልስ በቤቱ እያረፉ ጊዜያትን ቆጠሩ። ማረፊያና ምግብ በወጉ የተቸራቸው አባትና ልጅ ስድስት ወራትን በሕክምናው ቆዩ። ትንሹ አለሽኝ ውስጡ ከኖረው ድብቅ ዕጢ ይበልጥ ሕክምናው በአካል ፈተነው። የልጅነት አካሉ በኬሞቴራፒው ውጣ ውረድ ሲርድ፣ ሲሸነፍ ታወቀው። ይህ ቆይታ ከብዙ ክፉ ደግ አጋጣሚዎች አገናኘው። ከማይረሱ፣ አንዳንዴ ሲያስታውሷቸው ቶሎ ከማይፈዙ ድርጊቶች አመላለሰው።

**ከቀናት በአንዱ ...**

ሁሌም ከኬሞ ሕክምና በኋላ አካል ይደክማል፤ የቀመሱት ምግብ፣ ፉት ያሉት ሁሉ ልውጣ እያለ ይፈትናል። ሽታ፣ ጠረን ያስጠላል። ሕክምናው ግድ ነውና ደርሶ ልተው፤ ላቋርጠው ማለት አይቻልም። ይህ እውነት በልጆች ላይ በሆነ ጊዜ ሕመም፣ መከራው በእጥፍ ነው።

አንድ ቀን አለሽኝ በኬሞ ቴራፒ ሕክምና ሆስፒታል ቆይቶ ወደቤት ሊመለስ የሰፈሩን አውቶቡስ መጠበቅ ያዘ። እንደ ሁልጊዜው በእጅጉ ደክሞታል። በእግሩ መሄድ አልቻለምና አውቶቡስ መጠበቅ ምርጫው ሆነ።

ቆይታ ከፈጀ ጥበቃ በኋላ የሚጠበቀው አውቶቡስ ከስፍራው ደረሰ። አየነው እየተንገዳገደ ወደ ውስጥ ለማለፍ የአቅሙን ሞከረ። ሰዎች ተጠቅጥቀዋል፤ መቀመጫዎቹ ሞልተዋል። ልጅ ነውና እሱን ለማስቀመጥ ያሰበው አልተገኘም። አለሽኝ የኬሞው ድካም እያዞረ፣ እያጥወለወለው ነው። በዚህ መሀል እግሩን ዘርግቶ ከተቀመጠ አንድ ሰው ጋር በአካል ተነካኩ።

ሰውየው ብስጭቱ አይሎ ሊመታው ተጋበዘ። አቅም ያጣው ብላቴና ሊመልስለት አልቻለም። ለማስረዳት አፉን ከማላወሱ ይባስ ብሎ ገፍትሮ ጣለው። አለሽኝ ሆድ ባሰው፤ ዕንባ አነቀው። አጋጣሚ ሆኖ ጉዳዩን በቅርበት ያስተዋለ ሌላ ሰው ከወደቀበት አንስቶ ‹‹አይዞህ›› ሲል አጽናናው። ከወንበር አስቀምጦም በወጉ ተንከባከበው።

በወቅቱ አለሽኝ በሆነው ሁሉ ከልቡ አዝኖ በራሱ አማሯል። የዛን ዕለትን አጋጣሚ ዛሬ ሲያስታውሰው ሆዱ ይጎሻል። በአንዳንድ ሰዎች ድርጊት ይከፋል። እንደ ሁለተኛው ዓይነት ሰው ደግ ልቦና ባላቸው መልካም ሰዎች ደግሞ ይጽናናል፤ ይበረታታል።

አለሽኝ ዕድሜው መጨመር ሲይዝ ራሱን ችሎ ሕክምናውን መከታተል ጀመረ። ሕክምናው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብቻ በመሆኑ በየጊዜው ከጎጃም አዲስ አበባ መመላለስ ግድ ይለዋል። ቤተሰቦቹ እሱን ለማዳን ብዙ ደክመው አቅም ጉልበታቸውን፣ ገንዘብ ጊዜያቸውን ሰጥተውታል።

አንዳንዴ ወላጆቹ ስለልጃቸው ሕመም መልስ ባጡ ጊዜ ሁሉን ትቶት እንዲቀመጥ ይመክሩታል። ዓመታት በቆጠረው ሕክምና ተማረውም ይበሳጫሉ። ለእነሱ በመድኃኒት ቆይታ ጊዚያትን መግፋቱ ትርጉም የለሽ ነው። አንድ ቀን “ድኛለሁ” ብሎ እንዲያውጅ ይሻሉ። ይህ አለመሆኑ ውስጣቸውን አድክሞታል።

የልጃቸውን መጨረሻ የሚናፍቁት ወላጆች አሁን ላይ ሕክምናውን ሊረሱት እየፈለጉ ነው። አለሽኝ በምልልስ የሚፈጀውን ግዜ ከብክነት ቆጥረውታል። ከዚህ ይልቅ እንደ ልጅነቱ ውለታ እንዲመልስ፣ ጉልበት እንዲከፍል ይፈልጋሉ። እሱም ቢሆን ልፋት ድካማቸውን አይዘነጋም።

አለሽኝ ወላጆቹ ይህን የሚያስቡት ስለ ካንሰር ግንዛቤው ስለሌላቸው መሆኑን አሳምሮ ያወቃል። አሁን ወጣትነት ዕድሜ ላይ ነው። ትናንት ጤናውን ሊመልስ፣ ከመድኃኒቱ ለመገናኘት ሲል ያለፈበትን መንገድ አይዘነጋውም። ሕክምና ከጀመረ ወዲህ የሚሰማው ሕመም የለም። ለዚህም ፈጣሪውን ከልቡ ያመስግናል።

**ቁርጥ ውሳኔ ...**

ዛሬ ሕመም ላይ ባይሆንም ክትትሉን ማቋረጥ አይሻም። ቀጠሮ ባለው ጊዜ ከጎጃም አዲስ አበባ እየመጣ ይታከማል። አለሽኝ ኬሞቴራፒ ከወሰደ ከአስር ዓመት በላይ ሆኖታል። ክትትሉ በቀሪ ሕክምናው ላይ ነው። አስተውሎ ላየው ገጽታው ያምራል፣ አቋሙ ጥሩ ነው።

ሁሌም ይህን ለውጥ የሚያዩ ወላጆች ታዲያ ፍጹም የዳነ መስሏቸው የእጃቸውን ነፈጉት፤ ከኪሳቸው መክፈል ከልክለውም ‹‹ከእንግዲህ በቃን፤ አንችልም›› ሲሉ ድካማቸውን አሳዩት።

አለሽኝ በውሳኔያቸው አልተከፋም። ይህን ባወቀ ጊዜ ወደማቴዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ደውሎ ጉዳዩን አስረዳቸው። ውስጡን ያደመጠው ማዕከል ሃሳቡን ተቀብሎ ለማገዝ አልዘገየም። ሕክምና በኖረው ጊዜ ሙሉ የትራንስፖርት ወጪውን ችሎ ማረፊያውን ሊሰጠው ቃል ገባለት።

አለሽኝ ምላሹን በምስጋና ተቀበለ። ቀጠሮ ባለው ጊዜ ትራንስፖርቱ ሞልቶሎት፣ ማረፊያው ተመቻችቶለት መመላለሱን ቀጠለ። ዛሬ ሃያ አንደኛ ዓመቱን የያዘው ወጣት ከዓላማው አልተናጠበም። በሕመም ሲወድቅ ሲነሳ የወጠነውን ትምህርት ቀጥሎ ዘጠነኛ ክፍል ደርሷል።

አሁን አለሽኝ ፍጹም ጤነኛ ወጣት ነው። በጠዋቱ የተደረሰበትን የካንሰር ሕመም አሸንፎ በድል መራመድ ይዟል። ዛሬ ከፊቱ ብሩህ ተስፋ ይነበባል። ስለነገ የሰነቀው ደግሞ የእሱንና መሰሎቹን ሕይወት የሚታደግ ነው። ነገን ዶክተር ሆኖ ወገኖቹን ማከም፣ ሕመምን መፈወስ ህልሙ ነው።

ይህን ለመወሰን ምክንያቱ የራሱ ሕይወትና ያለፈባቸው ፈታኝ መንገዶች ናቸው። አለሽኝ ባሳለፈው የሕክምና ሂደት በርካቶች በሕመም ሲሰቃዩ፣ ለእንግልትም ሲደረጉ አስተውሏል። ለዚህ መሰል አጋጣሚ እማኝ የሆነው ወጣት ይህን ታሪክ ለመለወጥ በሕክምና ሙያ ማሸነፍ ምኞቱ ነው።

**ዛሬን ...**

አለሽኝን ያገኘሁት በማቴዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ግቢ ውስጥ ነበር። ዛሬን በሥፍራው የተገኘበት በሕክምናው ቀጠሮ ምክንያት ነው። ለቤቱ ቤተኛ የሆነው አለሽኝ አዲስ አበባ መምጣት በፈለገ ጊዜ ሶሳይቲው ከጎኑ ለመሆን ተባባሪው ነው። ለመንገዱ የትራንስፖርት ገንዘብ፣ ለማረፊያው ቤትና መኝታ ነፍጎት አያውቅም።

አለሽኝ ከሕክምናው ቆይታ በኋላ ቤተሰቦቹን በእርሻ ያግዛል። እንደ ልጅነቱ ዝቅ ብሎ ይታዘዛል። እነሱ ዛሬም ድረስ የሚወስደው የምልልስ ሕክምና ተመችቷቸው አያውቅም። ሁሉን ትቶ ቢቀመጥ፣ ከጎናቸው ሆኖ የልባቸውን ቢሞላ ይወዳሉ።

እርሻና ጉልጓሉ በኖረ ጊዜ የአለሽኝ ጉልበት የሚፈለገው እንደ ሌሎች ሰዎች ነው። ቢያመው፣ ቢደክመው እንዲያርፍ አይፈቅዱለትም። እሱን ያመዋል፣ ይደክመዋል የሚል አሳቢም ከጎኑ የለም። ቤተሰቦቹ እንዲህ በማድረጋቸው ተቀይሞ አያውቅም። በቻለው አቅም ሁሉን ሊያስረዳ፣ ሊያሳምናቸው ይሞክራል።

አለሽኝ አለማወቅ በፈጠረው የግንዛቤ ክፍተት ያለ አጋርና ደጋፊ ራሱን እያሳከመ እዚህ ደርሷል። ከተወለደባት ትንሽዋ የሊባኖስ ቀበሌ እንደ ባህር ከሰፋው አዲስ አበባ ድረስ ስለሕይወቱ ብዙ ከፍሏል። ነገ ግን ለእሱ ብሩህና ደማቅ ነው። ለመከራዎች እጅ አይሰጥም፤ ለክፉ አጋጣሚዎች አይሸነፍም። ጠንካራውና ብርቱ ወጣት አለሽኝ ቢተው።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

## ቡና ቀማሹ ሥራ ፈጣሪ

ማህሌት አብዱል

የዛሬው የስኬት እንግዳችን አቶ ምኒልክ ሀብቱ ይባላሉ። የምኒልክ ኢንጅነሪንግና የ‹‹ቲፒካ ስፒሻሊቲ ኮፊ›› ማኔጂንግ ዳይሬክተር ናቸው። ውልደታቸውም ሆነ እድገታቸው አዲስ አበባ ውስጥ ነው። ከ11 ቤተሰብ አባላት ካሉበት ቤተሰብ የወጡት እኚሁ ሰው ወላጆቻቸው ሥራ ወዳድና ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ከልጅነታቸው ጀምሮ ሥራ ሳይንቁ እንዲሰሩ በማድረግ ያሳደጓቸው መሆኑን ያነሳሉ። በተለይ ደግሞ ታታሪው አባታቸው ሰርተው በማሰራት ልጆቻቸው ችግሮቻቸውን በራሳቸው የመፍታት ብቃት እንዲያዳብሩ ያደረጓቸው መሆኑን ያስታውሳሉ።

አሁን ለደረሱበት ደረጃ እርሾ ሆና የጠቀመቻቸውን ገጠመኝ ሲያስታውሱ ‹‹የመጀመሪያ ገንዘብ ያገኘሁባት ሥራ የትምህርት ቤት ሽንት ቤት ጉድጓድ በመቆፈር ነው›› ይላሉ። በአንድ ወቅት ኳስ እየተጫወቱ ሳለ በአቅራቢያቸው ያለ አንድ ትምህርት ቤት መምህራን ሽንት ቤቱን ሳያስጠርጉ የትምህርት ቤት መከፈቻ ጊዜ መድረሱ አስጨንቋቸው ሲወያዩ ያደምጣሉ። ከሥራ ወዳድ ቤተሰብ የወጡት የያኔው ታዳጊ ምኒልክ፣ የመምህራኑን ጭንቀት አይተው ማለፍ አልቻሉም፤ ይልቁንም የመፍትሔ አካል ለመሆን ወደዱና እንደምንም አሳምነው ሊያግዟቸው ጥያቄ ያቀርባሉ። ይሁንና መምህራኑ በታዳጊው ልጅ ላይ እምነት ለመጣል አልደፈሩም።

ከብዙ ንግግር በኋላ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪው ምኒልክ ሃሳብ ተቀባይነት አገኘ። ከወንድሞቻቸው ጋር በመሆን በአንድ ሳምንት ውስጥ ሌላ ጉድጓድ ቆፍረው መፀዳጃ ቤቱን አድሰው ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አስረከቡ። ‹‹የትምህርት ቤቱ አመራሮች በሠራሁት ሥራ በጣም ስለተደሰቱ፤ ከውላችን ውጭ በእጥፍ ከፈሉኝ›› ይላሉ።

በዚያች አጋጣሚ በራስ ልፋት ገቢ ማግኘት የለመዱት እኚሁ ሰው 11ኛ ክፍል ሳሉ ደግሞ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለቴክኒክና መጋዘን ተቆጣጣሪ ባለሙያ ቅጥር ማውጣቱን ይሰሙና ሙያውን ያውቁት ስለነበር በድፍረት ይወዳደራሉ። እናም የ16 ዓመቱ ምኒልክ ዲግሪና ሰፊ ልምድ ከነበራቸው አንጋፋ ሰዎች ጋር ተዋዳድረው ፈተናውን በአንደኝነት አልፈው ተቀጠሩ። ግማሽ ቀን እየተማሩ በሥራቸው ረዳቶችን ቀጥረው ማሰራት ጀመሩ። የወጣቱን ቅልጥፍና እና ትጋት ያዩ የወባ መከላከል ተቋም የሥራ ኃላፊዎች የመድኃኒት ማውረድና መጫን ሥራን በኮንትራት ሰጧቸውና ጎን ለጎን ሠራተኛ ቀጥረው በማሰራት የፋይናንስ አቅማቸውን አጎለበቱ።

ከቴክኒሻን አባታቸው ሥር ሆነው ልምድ እየቀሰሙ ማደጋቸውን የሚናገሩት አቶ ምኒልክ፤ ይሁንና ሙያውን ገንዘብ ለማግኛ እንጂ ወደውት ይሰሩት እንዳልነበር ይናገራሉ። ‹‹የእኔ ምኞት ፓይለት ወይም ሐኪም መሆን ነበር፤ አባቴም ‹ፓይለት ትሆናለህ› እያለ ነው ያሳደገኝ፤ ግን የሚጠየቀውን መስፈርት ማሟላት ባለመቻሌ የምፈልገውን መሆን አልቻልኩም›› ይላሉ።

በመሆኑም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብተው በ‹‹ላይብረሪ ኤንድ ኢንፎርሜሽን ሳይንስ›› ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተው እንደወጡ በቀጥታ አባታቸውን በቴክኒኩ ያግዙ ጀመር። በኋላም አባታቸውን በሞት ሲያጡ ምኒልክ ኢንጂነሪግ የተሰኘውን የአባታቸውን ድርጅት የመረከብና ቤተሰቡን በፋይናንስ የማስተዳደር ኃላፊነት እሳቸው ላይ ወደቀ።

‹‹በወቅቱ ሥራውን ስረከብ እኔና ታናሽ ወንድሜ ብቻ ነበርን፤ በሂደት ግን ሌሎቹ ልጆች በእረፍት ጊዜያቸው አብረውን እንዲሰሩ በማድረግ ምኒልክ ኢንጅነሪንግን እያሳደግን መጣን›› ይላሉ። በየጊዜው ከውጭ ሠራተኞችን በመቅጠርም ትልልቅ የኢንጂነሪንግ ሥራዎችን ተረክበው የመሥራት አቅም ማጎልበታቸውን ይናገራሉ።

‹‹አልችልም›› የሚሉት ሥራ እንደሌለ የሚናገሩት አቶ ምኒልክ፣ ከሙያቸው ውጭ የሆነ ሥራ እንኳን ሲታዘዙ ተረክበው የሚችሉ ሠራተኞች ቀጥረው በማሰራት ለደንበኞቻቸው እንደሚያስረክቡ ያስረዳሉ። ‹‹በዚያ ሥራ ባላተርፍበትም እንኳን ሙያ እለምድበታለሁ፤ ደንበኞችን አፈራበታለሁ ብዬ ስለማምን አልችልም ብዬ የምገፋው ሥራ የለም›› በማለት ይገልፃሉ።

ይህም ጥረታቸው ታዲያ ለፍቶ መና አላስቀራቸውም። የኢንጂነሪንግ ኩባንያቸው እየተስፋፋ ሄዶ ‹‹ቲፒካ ስፔሻሊቲ›› የተባለውን ድርጅት ወለደ። ይህን ድርጅት የከፈቱበትን አጋጣሚ ሲናገሩ ‹‹እኛ የተለያዩ ማሽኖችን እናመርታለን፤ ግን ደግሞ የምናመርታቸው ማሽኖችን ጥራት ሞክሮ ማሳየት ይጠበቅብን ነበር፤ በዚህ ምክንያት የቡና መቁያ ማሽናችንን ጥራት ለደንበኞቻችን ለማሳየት ስንል ቡና ቆልተን ማሳየት ነበረብን፤ ነገር ግን ቡናውን ቆልተን ማስቀመጥ ኪሳራ በመሆኑ ቡናውን ቆልተን የምንሸጥበት ሌላ ድርጅት ከፈትን›› ይላሉ።



አቶ ምኒልክ ሀብቱ

> **ይህም ጥረታቸው ታዲያ ለፍቶ መና አላስቀራቸውም። የኢንጂነሪንግ ኩባንያቸው እየተስፋፋ ሄዶ ‹‹ቲፒካ ስፔሻሊቲ›› የተባለውን ድርጅት ወለደ**

‹‹ቲፒካ›› ማለት የመጀመሪያው የቡና ዘር ሳይንሳዊ ስያሜ እንደሆነ አስረድተው፤ ‹‹ቲፒካ ዓለም ላይ የሚታወቀው አረቢካ ቡና ዋና ዘር ነው፤ የኢትዮጵያን ቡና ወደ ገበያ ያወጡት አረቦች በመሆናቸው የእኛን ቡና በራሳቸው ስም መሰየሙ ሁልጊዜም ስለሚቆጨኝ ነው በሳይንሳዊ ስሙ እንዲታወቅ ስል የሰየምኩት›› ሲሉ ያብራራሉ። ድርጅቱ አረንጓዴ እና የተቆላ ቡና ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ መሆኑን አንስተው፤ በስሩ አምስት ራሳቸውን የቻሉ ተቋማትን መፍጠሩን ይገልጻሉ። ከእነዚህም መካከል በቡና አቆላልና አፈላል እንዲሁም ቡና የመቅመስ ችሎታን የሚያዳብሩ ስልጠናዎችንና የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም መከፈቱን ያመለከታሉ።

በዓለም የተመሰከረለት ቡና ቀማሽ እንዲሁም ቆዩ የሆኑት አቶ ምኒልክ፣ በግላቸው ጥረት በቡና ላይ ባደረጉት ጥናትና ምርምር እንዲሁም የተለየ ጣዕም ያለው የኢትዮጵያ ቡና ራሱን ችሎ በዓለም ደረጃ እንዲታወቅ ባበረከቱት አስተዋፅኦ በተለያዩ ጊዜያት በርካታ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝተዋል። ‘ካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ’ በተባለው ሀገር አቀፍ የቡና ቅምሻ ውድድር ንቁ ተሳትፎ የነበራቸው እኚሁ ሰው በቡና መቁላት፤ በካይዘንና በመሳሰሉት ዘርፎች በርካታ ሰርተፊኬቶችን አግኝተዋል።

በቡና ላይ ያገኙትን እውቀትና ልምድ ግን ብቻቸውን ይዘው ለመዝለቅ አልወደዱም፤ ይልቁንም ለተተኪው ትውልድ ለማውረስ በከፈቱት የስልጠና ተቋም ከሙያ ተቋማት የሚወጡ ወጣቶችን በመመልመል አጫጭር ሥልጠናዎችን መስጠት ጀመሩ።

ይህም በሀገር ውስጥ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲበራከት አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ ሲሆን፤ በተለይም ቡናው የእኛ ሆኖ ሳለ የጥራት ደረጃውን የሚሰጠው አካል በውጭ ምንዛሬ ከሌላ ሀገራት የሚመጣ መሆኑ፤ ይህም የዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ጉዳይ በሌላ ሀገር እጅ ስር እንዲወድቅ የሚያደርግ መሆኑን በመረዳት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከት እየተጉ ይገኛሉ። ‹‹ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከቡና መቁላት ጀምሮ እስከ ማፍላት ድረስ ባለሙያዎችን እናሰለጥናለን፤ ያሰለጠንናቸውንም መልሰን እንቀጥራለን፤ ሌሎችም እኛ አሰልጥነናቸው ትልልቅ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረዋል›› ይላሉ።

የኢትዮጵያ ቡና ቆዩዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ሆነው ለስምንት ዓመታት ያገለገሉት አቶ ምኒልክ፣ ድርጅታቸው ለማህበሩ አባላትና በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት በሙሉ በየዓመቱ ስልጠና ይሰጥ እንደነበር ያስታውሳሉ። በዚህም ከ100 ያላነሱ እውቅ የቡና ባለሙያዎችን ለሀገሪቱ ማበርከታቸውን ይገልፃሉ። በተያዘው በጀት ዓመት ማሰልጠኛ ተቋማቸው በጀማሪ ደረጃ 26፣ በመካከለኛ ደረጃ ደግሞ ስምንት ሰዎችን ማሰልጠኑን ይናገራሉ።

ዘርፈ ብዙ አገልግሎት የሚሰጠው ድርጅታቸው ገበያው የሚፈልገውን በማጥናት የተለያዩ ሥራዎችን መስራቱን የሚናገሩት አቶ ምኒልክ፤ በአንድ ወቅት የኮንስትራክሽን ዘርፉን በመቀላቀል በቤቶች ግንባታ ላይ ከብሎኬትና ፒሪካስት ማምረት እስከ ቤት ግንባታ ድረስ ተሳትፎ ማድረጉን ይገልፃሉ። በተለይም ከሜቴክ ጋር በመተባበር የትራክተር ተጎታቾች፤ የመኪና ላይ ቆሻሻ መጫኛዎች፤ ሲሚንቶ ማቡኪያ መሳሪያ፤ ትልልቅ የውሃና የነዳጅ ታንከሮች የመሳሰሉትን ማምረቱንም ያመለክታሉ። ባለሙያዎችን በማሰባሰብ በሀገሪቱ እጥረት በሚታይባቸው ዘርፎች ሁሉ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እያበረከቱ ቆይተዋል።

በአሁኑ ወቅት ከ60 በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድል የፈጠረ ሲሆን፣ ለወጣቶች የተለያዩ ስልጠናዎችን በነፃ በመስጠት የሥራ እድል እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታን በመፍጠርም አቶ ምኒልክ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ። በሀገር ውስጥ የተለያዩ አካባቢዎች በከፈቷቸው ሱቆች የተቆላ ቡና የሚያከፋፍሉ ሲሆን በተወሰነ ደረጃ ወደ ውጭም ይልካሉ። ሁለት ጊዜም ድርጅታቸው ያመረተውን የቡና መቁያ ማሽን ሃጂ ቱሬ በተባለ ድርጅት አማካኝነት ቻይና እና የመን መላካቸውን አቶ ምኒልክ ያመለክታሉ። በወቅቱ አምነው ሥራ ይሰጧቸው የነበሩ ተቋማት አሁን ለደረሱበት ደረጃ የጎላ ድርሻ እንዳላቸው ያነሳሉ። ‹‹እንደኛ ራሱን ለመቻል ጥረት የሚያደርግ ድርጅት የፋይናንስ አቅርቦት ማግኘት ከባድ በሆነበት ጊዜ እንደ ሜቴክና ሃጂ ቱሬ ያሉ ድርጅቶች አምነውን ቅድሚያ ክፍያ ሰጥተው ባያሰሩን ኖሮ እዚህ መድረስ አንችልም ነበር›› ሲሉ ይገልፃሉ።

አሁን ባለው የዓለም ገበያ ቡና ብቻውን ወደ ውጭ መላክ አትራፊ አለመሆኑን የሚያስረዱት አቶ ምኒልክ፤ በተለይም ጥሬ ቡና ወደ ውጭ ልኮ ገቢ ለማግኘት ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም የሚፈልግ መሆኑን ይናገራሉ። በሌላ በኩል የሀገር ውስጡ የቡና ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ አብዛኛውን የቡና ምርታቸውን እዚሁ ሀገር ውስጥ ለመሸጥ መገደዳቸውን ያመለክታሉ። ከዚሁ ጎን ለጎን የማስልጠንና ማማከር ሥራቸውን አጠናክረው ማስቀጠላቸውን ነው የሚያብራሩት።

በሌላ በኩል ከወጪ ንግዱ ጋር ተያይዞ የሚወጡ መመሪያና ደንቦች በአግባቡ የማይተገበሩ በመሆናቸው ሃቀኛ ነጋዴው ከገበያ ውጭ የሚሆንበት አጋጣሚ መኖሩን ይናገራሉ። ለአብነት አድርገው ሲጠቅሱም ‹‹ቱሪስቶች የእኛን ሀገር ቡና በጣም ስለሚወዱ ወደ ሀገራቸው ይዘው መሄድ ይፈልጋሉ። ይሁንና እሴት የተጨመረበት ቡና በውጭ ምንዛሬ ቢገዙም ከሁለት ኪሎ በላይ ይዘው መውጣት ይከለከላሉ። እኔ ታክስ ከፍዬ የምሰራ ሰው ሆኜ ሳለ የተወሰኑ ተቋማትን ለመጥቀም ሲባል ብቻ ኤርፖርት ላይ ካልተገዛ ይዞ ለመውጣት መከልከሉ ተገቢ አይደለም›› ሲሉ ይናገራሉ። በመሆኑም መንግሥት ቱሪስቱ ይዞ የመጣውን የውጭ ምንዛሬ እዚሁ ሀገር ውስጥ እንዲያስቀር ከተፈለገ ለጉብኝት በመጣበት አጋጣሚ ቡናውን ቀምሶ የሚገዛበት ሁኔታ ማመቻቸትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ማበረታታት ይገባዋል ባይ ናቸው። ይህም ሲሆን የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ይነቃቃል የሚል እምነት አላቸው።

ድርጅቱን ከአባታቸው ተረክበው ሥራ ሲጀምሩ ከ70 ሺ ብር የማይበልጥ ካፒታል እንደነበረው የሚያስታውሱት አቶ ምኒልክ፤ የራሳቸውን ማምረቻ ሕንፃ ቃሊቲ ላይ ከመገንባታቸውም ባሻገር ካፒታላቸውንም ከ100 ሚሊዮን ብር በላይ ማሳደጋቸውን ይናገራሉ። በቀጣይ ድርጅታቸው የሚያመርታቸውን ማሽኖች በምስራቅ አፍሪካ ተደራሽ ለማድረግ ራዕይ ሰንቆ እየሰራ መሆኑን ያመለክታሉ። በተለይ ልክ እንደ ቡናው ሁሉ ኢትዮጵያን በቡና ማሽኖች በአፍሪካ መሪ የማድረግ ራዕይም እንዳላቸው ይጠቁማሉ። በተጨማሪም የተቆላ ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብም ለሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ለማስገባትም የበኩላቸውን ጥረት እያደረጉም ስለመሆኑ ይገልፃሉ።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## መሬትን በተቀናጀና በተናበበ መንገድ ማስተዳደርና መምራት ያስፈለገበት ዘመን

በኃይሉ አበራ

የሀገሪቱ የመሬት አስተዳደር ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ መሬት ላይ ፍላጎት ያላቸው ተቋማት ወይም መሬትን እንዲመሩ የተቋቋሙ መንግሥታዊ ተቋማት በርካታ ናቸው። ይህ አሰራር ተቀናጅቶ መሬትን በማስተዳደር በኩል አለመግባባት እንዲፈጠር፣ የግጭት መንስኤ እንዲሆን እያደረገ መሆኑ እየተጠቆመ ነው። መሬት የሚተዳደርበት ሕግም የከተማና የገጠር የሚል መሆኑ በራሱ ሌላው የልማት ተግዳሮት እንደሆነም ይገለጻል።

የመሬት አስተዳደር ሥራ የከተማ እንዲሁም የገጠር በሚሉ ሁለት አደረጃጀቶች ሲሰራ ቆይቷል። በከተማ የመሬት አስተዳደር ውስጥ ብቻ ብዙ መቀናጀት የማይታይባቸው ተቋማት ይገኛሉ። በገጠርም በተመሳሳይ የመሬት ተቋምን አንድ ላይ ያቀፈ አካል አለመኖሩ ለመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ ለሀብትና ጊዜ ብክነት መነሻ ሲሆን ይታያል የሚሉ ወገኖችም አሉ።

የዘርፉ ባለሙያዎችም በሀገሪቱ ከሚታዩ በርካታ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አንዱና ዋነኛው የመሬት አስተዳደር ችግሮች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይሄንን ችግር ለመፍታት ቢያንስ ተቋማዊ አደረጃጀቱ ላይ መሥራት እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

በኢትዮጵያ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ማህበር የተቋቋመው እና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ተካሂዶ በቅርቡ የቀረበ ጥናት እንዳመለከተውም፤ ጥናቱ በመሬት አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለይቷል፤ በዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ተሞክሮ ላይ የተመሰረተና ለመንግሥትም የፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ምክረ ሃሳብም ይዞ ቀርቧል። የሀገሪቱ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት መዘመን እንደሚኖርበትም አመላክቷል።

ዶክተር አቻምየለህ ጋሹ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የመሬት አስተዳደር ኢንስቲትዩት ተባባሪ ፕሮፌሰር እንዲሁም ኢትዮጵያ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ናቸው። እሳቸው እንዳሉት፤ መሬት በደላሎች እጅ የገባበት አንዱና ዋነኛው ምክንያት መሬትን በአግባቡ ሊመራ የሚችል የተግባባ የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት ስለሌለ ነው። ደላሎች በብዛት ተፅዕኖ እያሳደሩ ያሉት በከተማ እና በከተማ ዙሪያ በሚገኘው መሬት ላይ ነው። በተለይም በከተማ ዙሪያ ባለው መሬት ላይ ችግሩ ተባብሶ ይስተዋላል።

የኢትዮጵያ መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ማህበር በሀገራችን ባለው የመሬት አስተዳደር ላይ የሚታዩ ከፍተኛ ችግሮችን ለማቅለል እንዲሁም የሀገራችን የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች መንግሥትንና ማህበረሰቡን በሙያቸው ለመደገፍ በሚል መነሻነት በ2012 ዓ.ም እንደገና የተቋቋመ ነው። ማህበሩ ሀገር አቀፍ ሽፋን ያለው ሲሆን በርካታ ባለሙያዎችንም ይዟል።

አባላቱም ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች እና ከትምህርት ተቋማት የተሰባሰቡ መሆናቸውን ዶክተር አቻምየለህ ጠቁመዋል። ማህበሩ ከተቋቋመ ወዲህ እንደ ሙያ ማህበር ጥናቶችን በማካሄድ መንግሥት ለፖሊሲ ግብዓት እንዲጠቀማቸው የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ተናገረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ማህበሩ መንግሥት በሚያካሂደው የመሬት አስተዳደር ፖሊሲ ዝግጅት ላይ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። በርካታ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችንም እየሰጠ ነው። አንድ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት በሚሻሻልበት መንገድ በሰው ኃይል ግንባታው ላይም መሥራት ያስፈልጋል። በቀዳሚነት የአቅም ግንባታ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው።

በክልል ደረጃ ለአብነት የአማራ ክልል የመሬት አስተዳደር ተቋማዊ አደረጃጀቱን ወደ አንድ ተቋም ሲያመጣም ማህበሩ እና በማህበሩ ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች ተሳትፎ ማድረጋቸውን ጠቅሰው፣ ለዚህ ፖሊሲ ግብዓት የሚሆን ጥናት በማካሄድ በዚያ መሠረት የክልሉን የመሬት አስተዳደር ሥርዓት የሚመራ አንድ ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር የመሬት ቢሮ የሚል አደረጃጀት ተፈጥሮ እየተሰራበት መሆኑን አመልክተዋል።

ዶክተር አቻምየለህ እንዳብራሩት፤ መሬት የሰው ልጆች ውድ ሀብት ነው፤ የሀብቶች ሁሉ ምንጭ የሆነ ሀብትም ነው። ይህ ውድ ሀብት በአግባቡ ካልተመራና ካልተዳደረ የችግሮች ሁሉ ዋና ምክንያት ይሆናል። የመልካም አስተዳደር፣ የግጭቶች ሁሉ ችግር ከመሬት ጋር ሊያያዝ ይችላል።

የሰው ልጅ አብዛኛዎቹ ግጭቶች ከመሬት ጋር የተያያዙ መሆናቸውን የፍርድ ቤት ኬዞችን ዋቢ በማድረግ ዶክተር አቻምየለህ ገልጸዋል። ከፍርድ ቤት ኬዞች በርካታዎቹ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ስለመሆናቸው ጥናቶች እንደሚያመለክቱ አስገንዝበዋል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፈንታ ደጀን በበኩላቸው የሀገሪቱ ትልቅ ሀብት የሆነውን መሬት የማስተዳደር ሥራን ለማዘመንና አጠቃቀሙን ለማሻሻል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት አጀንዳ መሆኑን አመላክተዋል።

> **የሀገሪቱ ትልቅ ሀብት የሆነውን መሬት የማስተዳደር ሥራን ማዘመንና አጠቃቀሙን ማሻሻል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራበት አጀንዳ ነው**

ሚኒስትር ዴኤታውም መሬት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማትና እድገት የማይተካ ሚና ያለው የሀብቶች ሁሉ ቁንጮ የሆነ ሀብት መሆኑን አስገንዝበዋል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የኢኮኖሚ መሠረታቸው እና ሕዝባቸው በእርሻ ሥራ ላይ ለተመሰረተ ሀገሮች ደግሞ መሬት ማለት የተለየ ትርጉም ያለው ይላሉ።

ይህንን በሚገባ በመረዳትም መሬት በሀገራችን የሕገ መንግሥት አካል ሆኖ ተደንግጓል። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት ላይ እንደተመለከተው መሬት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረ-ብሔሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ሀብት ነው። ክልሎች በተሰጣቸው የአስተዳደር ወሰን የፌዴራል መንግሥቱ በሚያወጣው ሕግ መሠረት የማስተዳደር ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።

መሬት ከተፈጥሮ ሀብቶች ሁሉ አንዱና ትልቁ ነው። የሰው ቁጥር ሲጨምር፣ የልማት ፍላጎት ይጨምራል፣ የተፈጥሮ ሀብት ይቀንሳል፣ በዚህም የጥቅም ግጭት ይፈጠራል። የአሁኑና የወደፊቱ፣ አካባቢ እና ልማት፣ የግል እና የሕዝብ የልማት እሳቤዎች ይህንን የሀብቶች ሁሉ መሠረት፣ ለመልካም አስተዳደር መስፈን ወይም መታጣት ምሰሶ የሆነን ሀብት በአግባቡ ማስተዳደር አስፈላጊ ነው ሲሉም አስገንዝበዋል።

መሬትን በአግባቡ ማስተዳደር ማለት የመሬት ይዞታ መብት የሚሰጥበት፣ ዋስትና የሚከበርበት፣ የመሬት ሀብት ዋጋ የሚተመንበት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት በመሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበትና ግዴታዎች የሚተገበሩበት መሆኑንም አስታውቀዋል። በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ በመሰብሰብ የሚተነተንበትና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጭበት ሂደትን በአግባቡ በሕግና በሥርዓት መምራትን እንደሚያካትትም ተናግረዋል።

እነዚህን ተግባራት በአግባቡ ለማከናወን፣ ከመሬት አስተዳደር ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት ወይም ለመቀነስ፤ ሀገር ከመሬት ማግኘት ያለባትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ሁለንተናዊ ጥቅም እንድታገኝ ለማድረግ መሬትን በተቀናጀና በተናበበ መንገድ ማስተዳደርና መምራት ለነገ የማይባል ወሳኝ ሥራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ የገጠርንም ሆነ የከተማ የመሬት አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባትና ዘርፉንም በተሻለ ሁኔታ ለመምራት እንዲቻል የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ መሆናቸው ይታወቃል። ነገር ግን በዘርፉ በመደረግ ላይ ያሉ ጥረቶች የሚፈለገውን ያህል ርቀት ያልተጓዙና በተበታተነ የተቋም ቅርጽና አደረጃጀት ላይ የተመሰረቱ በመሆኑ ዘርፉንም ሆነ ውጤቱን በዘላቂ መንገድ ላይ እንዲገኝ አላስቻሉትም።

በተለይም በመሬት ዙሪያ ያለው የአደረጃጀት ችግር ለዘመናት ሳይፈታ በመቆየቱ ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበና ስር እየሰደደ መጥቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ይህ ተቋማዊ ሁኔታ የዘርፉን ባለሙያዎች፣ ተግባሩን የመምራት ፖለቲካዊ ኃላፊነት ያለባቸውን ወገኖች እንዲሁም የዘርፉን መዘመን የሚሹና ለመልካም አስተዳደር መስረጽና ለኢኮኖሚ ዕድገት ያለውን ሚና የሚረዱ ወገኖችን ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ እያሳሰበ እንደሚገኝም አመላክተዋል።

በሌላ በኩል እስካሁን የተገኙ ውጤቶችን ለመጠበቅና ስር እንዲሰዱ ለማድረግ የሚቻለው፣ የመሬት አስተዳደር ሥርዓት ግንባታውም በዘላቂ መሠረት ላይ ሊቆም የሚችለው፣ እስካሁን እንደመጣንበት መንገድ በዘመቻ ወይም በአንድ ወቅት በሚገኝ የውጭ የድጋፍ አጋጣሚ ሳይሆን ወጥ የሆነ፣ ሩቅ የሚያይና ዘርፉን በሚገባ የተረዳ፣ የሚናበብ ተቋማዊ አደረጃጀት ሲኖር መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው አስገንዝበዋል።

በዚህ እሳቤና በመሬት ዘርፉ ዙሪያ የሚታየውን ችግር በመረዳት፣ በተለያየ ጊዜና አጋጣሚ በዘርፉ የሥራ ተሞክሮ ያላቸው ባለሙያዎች ተቋማዊ አደረጃጀቱን ለማሻሻልና ወጥ በማድረግ ሃሳቡን ባልተደራጀና በተበታተነ ሁኔታ ሲያቀርቡት መቆየታቸውንም አስታውሰዋል። በተለያዩ ባለሙያዎች የተደረጉ ጥረቶች መልካም ቢሆኑም፣ ሃሳቦቹ በተለይም ለውሳኔ ሰጭ አካላት ግልጽ በሆነና የችግሩን ጥልቀት ማመልከት በቻለ ሁኔታ የቀረቡ አልነበሩም ብለዋል።

ይህንን ሁኔታ በመረዳትና ዘርፉም ያለበትን የተቋምና አደረጃጀት ተግዳሮት በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲያግዝ ጉዳዩ ያስጨነቀው የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ማህበር የተለያዩ ጠቃሚ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱንም ጠቅሰዋል። ከበርካታ ጥረቶቹ መካከል አንዱና ዋናው የመሬት አስተዳደር ዘርፉ ተቋማዊ አደረጃጀት ያለበትን ሁኔታ መረዳት፣ የሚታይበትን ተግዳሮት መለየትና ሀገራዊ ሁኔታውን ከዓለም አቀፍ ልምዶችና ለተግባሩ ምቹ ከሆኑ መርሆዎች ጋር በማዛመድ ሀገራዊ የምክረ ሃሳብ ሰነድ ማዘጋጀት መሆኑንም አስታውቀዋል።

በዚህም መሠረት የመጀመሪያ የምክረ ሃሳብ ረቂቁን በማዘጋጀትና በዘርፉ ከሚገኙ የተለያዩ ባለሙያዎች ጠቃሚ ግብዓት ሲያሰባስብ ቆይቷል ይላሉ። በዋናነትም የመጀመሪያው ሰነድ ከተዘጋጀ በኋላ ሶስት መድረኮች ላይ በማቅረብ ግብዓቶችን በማሰባሰብና በማካተት የማዳበር ሥራ መሠራቱን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ባለሙያዎች ማህበር አባል እና የጥናት ባለሙያ የሆኑት ዶክተር ዘርፉ ኃይሉ በበኩላቸው ሙያዊ ግብዓት የታከለበት አንድ ወጥ የመሬት አስተዳደር አደረጃጀት መፈጠር አለበት ይላሉ።

በመሬት አጠቃቀም ላይ ቀደም ብሎ የታቀደ ወጥ አሠራር ከሌላ ተገቢውን የመሠረተ ልማት ግንባታ ለማከናወን ተግዳሮት እንደሚሆን ዶክተር ዘርፉ ጠቅሰው፣ ይሄ ቦታ ለመንገድ፣ ይህ አካባቢ ለመኖሪያ፣ ይህ ደግሞ ለፓርክ ይሁን፣ ወዘተ. የሚል የመሬት አጠቃቀም እንዲኖር አንድ ወጥ እና ተመሣሣይ የማኔጅመንት አሠራር ሊኖር እንደሚገባም አስታውቀዋል።

እሳቸውም በዓለም መሬት ትልቅ ሀብት እንደሚመነጭበት ተናግረዋል። ለኢንዱስትሪ እና ለከተማ ማስፋፊያ መሬት በሚወሰድበት ወቅት ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል ሲሉም ጠቅሰው፣ አሁን ባለው ሁኔታ ለሰብል ምርታማነት በጣም ተመራጭ የሆነው መሬት የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ አኳያ ያለው ጠቀሜታ ሳይታይ ኢንዱስትሪ ሲገነባበት ይታያል ብለዋል። በዚህ ሚዛን ሳይታይ በዘፈቀደ የሚሰሩ የመሬት አስተዳደር ክፍተቶች መኖራቸውም ጠቁመዋል።

ጥቅሞቻችን እና ፍላጎታችን ሰፊ ናቸው ያሉት ዶክተር ዘርፉ፤ ከተማ ለማስፋፋት ሲፈለግ ወደ ከተማ የሚገባው መሬት የምግብ ሰብል ሊመረትበት የሚችለውን መሬት እያሳጣና እየቀነሰ ይገኛል ብለዋል። በየዓመቱ ምን ያህል ሄክታር መሬት ወደ ከተማ እንደሚገባ በጀት መያዝ እንደሚገባም አስታውቀው፣ ከምርት ውጭ የሆነው መሬት በምግብ አቅርቦት ላይ ያለው ተፅእኖ መታየትና መጠናት እንዳለበትም አስታውቀዋል።

በተመሣሣይ የዱር እንስሳት ባሉባቸው ፓርኮች አካባቢ ከተሞችን መመሥረት ወይም እርሻ ማስፋፋት እንደማይቻልም ጠቅሰው፣ ከተማውንም እርሻውንም የዱር ብዝሀ ሕይወት እንስሳቱን እንፈልጋቸዋለን ብለዋል። ለእነዚህ ሁሉ በእውቀት ላይ የተመሠረተ የመሬት አጠቃቀም አሠራር መኖር እንዳለበት ጠቁመዋል።

ለምሳሌ የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ ላይ የአፋር እና የከረዩ አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በኩል የሚታየው ወደ ፓርኩ የመግፋት ሁኔታ፣ ለስኳር ፋብሪካ ሸንኮራ አገዳ ለመትከል የሚደረገው መሬት መግፋት በፓርኩ ህልውና ላይ ፈተና መደቀኑን ጠቁመዋል። ይህም ለከብቶች ግጦሽ፣ ለዱር እንስሳት፣ ለኢንዱስትሪ መስፋፋትና ለመሳሰሉት በጥናት ላይ የተመሠረተ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

የበለጸጉት ሀገራት መሬታቸውን ቆጥረው በአግባቡ በመጠቀማቸው ነው እድገት ያሳዩት ያሉት ዶክተር ዘርፉ፣ የዘርፉን ችግሮች ለመፍታት በከተማና ገጠር መሬት አደረጃጀት አዋጆች ላይ የሕግ ማሻሻያዎችን እስከ ማድረግ የሚደረስ ሥራ መሥራትን ይጠይቃል ሲሉም ገልጸዋል። አዋጆችን ወደ አንድ የማምጣት አስፈላጊነትንም ጭምር ጠቁመዋል።

ከፖሊሲ ጋር የተያዙትን በክልሎች የሚታዩ የተዘበራረቁ አሠራሮችንም ወደ አንድ ዘመናዊ አሠራር መቀየር እንደሚገባ አመልክተዋል። ለማሻሻያውም የመጨረሻ ግብዓት መሰባሰቡን የተናገሩት ባለሙያው፣ ከተማ ልማትም ለጉዳዩ ወቅታዊና ተቋማዊ ምላሽ ለመስጠት በ10 ዓመት እቅዱ ላይ ማስቀመጡን አስታውቀዋል።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ሀዘን ሀዘንን እንዳይወልድ

ገርማ መንግሥቴ

"ሀዘን አታብዙ። ሀዘን ሲበዛ ሀዘንን ነው የሚወልደው" የሚል ዘመን የተሻገረ አባባል አለ። አባባሉ "እውነት" ስለመሆኑ ዘመን ጠገብነቱ ብቻ በራሱ ማረጋገጫ ነው።

ከሰው ልጅ ቁጥጥር ውጭ ከሆኑት ባህርያት አንዱ ሀዘን (ማዘን) ነው። ማንም ሰው ወዶ አያዝንም፤ ማንም ሰው፣ አላዝንም ቢልም እንኳን፣ ከማዘን አያመልጥም። መደሰትም እንደዛው ሲሆን፣ በግድ መደሰት እንደ ሌለ ሁሉ፣ በውድ አለመደሰትም አይቻልም። በመሆኑም፣ ሁለቱም ውስጣዊ በመሆናቸው ፈንቃይ ናቸው።

ምንም ሆነ ምን፣ የሰው ልጅ አንድ ማድረግ የሚችለው ነገር ያለ ሲሆን፣ እሱም ምንም ይሁን ምን "መቆጣጠር መቻል" ነው። አዎ፣ ደስታንም ቢሆን ካልተቆጣጠሩትና በአግባቡ ካልያዙት ጦሰኛ ነው። ሀዘንም እንደዛው ሲሆን፣ ቻል ካላደረጉት የሚያስከትለው ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ከመሪር ሀዘን (ትካዜ፣ ቁዘማ፣ ሙሾ . . .ን ይጨምራል) ምንም አይገኝም። ከፈጣሪ በስተቀር፣ እኛ ጸጉር በመንጨትም ሆነ ደረትን በመድቃት ማንንም ከሞት ወደ ሕይወት መመለስ አይቻለንም። በመሆኑም፣ ዝቅ ብለን እንደምንመለከታቸው አስተዋይ ሰዎች ራሳችንን መግዛት ግድ ይለናል።

2016 ዓ.ም ከገባ ወዲህ አንድ ለየት ያለና ሰው ተኮር የሆነ አቢይ ጉዳይ ተከናውኗል። ዝቅ ብለን ታሪካቸውን የምንመለከትላቸው ሰው እንዳሉት "የምናለቅሰው ለሀገራችን ሞት እንጂ፣ ለልጃችን አይደለም" እስከ ማስባል ድረስ የዘለቀ ክስተት ነው።

ሰኞ፣ ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ.ም "የትግራይ ክልላዊ ሐዘን ሦስተኛ ቀን" በሚል ርዕስ ለንባብ የቀረበ ዘገባ "ትግራይ የቀድሞ ተዋጊዎች የህልፈት መርዶ ለቤተሰቦች መነገሩን ተከትሎ ከፍተኛ ሐዘን ላይ ናት። በከተሞች እንቅስቃሴዎች ተገድበዋል፣ በክልሉ ብሔራዊ ሐዘን ከታወጀ ሶስተኛ ቀኑ ላይ ይገኛል። ለወትሮው በሰዎችና ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ፣ በግብይት እንዲሁም ሌሎች ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ትደምቅ የነበረችው መቐለ ዛሬ እንደ ሁልጊዜው አይደለችም።" ይላል።

ሌላው የወቅቱ ዜና ደግሞ የሶስት ቀን (ከጥቅምት 3 - 5 ቀን፣ 2016 ዓ.ም) "ብሔራዊ ሀዘን በታወጀባት ትግራይ፥ በተለያዩ የጦር ግንባሮች ያለፉ የቀድሞ ተዋጊዎች መርዶ ለቤተሰቦቻቸው ተነግሮ ከፍተኛ የሐዘንና ፀጥታ ድባብ ሰፍኖባት ይገኛል።" ይላል።

ለጀርመኑ ዶቸቨሌ ዘጋቢ አስተያየቱን የሰጠው፣ የመቐሌው ነዋሪ ወጣት አማኑኤል ኃይለ "ትግራይ ሐዘን ላይ ናት። በትግራይ የሶስት ቀናት ክልላዊ ሀዘን ታወጀ። ትልቁ ትንሹ፣ ወንዱ ሴቱ ሁሉም ነጠላ ለብሶ፣ እያለቀሰ ነው የምታየው። እኔ በርካታ አብሮ አደጎቼ፣ የሰፈሬ ልጆች፣ አብረውኝ የተማሩ አጥቻለሁ። የትኛውን ሀዘን ደርሰህ የትኛውን መተው እንዳለብህ እስኪጠፋብህ ድረስ በአንድ ጊዜ መርዶው መጥቷል። እንደዚህ ዓይነት ፈታኝ ጊዜ የለም። ለቅሶ በመድረስ ደከምን። አሁን እኔ ዕዳጋዓርቢ ሄጄ የዘመድ ለቅሶ መድረስ ነበረብኝ። ግን እዚህ ያሉትስ ብዬ ተውኩት። ለትግራይ ሕዝብ መፅናናትን ነው የምመኘው።"

ሌላው አስተያየት ሰጪ ዳንኤል መብራህቱ "በርካታ ጓደኞቻችን፣ የዕድሜ እኩዮቻችን፣ በርካቶችን አጥተናል። አሳዛኝ ድባብ ነው ያለው። እናቶች ልጆቻቸውን አጥተው ሲያለቅሱ እንደ ማየት የሚያም ነገር የለም። ብዙ ብርቅዬ ወንድሞቻችን አጥተናል። ትግራይ በየጊዜው በርካቶችን እየገበረች መኖር የለባትም። ያለፈው ይበቃል። ከእኛ ጀምሮ፥ ይህ እንዳይደገም ጥረት ይፈልጋል" ማለቱም ተዘግቧል። "ትግራይ ሐዘን ላይ ናት።" የሚለውም የዚሁ ንግግር አካል ነው።

ለሁለት ዓመት በመንግሥት እና የትግራይ ኃይሎች መካከል የተደረገው ጦርነት፤ በተለይም በሰው ሕይወት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ማድረሱ ሲገለፅ ቆይቷል። በትግራይ ኃይሎች በኩል በውጊያ ግንባሮች ያለፉት ቁጥር ስንት መሆኑ እስካሁን በግልፅ ባይቀመጥም (የተለያዩ አስተያየቶች እንዳሉ ሆነው)፣ የትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ረዳ በሀዘኑ ሳምንት ሰጥተውት በነበረ መግለጫ "ከፍተኛ ኪሳራ" መድረሱ ተነግሯል። ሁለት ዓመት ወደኋላ እንሂድ።

> **"በርካታ ጓደኞቻችን፣ የዕድሜ እኩዮቻችን፣ በርካቶችን አጥተናል። አሳዛኝ ድባብ ነው ያለው። እናቶች ልጆቻቸውን አጥተው ሲያለቅሱ እንደ ማየት የሚያም ነገር የለም። ብዙ ብርቅዬ ወንድሞቻችን አጥተናል. . ."**

"የሕወሓት ቡድን በአፋር ክልል፣ በፈንቲ ረሱ በጋሊኮማ ጊዚያዊ መጠለያ በነበሩ ንፁሃን ዜጎች ላይ የፈፀመውን አሰቃቂ ጭፍጨፋ አስመልክቶ ከዛሬ ጀምሮ ለሶስት ተከታታይ ቀናት (ከነሐሴ 05 /2013 እስከ ነሐሴ 07/2013 ዓ.ም) የሀዘን ቀን እንዲሆን የአፋር ክልል መንግስት አውጇል።" መባሉ የሚረሳ አይደለም።

እንዲህ እንዲህ እያልን ብንቀጥል ነገሩ ሁሉ ቀልድ እስኪመስለን ድረስ ሊገርመን ይችላል። "የሀገሪቱ ሕዝቦች አብደዋል እንዴ፣ የጦርነት ሱስ አለባቸው እንዴ? ምነው መተላለቅ ሥራቸው ሆነ?" ሊያስብለን ሁሉ ይችላል። ወደድንም ጠላንም ግን፣ በሀገራችን እየሆነ ያለው፤ እየተደረገ ያለው፤ መቆሚያ ያልተበጀለት ይሄ ነው።

ሀዘንን በተመለከተ በሀገራችን የነበረውን ታሪካዊ ዳራ እንመልከት፤ ከመሪዎችም እንጀምር።

አፄ ኃይለሥላሴ በልጃቸው ልዕልት ዘነበወርቅ ሞት እጅጉን አዝነው እንደነበረ፤ ለቅሷቸውም ከ"ስቅስቅቅቅቅቅ . . ."ም አልፎ ከቁጥጥራቸው ሁሉ ውጭ ሆኖ ያየ የተመለከታቸውን ሁሉ ሲያስለቅስ እንደነበረ በበርካታ ድርሳናት ውስጥ ተሰንዶ ይገኛል። ምክንያታቸውንም "አሁን፣ ዛሬ በልጄ በዘነበወርቅ ሞት ሀዘን የፀናብኝ ስለ ሶስት ነገር ነው፤ 1ኛው በሕፃንነቷ፣ 2ኛው ባዲስ ሙሽርነቷ፣ 3ኛው ነፍሰ ጡር ሆና ሳትገላገለው በመሞቷ ነው።" በማለት መናገራቸው እንዲሁ የታሪክ እውቅና ተቸሮት በድርሳናት አማካኝነት ለምስክርነት በቅቷል።

"እነዚህ እጅግ የከበዱ ሶስት ነገሮች ባንድ ጊዜ ስለደረሱብኝ ሀዘኔን እያፀናሁ ብቆይ እወድ ነበር፤ ነገር ግን በአንድ ወገን ፅኑ ሀዘን አድርጎ መቆየት ተስፋ የሌላቸውን አሕዛብን መምሰል ነው ተብሎ በመጽሐፍ መከልከሉን ስላወቅሁ፤ በሁለተኛውም ወገን ለእናንተ፣ ለሁላችሁም የጉዳት አብነት (ምሳሌ) ማሳየት የማይገባኝ መሆኑን ስላወቅሁ ሀዘኔን ትቼዋለሁ።" ማለታቸውም እንደዚሁ ስለ ሀገርና ሕዝብ በተጻፉ ድርሳናት (ለምሳሌ፣ የብላታ መርስኤ ሀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ "ዝክረ ነገር" (1942 ዓ.ም)) ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ንጉሡና ንጉሠ ነገሥታቸው በተነገሩ ታሪኮች ላይ ሁሉ ተገቢውን ስፍራ ይዞ እንመለከታለን።

በንጉሡ ጊዜ በተለያዩ ሀገራዊ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሰሩ ወደ ነበሩትና እውቅ ደራሲና ዲፕሎማት ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ (1870 – 1931) እንሂድ።

እራሳቸው ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደሥላሴ "የልቅሶ፣ ዜማ ግጥም፤ ምስጢሩ ከመጻሕፍት ጋት የተስማማ"(1910 ዓ.ም) በሚል ርዕስ ባሳተሙትና በወዳጅ ዘመዶቻቸው አማካኝነት በ2001 ዓ.ም በድጋሚ በታተመው መጽሐፋቸው ላይ "የዚህችኛዋ እትም አጭር መግቢያ" ስር ስለ እሳቸው በሰፈረው ጽሑፍ ላይ "ታላቁ ሰው ህሩይ ሞትን፣ ሀዘንን፣ ልቅሶን በተመለከተ፣ ከነበሩበት ዘመንም ሆነ፣ አሁን ከአለው የሀገራችን ማህበረሰብ ከአብዛኛው በተለየ መልኩ የሚመለከቱበት የራሳቸው የሆነ ፍልስፍና አላቸው። አንዱ፡- 'ለሞተው ወዳጅህ ከምታልቀስ ይልቅ በሕይወት ሳለ የከፋት ሥራ ለሚሰራ ወዳጅህ አልቅስለት' የሚል ነው።" (ገጽ 4 – 5) የሚል ሰፍሮ እናነባለን።

"በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢሮ ከአባቱ ስር ሆኖ፣ ያላንዳች የደመወዝ ክፍያ እናት ሀገሩን በነፃ ያገለገለው፣ ከማይጨው ጦርነትም በኋላ፣ የጥቁር አንበሳን ጀግኖች አርበኞች የተጋድሎ ማህበር ከመሰረቱት አባሎች አንዱ የሆነው ልጃቸው፣ የኬምብሪጅ ምሩቅ ልጅ ፈቃደ ሥላሴ ህሩይ ከቤቱ በጠቋሚ ተወስዶ በየካቲቱ ጭፍጨፋ መገደሉን፣ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በተገኙበት፣ በእንግሊዝ ቤተመንግሥት በተረዱ ጊዜ ምን ነበር የተሰማቸው?" የሚል ጥያቄ ከሰፈረ በኋላ፡-

"እንኳን ለተወለደው-ለተዛመደው፣ እንኳን ለቀረበ-ላወቀው ይቅርና ፎቶግራፉን [ፎቷቸው አለ] ብቻ እንኳን፣ እንዲሁ ላየው፣ የሚያሳሳ፣ አንጀት የሚበላ፣ ይህ መለሎ ወጣት፣ ሕይወቱ በአጭር መቋጨቷ የሚያስከትለው መሪር ሀዘን፣ እንዳለ ይቆይና በፋሽስቶች እብሪትና ጥጋብ በከባድ ጭካኔ፤ ሊያውም በግፍ የመገደሉ ነገር ታውሷቸው ሀዘናቸውን አላከበዱትም፤ እንባቸው ፈንቅሎ እንዲወጣ እንኳን እሺ-በጅ አላሉትም፤ የእንጉርጉሮ ስንኝም አልቋጠሩለትም። ሀዘናቸውን የገቱት በአንዲት ዘለላ እንባና በአንዲት ዓረፍተ ነገር ብቻ ነበር፤ 'የምናለቅሰው ለሀገራችን ሞት እንጂ፣ ለልጃችን አይደለም' " ተብሎ ተጽፎላቸው እናገኛለን።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ሀዘን ስለደጋገማቸው ህሩይ የሚከተለውም ሰፍሮ ይገኛል።

"ወ/ሮ አምሳለ ህሩይ የተባለች የመጨረሻ ልጃቸውን በ11 ዓመትዋ ለትምህርት ወደ አውሮፓ ልከዋት ትምህርትዋን አጠናቅቃ ከተመለሰች በኋላ ትዳር ይዛ በወሊድ ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ ገና የት ትደርሳለች ብለው ያሰቧት ልጃቸው እንዲህ ባጭሩ በመቀጨትዋ ለሀዘኑ፣ ለልቅሶው አልተንበረከኩለትም፤ ሀዘኑንም ልቅሶውንም ባጭሩ ገትተውታል።

"ከቀብር መልስም ባደረጉት ንግግር፣ እንደ ኢዮብ 'እግዚአብሔር ሰጠ፤ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።' ካሉ በኋላ ስለ አቃበራችሁኝ አመሰግናችኋለሁ፤ ቀባሪ-አቃባሪ አያሳጣችሁ። ሀዘኑም፣ ልቅሶውም እዚሁ አብቅቷል፤ ስለ ሀዘኑ ቤት አንቀመጥም፤ የሰልስት ልቅሶም የለንም፤ ስለዚህ አላደክማችሁም፣ ወዳጆቼ ከዚሁ እንድትሰናበቱልኝ እለምናችኋለሁ።" በማለት መናገራቸው ተሰንዷል።

በመጨረሻም፣ ነገሩ ሁሉ፡-

**የገደለው ባልሽ፤**
**የሞተው ወንድምሽ**
**ሀዘንሽ ቅጥ አጣ፣**
**ከቤትም አልወጣ።**

እንደተባለው ነው - የእኛ ነገር። ሚችም ገዳይም የአንድ ቤት ሰዎች ሆነውብን ተቸግረናል። በሶስቱ የአፋር ሀዘን ቀናት የተቸገርነው ይህንኑ ሆኖ ሳለ፣ አሁንም፣ በሶስት የትግራይ የሀዘን ቀናት የተቸገርነው በተመሳሳይ የላይኛውን፣ የአልቃሿን ግጥም የሚያስታውስ ነው። በመሆኑም ዘላለማዊ በሆነ መልኩ "መቸም መቸም አይደገምም" ካላልን እና በቃላችን ካልፀናን በስተቀር፣ እየገደልንና ተገዳደልን፤ ለሟች ቤተሰብም ". . . የሞተበት ሰርተፊኬት" እየሰጠን መቀጠላችን ነው።

እዚህ ላይ ምህላን በተመለከተ አንድ ነገር ብሎ ማለፍ የሚገባ ሲሆን፣ እሱም "መቸም መቸም አይደገምም" የሚለው ነው።

የአብዮቱን መፈንዳት ተከትሎ፣ በቀይ እና ነጭ ቀለሞች አሳብበን መተላለቃችንን መቸም ላለመድገም በመማል የሰማእታት ሀውልት ማቆማችን፣ አቁመንም እላዩ ላይ "መቸም መቸም አይደገምም" ብለን መጻፋችን የሚታወስ ብቻ አይደለም የሚታወቅ ነው። ይሁን እንጂ "መቸም መቸም አይደገምም" ባልንበት አንደበታችን መፅናት አቅቶን ስሙን እየቀያየርን መተላለቃችንን አላቆምንም። ጭራሽ ወደ ለየለት ጦርነት ውስጥ በመግባት በሚሊዮኖች እንዲያልቁ እያደረግን እንገኛለን። ዛሬም ድረስ። ታዲያ፣ ይህ የጤና ነውን???

ምንም ሆነ ምን፣ ያለን እድል አንድ ነው። ሀዘንተኞች ከላይ እንደተመለከትናቸው ሁለት አንጋፋ ሰዎች ሁሉ፣ ራሳችንን ተቆጣጥረን ሀዘናችንን ቻል ማድረግና ወደ መደበኛ ሕይወታችን መመለስ ነው። ሌላውም፣ በትግራይ ክልል ሀዘኑን አስመልክቶ በተሰጠው የሀዘን መግለጫ "ለሁሉም የትግራይ ሕዝብ መጽናናቱን ይስጥህ፣ መጽናናቱን ይስጠን። የልጆቻችን እና ወንድሞቻችን መስዋዕትነት የሁላችንም መስዋዕትነት ነው። ይህ ዓይነቱ አሳዛኝ ሁኔታ እንዳይደገም የፖለቲካ አመራሩም፣ ሁሉም ራሱን መፈተሽ አለበት።"

መቸም በየትኛውም የከፋ ሀዘን ውስጥ ድምፃቸው ጎልቶ የሚሰማው፣ ሀዘናቸው ጠልቆ የሚጎዳቸው . . . እናቶች ናቸውና በ"የራሔል እንባ" መፅናናትን እንመኝላቸው፤

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የኀዘን የልቅሶና የጩኸት ድምጽ በራማ ተሰማ፤ ራሔል ስለ ልጆችዋ አለቀሰች፤ የሉምና ስለ ልጆችዋ መጽናናትን እንቢ አለች። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ድምጽሽን ከለቅሶ ዓይኖችሽንም ከእንባ ከልክይ፤ ለሥራሽ፤ ዋጋ ይሆናልና፥ ይላል። እግዚአብሔር፤ ከጠላትም ምድር ይመለሳሉ። ለፍጻሜሽም ተስፋ አለ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ ልጆችሽም ወደ ሀገራቸው ይመለሳሉ።» ኤር 36፥15።

ቅዳሜ ጥቅምት 3/ 2016 ጀምሮ በትግራይ ክልል የታወጀውን የሀዘን ቀን እና የመርዶ ሥነ ሥርዓት ተከትሎ፤ አዲስ አበባ የሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት እና ፖለቲከኞች በሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ሕይወታቸውን ላጡ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የጸሎት እና የጧፍ ማብራት ሥነ ሥርዓት አከናውነው እንደነበር ይታወሳል። በሥነ ሥርዓቱ ላይም የሰባት ሀገራዊ እና ክልላዊ ፓርቲዎች አመራሮች እና አባላት ተገኝተው ሀዘናቸውን ገልጸዋል። ይህ መሆን ያለበትና ሁሉም ሊያደርገው የሚገባ ጉዳይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ሀዘኑ የሁላችንም ስለመሆኑ ጥሩ ማሳያ ነው።

በእለቱ ከተገኙት አንዱ የሆኑት፣ የመኢአድ ሊቀመንበር አቶ ማሙሸት አማረ "የዛሬው ቀን ምን ተብሎ እንደሚሰየም ባላውቅም፤ ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ ላይ ላለቁት ወገኖቻችን፣ አጠቃላይ እንደ ሀገር በወደቁት ወንድሞቻችን የመከላከያ ሠራዊት ጭምር እንዳናስበው፣ የጋራ እንዳናደርገው ሌላ ደግሞ ችግር አለብን። ሌላ ችግር ውስጥ ነው ያለነው። ከአንዱ ችግር ወደ [ሌላ] ችግር ነው እንጂ፤ ከአንዱ ችግር ወደ ተሻለ ነገር መሸጋገር አልቻልንም [. . .] ይሄ ሁሉ ሕይወት፣ ይሄ ሁሉ ዋጋ የተከፈለበት ዓላማው ምንድነው? ግቡ ምንድነው? በውጤቱስ ምን ተገኘ? ብለን ብናስብ፤ ምንም የለም። ዜሮ እንኳ አይሆንም" ያሉትም ሊዘለል የሚገባው አይደለም።

በእለቱ (እሑድ ጥቅምት 4/ 2016 ዓ.ም) የመርሃ ግብሩ ተሳታፊዎች ባስተላለፉት መልዕክት፤ በትግራይ ክልል የደረሰው ሀዘን የጋራ መሆኑን ጠቅሰዋል። በሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት ሕይወታቸውን ያጡ የአማራ እና የአፋር ዜጎችንም ጭምር ለማሰብ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሀዘን ቀናት ሊታወጅ ይገባ እንደነበርም ተናግረዋል። በኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት የነበረው "የእርስ በእርስ መገዳደል" በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በሌሎች ቦታዎች መቀጠሉ የሚያሳዝን እና መፍትሔ ሊበጅለት የሚገባ እንደሆነም አሳስበዋል። ይህም ሌላው የሀዘኑ የጋራ መሆን አመላካች ነውና ተሳታፊዎቹ ሊመሰገኑ ይገባል።

በወቅቱ "ኢትዮጵያ ኢንሳይደር" ለንባብ እንዳበቃው፣ በመርሀ ግብሩም "ሁላችንም ያለፈውን መመለስ አንችልም፤ ግን ከዚህ በኋላ የተሻለ ሥርዓትን በመገንባት ሕዝቡን መካስ መቻል አለብን።" የሚለው ሃሳብ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ሲንሸራሸር መቆየቱ፤ "ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ለገባችበት ውድቀት ተጠያቂው ሕዝቡ ሳይሆን ፖለቲከኞች መሆናቸው፤" "የፖለቲካ ኤሊቱ" ነው የሚለው የውይይቱ ማዕከላዊ ነጥብ ሆኖ የነበረ መሆኑ ስለ ወደፊቷ ኢትዮጵያ ሲባል ተስፋን የሚያጭር ነው።

በመጨረሻም፣ ሀዘኑ የሁላችንም ነውና ነፍስ ይማር እንላለን። ለወዳጅ ዘመዶች፣ በአጠቃላይም ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ መጽናናትን እንመኛለን። ይህንን ስንል ግን አሁን እየሆነ ያለው፤ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ባህልና ወግ ያልሆነው መገዳደልም እንዲቆም፤ ፊታችንን ከጦርነት ይልቅ ወደ ሰላም እንድናዞር በመማፀን ጭምር ነው።

# ማህደረ ጤና

## ለሕክምናው አስተዋፅኦ ያደረገ ፕሮግራም

**አስናቀ ፀጋዬ**



**በቀዶ ሕክምና ደህንነት ታካሚዎችን ከኢንፌክሽንና ከሞት መታደግ ይቻላል**

የሰዎችን ጤና አደጋ ውስጥ ከሚከቱ ዋነኛ ምክንያቶች መካከል አንዱ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ቀዶ ሕክምና አለማድረግ ነው። በዋናነት ደግሞ የቀዶ ሕክምና ክፍሎች ከኢንፌክሽን የጸዱ አለመሆን፣ በተደራጁ የሕክምና ግብአቶችና የቀዶ ሕክምና ባለሞያዎች አለመሟላትና የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸውን የደህንነት ቼክ ሊስቶች ተከትሎ ቀዶ ሕክምና አለማድረግ ህመምተኞችን ለኢንፌክሽን ከማጋለጥ በዘለለ ለተወሳሰቡ የጤና ችግሮች ሲያጋልጣቸው ይስተዋላል። ይህ ችግር ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ገና በማደግ ላይ ባሉ ሌሎች ሀገራት በስፋት ይታያል። ይህንኑ ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ "ላይፍ ቦክስ" የተሰኘ ምግባረ ሰናይ ድርጅት አንድ ፕሮግራም ይዞ ብቅ ብሏል።

ዶክተር አሰፋ ተስፋዬ በሙያቸው ሀኪም ሲሆኑ በሕብረተሰብ ጤና የማስተርስ ዲግሪ አላቸው። በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል የክሊኒካል አስተዳደርና ጥራት ክፍል ኃላፊ ናቸው። ላይፍ ቦክስ በተሰኘው ድርጅት ውስጥ ደግሞ ‹‹ክሊን ከት›› የተሰኘው ፕሮግራም ክሊኒካል መሪ ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት ‹‹ላይፍ ቦክስ›› ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሲሆን ደህንነቱ የተጠበቀ ቀዶ ሕክምና ላይ ትኩረት አድርጎ ይሰራል። ደህንነቱ የተጠበቀ ቀዶ ሕክምና እንዲኖር የዓለም ጤና ድርጅት የደህንነት ቼክ ሊስት መሳሪያ የፈጠሩ ሰዎች የመሰረቱት ድርጅትም ነው። በተለይ ‹‹ላይፍ ቦክስ›› ኢትዮጵያ ውስጥ ‹‹ክሊን ከት›› የተባለውን ፕሮጀክት ሀሳቡን ከመጠንሰስ ጀምሮ እ.ኤ.አ በ2016 ተግባራዊ እንዲሆን በማድረግ ይታወቃል። በጊዜው ፕሮጀክቱ በሙከራ ደረጃ በአምስት ሆስፒታሎች ላይ ተግባራዊ ተደርጓል። ከነዚህ ሆስፒሎች ውስጥ ደግሞ ቀዳሚው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ነው።

በመቀጠልም፣ ጥቁር አንበሳን ጨምሮ በምኒልክ፣ ቅዱስ ጴጥሮስና በአዲስ አበባ አጎራባች በሚገኘው ፍቼ ሆስፒታሎች ተግባራዊ ሆኗል። በተጨማሪም ፕሮግራሙ በአብዛኛው በአዲስ አበባ በሚገኙ ሌሎች ሰባት ሆስፒታሎች ውስጥ ተግባራዊ ተደርጓል። ከአዲስ አበባ ውጪ የሚገኙት እንደነ ሕይወት ፋና፣ አደሬ፣ ወልቂጤና ሌሎች ሆስፒታሎችም የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ባጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ36 በላይ በሚሆኑ ሆስፒታሎች ውስጥ ፕሮግራሙ ተግባራዊ ሆኗል። ይህ ሲባል ኢትዮጵያ የፕሮግራሙ መነሻ ሆነች እንጂ በውጪ ከሰባት ሀገራት በላይ የፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። ከነዚህ ውስጥ ላይቤሪያ፣ ማዳጋስካር፣ ቦሊቪያ፣ ማላዊ፣ ሕንድና ኮትዲቯር ይጠቀሳሉ። ፕሮግራሙን የማስፋት ስራም በአሁኑ ጊዜ በደምብ እየተሰራ ይገኛል።

‹‹ክሊን ከት›› ፕሮግራም ላይፍ ቦክስ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እንደ ዋና ምሰሶ ተደርጎ የሚወሰደው ትልቁ ፕሮጀክት ነው። ሆኖም ከዚህ ፕሮግራም ውጪ ሌሎችም በላይፍ ቦክስ የሚከናወኑ ስራዎች አሉ። የዓለም ጤና ድርጅት እ.ኤ.አ በ2008 የደህንነት ቼክሊስትን ለዓለም ሲያስተዋውቅ ላይፍ ቦክስን የመሰረቱ ሰዎች የደህንነት ቼክሊስቱን በማበልፀግ ሂደት ተሳትፎ ነበራቸው። ይህን የደህንነት ቼክሊስት መሳሪያ እንዴት በሁሉም ሀገራት ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል ከሚል መነሻም ነው እንዲበለፅግ የተደረገው። ከዛ በኋላ ደግሞ ይህን የደህንነት ቼክሊስት በተለይ አቅማቸው ደከም ባሉ ሀገራት ውስጥ እንዴት ማድረስ ይቻላል የሚል ውይይት ነበር። ከዚህ ሂደት በኋላ ነው ክሊን ከት ፕሮግራም ኢትዮጵያን ጨምሮ በላይቤሪያ፣ ማዳጋስካር፣ ቦሊቪያ፣ ማላዊ፣ ሕንድና ኮትዲቯር ተግባራዊ መሆን የተጀመረው።

ዶክተር አሰፋ እንደሚያብራሩት የላይፍ ቦክስ ትልቁ ተልእኮ ደህንነቱ የተጠበቀ ቀዶ ሕክምና እንዲኖር ማድረግ ነው። ይህን ተልዕኮ ለማሳካት በርካታ ባለሞያዎች እንዲሰለጥኑ ሙከራ ተደርጓል። በዚህም ከ14ሺህ በላይ የሚሆኑ የሕክምና ሙያተኞች፣ የቀዶ ሀኪሞች፣ የሰመመን ባለሙያዎችና በቀዶ ሕክምና ክፍሎች ውስጥ የሚሰሩ ነርሶች ስልጠና ወስደዋል። ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ በሆኑ ሀገራት ከ35ሺህ በላይ የሚሆን /pulsoksym-etry/ በቀዶ ሕክምና ወቅት በታካሚው ደም ውስጥ ምን ያህል የኦክስጂን መጠን እንዳለ የሚለካ መሳሪያ በነፃ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ይህም ደህንነቱ የተጠበቀ የቀዶ ሕክምና እንዲኖር በማስቻል ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ከ180 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕሙማንም የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በዚሁ ክሊን ከት ፕሮግራም አማካኝነት የቀዶ ሕክምና ኢንፌክሽን አደጋን በ34 በመቶ መቀነስ ተችሏል። በተለይ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ያሉ ስድስት የኢንፌክሽን ቅድመ መከላከል እርምጃዎች፣ ማለትም የእጅ ንፅህናና መጠበቅ፣ የቀዶ ሕክምና ክፍል ጨርቆች ንፅህና፣ የቀዶ ሕክምና መሳሪያዎች ፅዳት፣ ኢንፌክሽንን ለመከላከል ለታካሚዎች የሚሰጡ መድሃኒቶች ደህንነትና አሰጣጥ እና ሌሎችም የህሙማንን ጤና ከማሻሻልና በኢንፌክሽን ምክንያት ሊመጣ የሚችለውን የጤና እክል በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ለማየት ተችሏል።

የቀዶ ሕክምና ደህንነት ቼክሊስት እንደ ሀገር በሁሉም ጤና ተቋማት ውስጥ ከቀዶ ሕክምና በፊት እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ የሚታይ እንዲሆን ተደርጓል። ጤና ሚኒስቴርም የቀዶ ሕክምና ደህንነት ቼክሊስት አጠቃቀም ያለበትን ደረጃ በየወሩ ይከታተላል። ከላይፍ ቦክስ ውጪ ያሉ አጋር ድርጅቶች በሚሰሯቸው ስራዎች ደህንነቱ የተጠበቀ ቀዶ ሕክምና እንዲኖርና በማድረግና ደህንነቱ ካልተጠበቀ ቀዶ ሕክምና ጋር በተያያዘ የሚመጡ ኢንፌክሽኖችን በመቀነስ ረገድ የራሳቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ዶክተር አሰፋ እንደሚገልፁት ክሊን ከትን የመሰሉ ፕሮግራሞች ከዓለም ጋር የሚያቀራርቡ ናቸው። ለአብነትም የዓለም ጤና ድርጅት የደህንነት ቼክ ሊስት ሲበለፅግ በኢትዮጵያ በሚተዋወቅበት ጊዜ በብዙ የሕክምና ባለሙያዎች ዘንድ እንደ ተጨማሪ ስራ ተደርጎ ነበር የሚወሰደው። ይሁንና ዛሬ ይህ የደህንነት ቼክ ሊስት ከቀዶ ሕክምና በፊት በሁሉም ጤና ተቋማት ውስጥ እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ የሚታይ ነው። ይህም በተለይ ሕሙማን ለከፋ የጤና ችግርና ለአላስፈላጊ ኢንፌክሽኖች እንዳይጋለጡ ከመከላከል አንፃር ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፤ እያበረከተም ይገኛል።

በርካታ ታካሚዎችም ደህንነቱ የተጠበቀ የቀዶ ሕክምና አገልግሎት እንደማያገኙ ይታወቃል። የቀዶ ሕክምና አገልግሎት ተደራሽነትም ውስን ነው። የቀዶ ሕክምና እድል ቢገኝም ደህንነቱ የተጠበቀ የቀዶ ሕክምና አገልግሎት ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። አደጋውም የዛኑ ያህል ከፍ ያለ ነው። እንደ ሀገርም ከቀዶ ሕክምና ጋር በተያያዘ የሚከሰቱ በርካታ ችግሮች መኖራቸው ሲነገር ይሰማል። ከዚህ በተቃራኒ ባደጉት ሀገራት የቀዶ ሕክምና ደህንነት ቼክ ሊስት በአግባቡ ስራ ላይ ይውላል፤ ግዴታም ነው። በኖርዝ ካሮላይና ላይ በተሰራ ጥናት በርካታ ሆስፒታሎች በጥናቱ ተሳትፈው የቀዶ ሕክምና ደህንነት ቼክ ሊስት በአግባቡ ተግባራዊ ያደረጉ ሆስፒታሎች የቀዶ ሕክምና ቦታ ኢንፌክሽኖችንና በዚህ ምክንያት የሚከሰተውን ሞት በከፍተኛ ደረጃ መቀነሳቸው ተረጋግጧል። ይህን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት እንደ ላይፍ ቦክስ አይነት ድርጅቶች ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ከቀዶ ሕክምና ጋር በተያያዘ እንደ ሀገር በርካታ ችግሮች አሉ። ለምሳሌ የሕክምና ባለሙያዎች የሚወስዷቸው ስልጠናዎች አንዳንድ ጊዜ ልክ አይደሉም። የቀዶ ሕክምና ክፍል ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች እንዴት መስራት እንዳለባቸው ቀጥተኛ የሆነ ትምህርት አይሰጣቸውም። ከዚህ አንፃር የላይፍ ቦክስ አንዱ ምሰሶ የጋራ ስራና ኮሚዩኒኬሽን ነው። ይህ ማለት በቀዶ ሕክምና ክፍል ውስጥ የሚሰራ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ፣ የሰመመን ባለሙያ፣ ነርሶች፣ የፅዳት ባለሙያዎች እንደ ቡድን መስራት አለባቸው። እንዲህ አይነት ትምህርቶች በመደበኛው ትምህርት ላይ አምብዛም አይታዩም። ይህን ሁኔታ ለመቀየር ላይፍ ቦክስ ይዞት የመጣው የጋራ ስራና ኮሚዩኒኬሽን ስልጠና ትልቅ ውጤት አምጥቷል።

ከዚህ ውጪ ግን ከቀዶ ሕክምና መስጫ ተቋማት መሰረተ ልማት ጋር በተያያዘ ሰፊ ችግር እንዳለ ይታወቃል። ለምሳሌ የቀዶ ሕክምና መስጫ ክፍሎች ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ላይሰሩ፤ ወይም የሚፈለገውን ግብአት ላያሟሉ ይችላሉ። ከዚህ አኳያ ላይፍ ቦክስ በጣም ቀላል የሚመስል ነገር ግን ደግሞ ለቀዶ ሕክምና በጣም አስፈላጊ የሆኑ የpulsoksymetry መሳሪያዎችን በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለሆኑ ሀገራት በነፃ አሰራጭቷል። አሁን ደግሞ ባደጉት ሀገራት እንደቀላል የሚታይ፣ ነገር ግን፣ እንደ ሀገር በበርካታ ጤና ተቋማት ውስጥ የማይገኘውን capnography የተሰኘ መሳሪያ ከነስልጠናው በነፃ እየሰጠ ይገኛል። ይህም ከቀዶ ሕክምና ጋር በተያያዘ ያለውን ችግር በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ውጤት እያመጣ ነው።

በተጨማሪም በላይፍ ቦክስ የሚሰሩ የፐሮሰስ ዲዛይን ስራዎችም አሉ። ማለትም የቀዶ ሕክምና ፍሰቱ ምን መምሰል እንዳለበት፣ ታካሚዎች እንዴት አድርገው መግባት እንዳለባቸው፣ በየትኛው መንገድ ነው ቅድመ ሁኔታዎች ከተሰሩ በኋላ የቀዶ ሕክምና መሳሪያዎች ሊወጡ የሚችሉት የሚሉና ሌሎችም ሰፋ ያሉ የዲዛይን ስራዎችን ይሰራል። ለምሳሌ የካቲት 12 እና አለርት ሆስፒታሎችን መውሰድ ቢቻል የቀዶ ሕክምና መሳሪያዎች የሚጓጓዙባቸውን ነገሮች እንደላይፍ ቦክስ ዲዛይን ተደርገው ፖሊሲ የተደረገባቸው አሉ።

የባዮ ሜዲካል ባለሙያዎች ምንም እንኳን ስልጠና ወስደው እንደ ሀገር ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቢመረቁም ተግባራዊ የሆነ እውቀትና መፍትሄ መስጠት ላይ ክፍተት እንዳለባቸው በማየት ላይፍ ቦክስ ለባዮ ሜዲካል ባለሙያዎች ጠንካራ ስልጠናዎችን ሰጥቷል። ለዚህ መነሻ የሆነውም ቀዶ ሕክምና የሚሰራባቸው እቃዎች ማፅጃ ማሽኖች ብልሽት ማጋጠም ነው። እነዚህን መሳሪያዎች ለመጠገንና መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት አዲስጡ ተደርጓል።

ዶክተር አሰፋ እንደሚሉት በቀዶ ሕክምና ደህንነት ዙሪያ የሚሰራው ስራ በላይፍ ቦክስ ብቻ የሚሰራና የሚቀጥል አይደለም። በላይፍ ቦክስ በኩል የሚመጡ ሀሳቦችም የፕሮጀክት ሀሳብ ብቻ ሆነው መቅረት የለባቸውም። ፕሮጀክቶቹ እንደ ሀገር ለቀዶ ሕክምና ደረጃ ሆነው መቅረብ የሚገባቸውና ለሁሉም ጤና ተቋማት ተደራሽ መሆን ያለባቸው ናቸው። በቀጣይም በርካታ ታካሚዎችን ለመርዳትና ሕክምና ባለሙያዎችንም ለማብቃት አሁን ያለው ከአጋር ድርጅቶችና ከጤና ሚኒስቴር ጋር ያለው ቅንጅት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያውያን መልክ የሚገለጥበት በአል - ጥምቀት

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

በኦርቶዶክስ እና በካቶሊክ ክርስቲያን አማኞች ዘንድ በየአመቱ ጥር ıı የሚከበረው በዐለ ጥምቀት፤ ምዕመኑ አምላኩን በአደባባይ በጋራ የሚያመሰግንበት ከዘጠኙ የጌታ በአላት መካከል አንዱ ነው። የበአሉ ታሪካዊ ዳራም ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሃንስ እጅ መጠመቁን የሚያመላክት እና ሰው ከውሀ እና ከመንፈስ ካልተጠመቀ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም የሚለው መጽሀፍ ቅዱሳዊ መልዕክት ያለው ሆኖ እናገኘዋለን።

እየሱስ በዮሀንስ እጅ በዮርዳያኖስ ወንዝ ለምን ተጠመቀ? ብለን ስንጠይቅ ሶስት አንኳር መልሶችን እናገኛለን። የመጀመሪያው ምስጢረ ስላሴን (አንድነቱን ሶስትነቱን) ሊያስተምረን ነው። በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ደቀ መዝሙሬ አድርጓቸው ከሚለው መጽሀፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮት ጋር የሚዛመድ አንድምታ ያለው ነው። ሁለተኛው ከትህትና እና ከአርዐያነትን አንጻር የሚቃኝ ነው። የጌታን የትህትና አጽናፍ ከውልደቱ የምናውቀው ቢሆንም በሌሎች አስተምህሮቶች ላይም የምናገኘው ነው። በከብቶች በረት ተወልዶ ክብርና ጌትነት ምንም እንደሆኑ አሳይቶናል። በታናሹ በዮሀንስ እጅ መጠመቁም ለዚህ ነው።

በስተመጨረሻ የምናገኘው ጥምቀትን ይባርክልን ዘንድ መጠመቁን ነው። ይሄ የሚያሳየን ጥምቀት በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለውን ውርስ እና ቁርኝት ነው። በእግዚአብሄር የሚያምኑትን ሁሉ የእግዚአብሄር ልጅነት ሰጣቸው ተብሎ እንደተጻፈ የእየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቅ ከላይ ባየናቸው ሶስት በኩር አላማዎች ምክንያት እንደሆነ ከማመን ባለፈ የጥምቀትን በአል ዓላማ አያይዘን መረዳት እንችላለን።

ጥምቀት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እና ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያናት ከሚያከብሯቸው የአደባባይ በዓላት መካከል አንዱ ነው። እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ትርጓሜ ጥምቀት የሚለው ቃል "ማጥመቅ፣ መጠመቅ፣ አጠማመቅ፣ ጠመቃ፣ የማጥመቅና የመጠመቅ ስራ፣ ሕጽበት፣ በጥሩ ውሀ የሚፈጸም" ሆኖ ይፈታል። በቃሉ ስርወ መነሻ ተመርተን የጥምቀት በአልን ዓላማና ተልዕኮ መገንዘብ ይቻላል። ራሳችንን ለፈጣሪ የምናቀርብበትና ፈጣሪንም ወደራሳችን የምናቀርብበት የንጽህናና የጽድቅ በአል ብለን ልንወስደው እንችላለን።

ከዋናው በአል አንድ ቀን ቀደም ብሎ የሚከበረው የከተራ በዓልም ሌላው የጥምቀት በአል አካል ነው። ከተራ "ከተረ" ወይም ደግሞ "ገደበ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የመጣ ሲሆን፤ የዋናው የጥምቀት በአል ዋዜማ ነው። በከተራ እለት በሕብረ ዝማሬ ያጌጡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች ክብረ እግዚአብሄር ታቦተ ሕጉን አጅበው ወደ ጥምቀተ ባህሩ የሚተሙበት እለት ነው። ይህ እለት ምዕምናን፣ ዘማሪያን፣ ካህናት በዝማሬና በሽብሻቦ ለአምላካቸው ምስጋና የሚያቀርቡበት እለት ነው።

ከገና በአል ቀጥሎ የሚከበረው ጥምቀት ከክርስቶስ መወለድ ቀጥሎ በአማኙ ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሀይማኖታዊ በአል ነው። መንፈሳዊ አንድምታውን ስንቃኘው በእግዚአብሔርና በሰው ልጆች መካከል ያለውን የመፈጠር ዓላማ አጉልቶ የሚያሳይ የምስጋናና የአንድነት በአልም ሆኖ እናገኘዋለን።

በአሉ ፈጣሪ የሚከብርበት፣ ህዝበ ክርስቲያኑ ደግሞ ተባርኮና ተቀድሶ በአዲስ ማንነት ወደነገ የሚሄድበት እለት ነው። ለሌሎች ፍቅር የምንሰጥበት፣ በፍቅርና በይቅርታ ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር የምናብርበት የመጠመቅ እለት ነው። በየትኛውም ሚዛን ላይ ቢቀመጥ ጥምቀት ከዚህ የተለየ አከባበር አይኖረውም።

ሰላምና መንፈሳዊነት የአንድ እጅ መዳፍና አይበሉባ ናቸው። በአንድ እጅ ላይ የበቀሉ መዳፍና አይበሉባ አንዱ ያላንዱ ታሪክ እንደሌላቸው ሁሉ እንዲህ ያሉ መንፈሳዊ በአላትም ከዓላማና ከመነሻቸው አንጻር ይሄን እውነታ የሚጋሩ ናቸው። ሰላም የማይሰበክበት በአል መንፈሳዊ ነው ሊባል አይችልም።

> **መ**ንገድ ላይ የታሸጉ ውሀዎችን በማስቀመጥ፣ የተራቡ ካሉ እህል የሚቀምሱበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ እንዲያርፉና እንዲበረቱ መልካም መስተንግዶ በማድረግ አብሮነታቸውን የሚገልጹበትን እውነታ በደማቅ ማስታወስ ያስፈልጋል

መንፈሳዊነት ስረ መሰረቱ ሰላምን መስበክ፣ አብሮነትን ማነጽ ነው። ጥልና ክርክርን በስመ እግዚአብሔር መኮነን፣ ጥላቻና መለያየትን መሻር ነው። ከዚህ ረገድ የሚነሳ መንፈሳዊነት በፈጣሪም ዘንድ ቅቡልነትን እንደሚያገኝ ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

ጥምቀት የሁሉም ኢትዮጵያውያን በአል ነው። የዓለም የቅርስና የባህል ተቋም በቅርስነት ሲመዘገብ ከአደባባይ በአልነቱ ጎን ለጎን የሕዝብ በአል መሆኑን በማመን ነው። ይህ እለት ኢትዮጵያውያን የሚጠያየቁበት፣ የሚመሰጋገኑበት፣ የሚመራረቁበትም ጭምር ነው። በተለይ ሙስሊሙ ለክርስቲያን ወገኑ በአል ድምቀት አብሮ መንገድ የሚያጸዳበት፤ የታቦታት ማደሪያዎችን የሚሰራበትና የሚጸዳበት፤ እንኳን አደረሰህ አደረሰሽ የሚልበት፣ የሚተቃቀፍበት እለት ስለሆነ በአሉ ለኢትዮጵያውያን ልዩ ነው ያስብላል።

ይሄን እውነታ የሚያጠነክሩ በየዓመቱ በጥምቀት በአል ላይ የሚስተዋሉ አንድ ሁለት ምስክሮችን ላስታውሳችሁ። ጥምቀት የክርስቲያኖች ብቻ እንዳይደለ በተግባር ያሳዩ የሌላ ሀይማኖት ተከታዮች በጥምቀት በአል ላይ ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው ጋር በመደባለቅ ክብረ በአሉን ከማድመቅ ጎን ለጎን ታቦት ሲሸኙ እንደሚታዩ ማስታወስ ይቻላል። ሌላው በየዓመቱ የጥምቀት በአል በመጣ ቁጥር ታቦት በሚሄድበት መንገድ ላይ ምንጣፍ እያነጠፉ ከኦርቶዶክስ ወንድሞቻቸው ጎን የቆሙ ብዙ የሌላ እምነት ተከታዮች መኖራቸውም እሙን ነው።

በጣም የሚደነቀውና በኢትዮጵያ የሀይማኖት ቀለም ውስጥ ገኖ የወጣው ለዚህ ነጻ ሀሳብም እንደ ዋና የሰላም ምልክት ሊወሰድ የሚችለው ቀጥሎ የምነግራችሁ ፍሬ ነገረ ነው። እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ከአንድ አጥቢያ ታቦት ይዘው ወደጥምቀተ ማደሪያ ሲሄዱ በዝማሬና በውዳሴ ታጅበው በእግር ጉዞ ነው። ጉዞው ረጅም ሊሆን ይችላል። በዚህ ጉዞ ውስጥ መራብ መጠማት፣ ድካምና የመሳሰሉ ስጋዊ ዝለቶች መኖራቸው ግድ ነው። ምዕመኑ ታቦት ሲሸኝ ረጅም መንገድ እንደሚሄድ የተረዱ ሙስሊም ወንድሞቻቸው ግን ይሄን የወገኖቻቸውን ድካም ዝም ብለው አያዩትም።

መንገድ ላይ የታሸጉ ውሀዎችን በማስቀመጥ፣ የተራቡ ካሉ እህል የሚቀምሱበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ እንዲያርፉና እንዲበረቱ መልካም መስተንግዶ በማድረግ አብሮነታቸውን የሚገልጹበትን እውነታ በደማቅ ማስታወስ ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር አብሮ ሊነሳ የሚገባው በአንዱ መንፈሳዊ በአል ላይ የሌላው እምነት ተከታይ የሚያደርገው የኢትዮጵያዊነት መረዳዳት ባህል ነው።

ሌላም የኢትየጵያውያንን ጌጥ እንጥቀስ ካልን ተጠቃሽ እውነት አናጣም። ከሕዝበ ክርስቲያኑ ለምነው መስኪድ ያሰሩ መነኩሴ እንዳሉ ሁሉ፤ ለቤተክርስቲያን ማሰሪያ ገንዘብ የሚለግሱ ሙስሊም አማኞችም ያሉት በኢትዮጵያ ነው።

ይሄ እኔ ብቻ ያየሁት ወይም ደግሞ አንድ ቦታ በተወሰኑ ሰዎች የሆነ አይደለም። በሁሉም ቦታ በሁሉም ዘማኞች ዘንድ የሆነ ኢትዮጵያዊነትን ዛሬም ከነወዙ እንዳለ የሚያሳይ እንደ አንድ የመቻቻል ምልክት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው እውነታ ነው። ይሄን በመሰለው እውነታ የጥምቀትን ዓላማ መረዳት እንችላለን። እንደ ጥምቀት ያሉ የአደባባይ በአሎችን ሰላም ሰባኪ እና አስታራቂ ይዘት ባላቸው በጎ መልዕክቶች ሀገራችን ላለችበት ወቅታዊ ሁኔታ ለእርቅና ለሽምግልና፣ ለአንድነትና ለአብሮነት ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

በጥምቀት በአል ላይ ምዕመኑ ከአምልኮ እኩል ፍቅርና አንድነትን ሊሰብኩ ይገባል። ፍቅር በሌለው ልብ ውስጥ ፈጣሪ አይገኝም። ለየትኛውም መንፈሳዊ በአል ፍቅር ከፈጣሪ ጋር መገናኛ ከፍጡር ጋር ደግሞ አብሮ የመኖሪያ ጥበብ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በብዙሀነት ውስጥ ለበዙና ለሰፉ አገርና ሕዝብ ሰላም ሰባኪ፣ ፍቅርን የሚያጸና አእምሮና ልብ ያስፈልጋል። ያለንበት ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድነትና ፍቅራችንን አጽንተን ወደፊት የምንቀጥልበት እንጂ አጋጣሚ እየጠበቅን ጥላቻ የምንነዛበት ሊሆን አይገባም።

ኢትዮጵያን ከማጽናት አኳያ መንፈሳዊ በአላት ሚናቸው ላቅ ያለ ነው። ከአምልኮው ጎን ለጎን አብዛኛው ሕዝብ የሚሰባሰብበት፣ አብሮ የሚበላበት፣ የሚጠያየቅበት በአል ነው። አብረን በሆንን ቁጥር ኢትዮጵያዊነት እያበበ፣ ባህል ስርዐት እየጠነከረ ይመጣል። በመንፈሳዊ አስተምህሮትም ይሄን አይነቱ መሰባሰብና መጠያየቅ በፈጣሪ ዘንድ ዋጋ ያለው እንደሆነ የተመሰከረለት ነው። በበአንድ ልብ ወደፈጣሪ እንደመቅረብ ያለ የበረከት ምንጭ የለም። ከትላንት እስከዛሬ ጸንተንና ተዋደን በኢትዮጵያዊነት ስም የተጠራነው አንድነትን በሚሰብኩ፣ አብሮነትን በሚያገኑ በጎ አንደበቶችና ተግባራት ነው።

መንፈሳዊ በአላት ፈጣሪ በፍጡር የሚመሰገንበት፤ ፍጡር ከፈጣሪው በረከት የሚገኝበት እንጂ ማንም የግል ፍላጎቱን የሚያራምድበት አይደለም። ለየቱም አይነት ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ ዓላማ ማስተናገጃነት የሚውል መንፈሳዊ በአል አላማውን የሳተ ነው። መንፈሳዊነት ለፍቅር የሚወግን መለያየት ቢኖር እንኳን በጣመ ስብከት መዳን እና መሻር የሚያመጣ የሰላም አርማ ነው። እንዲህ ያሉ ሕዝባዊ በአላት እኩይ አላማን ለማስተናገድ ለአንዳንዶች ምቹ ሲሆኑ አይተናል። መለያየትና ጥላቻን የሚሰብኩ የእኩይ ዓላማ ባለቤቶች ከድርጊታቸው ተቆጥበው ፈጣሪያቸውን ቢያገለግሉበት ትርፉ የላቀ ነው።

ጥምቀት ዘር፣ ቋንቋ፣ ጎጥና መንደር የሌለበት የሁሉም ኢትዮጵያውያን የምስጋና በአል ስለመሆኑ መናገር ለቀባሪ ማርዳት ነው የሚሆነው። ኢትዮጵያዊ ውበታችን በአንድ ቦታ ስለአንዱ ፈጣሪ የሚታይበት የአምልኮ ስፍራ ነው። በፍቅር ካልሆነ መንፈሳዊ ዓላማችን ግቡን እንደማይመታ የገባን ብዙዎች ነን። በፍቅር እና በወንድማማችነት መንፈስ ካልሆነ ፈጣሪን ፈልገን እንደማናገኘው የገባንም ጥቂቶች አይደለንም። እንዲህ ያሉ ሀይማኖታዊ በአላት አንድነታችንን የምናጠነክርባቸው እንጂ የምናላላባቸው አይደሉም።

ፈጣሪ ራሱን ከገለጠበትና ሰዎችን ለማዳን ከመረጠበት ሁነኛ መንገድ መሀል ቀዳሚው የፍቅር ሕግ ነው። ስለሰው ልጅ ሲወለድም ሆነ መከራን ሲቀበል፣ ሲሰቀልም ሆነ ትንሳኤውን ሲያሳየን ፍቅር በሚሉት የሕግ ስርዐት በኩል ነው። ጥምቀት ደግሞ ፍቅር ጀምሮ አንድነት የተከተለበት የፈጣሪ የሕግ መጀመሪያ ነው። ሁሉም ሀይማኖታዊ በአላት ከፈጣሪ መወለድ በኋላ እውቅና ያገኙ ናቸው። ፈጣሪ ፍቅር አስገድዶት ስለሰው ልጅ ተወለደ ካልን ስለእሱና እሱን አስበን የምናከብራቸው መንፈሳዊ በአላት ሁሉ የፍቅርና የአንድነት በአላት ናቸው ማለት ነው።

የጥምቀትን በአል በአንድ ሁነኛ ቃል ስናስረው ‹ጥምቀት የኢትዮጵያውያን መልክ› የሚል ይሆናል። አንዳንድ በአላት ኢትዮጵያን የሚገልጡ፣ ታሪክን የሚናገሩ የአብሮነትና የመቻቻል ምልክቶች ናቸው። ጥምቀትም በተለያዩ አለባበሶች፣ ዘር ቀለም ሳንል በአንድነት የምንታደምበት፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ ፍቅርና መቻቻልን የምንሰብክበት በአላችን ነው። ተከባብረን እና ተዋደን ስናከብረው እንጂ ተጠላልተንና ተናንቀን ስናከብረው አያምርም።

በአሎቻችን መድመቂያዎቻችን ናቸው። ሁሉም በአላት ኢትዮጵያ የምትደምቅበት፣ ሕዝቦቿ የሚጠያየቁበት በአል ነው። የእኔ የአንተ የሌለባቸው ስለአንዱ ፈጣሪ በአንድነት የምንቆምባቸው ናቸው። ባልተገባና ስርዐቱንም ሆነ ዓላማውን በሳተ አካሄድ በጥላቻና በአጉል ፍላጎት ልናደበዝዛቸው አይገባም። አሁን ላይ በበአል ስም ሁከት ፈጣሪ አንዳንድ አላስፈላጊ ድርጊቶች እየተስተዋሉ ነው። እኚህ ድርጊቶች በአሉን ፈር ከማሳት ብሎም በአማኙ መካከል መተማመን እንዳይኖር ከማድረግ ባለፈ ዋጋ የሌላቸው ናቸው።

እውነተኛ አምልኮ በማስታረቅና በማግባባት፣ በማስተቃቀፍና ይቅር በማባባል ውስጥ የሚገለጥ ነው። ሌሎችን ከማቀፍ፣ ስለሌሎች በማሰብ ውስጥ የሚያብብ ነው። ተቃቅፈንና ተደጋግፈን ፈጣሪ በሚወደው እምነት ውስጥ ወደነገ ስንሄድ ብቻ ነው አምልኮታችን ፈጣሪን ፈጣሪም እኛን የሚያግዘን። ለጠብ ጫሪነት የሚውሉ በአላት በፈጣሪም ዘንድ ተገቢዎች አይደሉም።

ተረቱስ ቢሆን "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" አይደል የሚለው። ጥምቀት አዲስ የመልበስ ብቻ ሳይሆን የአዲስ ልብ እና የአዲስ አእምሮ መነሻ ነው። በጥምቀቱ ፊት ስንቆም ጠላቶቻችንን ይቅር ልንል፣ ለበደሉን ምህረት ልናደርግ ነው። በማደሪያው ፊት ስንቆም በፍቅርና ስለፍቅር ሰላም ወዳዶች ሆነን ነው። አዲስ መልበስ ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ነው እንደሀገርም ሆነ እንደመንፈሳዊነት ዋጋ የሚያስገኘው።

# ተናጋሪው ዶሴ

## የጎዳና ተዳዳሪዋን ወጣት...

አስመረት ብስራት



በአፍላው የወጣትነት እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ከሁለቱም ፆታዎች የተሰባጠሩ ናቸው። በርከት ብለው ነው ከወዲያ ወዲህ የሚንቀሳቀሱት። በቡድን መጋዛቸው ጥቃትን ባያስቀርም ስለሚቀንስ መለያየትን አይመርጡም። ወጣቶቹ በተለመደው አጠራር ጎዳና ተዳዳሪ ይባላሉ፤ 'ተዳዳሪ' የሚለው ቃል እድሜ ልካቸውን የሚኖሩ ያስመስለዋል ብለው የሚቃወሙ ሰዎች ደግሞ 'ጎዳና አዳሪዎች' የሚለውን ስያሜ ይጠሯቸዋል። እኔም ለዚህ ፅሁፍ ጎዳና አዳሪዎች የሚለውን ምርጫዬ አድርጊያለሁ።

ልጆቹ በበጋ ወቅት የሚለበስ እንኳን ሳይፈልጉ በመሸባቸው ቦታ ማደርን ይመርጣሉ፤ ክረምት ግን እንዲህ እንደዋዛ በመሸበት ማደር አይሰራም። አጅግ በጣም ከባድም አደገኛም ሊሆን ይችላል። ለደህንነታቸው ሲሉ ዶፍ ዝናብ፣ ጎርፍ፣ ውርጭ የማይደርስበት ቦታ መምረጥ የግድ ይላቸዋል። ለብርዱ ደግሞ ከድልድይ በታች የተሻለ ቦታ አይገኝም።

ከድልድይ በታች ቦታ ለማግኘት ግን መታደል ያስፈልጋል። በክረምት ከጥጋጥጉና ከድልድዮቹ ስር ሌላ ሕይወት አለ። እንደ ነገሩ በካርቶን እና ጣውላ የታጠሩ ክፍሎች የሚመስሉ ስፍራዎች አሉ፤ መሀላቸው ቀጫጭን ፍራሾች፣ ብርድ ልብሶችና አንሶላዎች አሉ። ላስቲክም ማደበሪያም የተገኘው ነገር በሙሉ ተሸፍኖ የውሃ ነጠብጣቦች እንዳይገቡበትም መከላከል ይገባል። ያገለገሉ ሶፋዎች እና ምድጃዎችም ሌሎች ለመኝታም ለመመገቢያም የሚያገለግሉ ቁሶች ይታያሉ።

ሕፃናት ከነወላጆቻቸው አነስተኛ ቦታ ላይ ተደርድረው ይታያሉ፤ ወጣቶች በብዛት አራትም አምስትም ከዚያም በላይ ሆነው ሙቀት ለመፍጠር በሚመስል መልኩ ተጠባብቀው ይተኛሉ ሌሎች የተወሰኑ ወጣቶች ደግሞ ንጋት ላይ እሳት አያይዘው በዙሪያው ተኮልኩለው ይጨዋወታሉ።

የግንብ ስሮችና ድልድልዮቹ በጎዳና አዳሪዎቹ ዘንድ ለምን ተመራጭ ሆኑ ተብለው ሲጠየቁ የሚመልሱት "እንዴ! ድልድዮቹ ለእኛ በአጭሩ ቤታችን ናቸው። እንዲሁ ዝም ብለን በምናብ የሳልነው ቤት ሳይሆን እንደ ሀብታሞቹ በክረምት ከዝናቡና ብርዱ፤ በበጋም አልፎ አልፎ ከፀሀዩ የምናርፍባቸው ቤታችን ናቸው" ይላሉ።

ጎዳና አዳሪዎች የቀን መኝታ ብሎ ነገር አያወቁም። አይደለም ጎዳና አዳሪዎች ኑሮ የሞላላቸው ሰዎች ራሳቸው ቀን አይተኙም። ልተኛ ቢባልስ ደግሞ ሆድ ባዶ ሆኖ እንቅልፉ ራሱ ከዬት ይመጣል? ይህ ከባድ እውነታ ነው።

ከንጋት እስከ ምሽት ድረስ ያለውን ጊዜ የሚያሳልፉት ግማሾቹ የተጣሉ የፕላስቲክ ምርቶችን፣ ከፊሎቹ ደግሞ ብረታ ብረት ለቅመው ይሸጣሉ። ይህን የሚያደርጉት ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ በልቶ ለማደር ቢሆንም የሰበሰቡት ገንዘብ እንዲቀመጥላቸው ሲሉ በየምግብ ቤት እየዞሩ 'ተመላሽ' መፈለግም የየእለት ተግባራቸው ነው። 'ተመላሽ' ማለት የምግብ ቤት ደንበኞች በልተው የተረፋቸው እና ተጠራቅሞ በፌስታል የሚሰጣቸው ምግብ ነው፡፡ ተመላሽ በነፃ የሚሰጧቸው ምግብ ቤቶች እንዳሉ ሁሉ በተወሰነ ገንዘብ የሚሸጡላቸው አሉ። አንዳንዴም በጉርሻው መጠን ተመን ይወጣለታል።

ታዲያ ቀን የእለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ሲንጠራወዙ ከሚውሉት የጎዳና ልጆች መካከል ደመቅ ጎላ ብላ የምትታየው ወጣት ሳምራዊት ትባላለች። ሳምራዊት ከልጅነት እስከ እውቀት መሸከም የማትችለው ስቃይ ወላጆቿ ይሁኑ አሳዳጊዎቿ በውሉ በማይገቧት ሰዎች ቤት ውስጥ ደርሶባታል። ከረሀቡ ጭቅጭቁ፤ ከጭቅጭቁ ዱላው በየተራ ሲፈራረቁባት ነበር ደጁን የማተረችው። በአቅራቢያዋ ጎዳና ላይ የምታያቸው ልጆች እሷ ቤቷ ውስጥ ከሚደርስባት መከራ የተሻሉ መስሎ ታያት። እሷ መከራ ብላ የምታስበው ነገር ሲበዛ ከመሞት መሰንበት ብላ ጎዳናን ምርጫዋ ያደረገች ወጣት ናት።

### ወጣቷ ሳምራዊት

ከቤቷ የወጣችው ሳምራዊት አሁን ላይ ከድልድዩ ስር ከሚኖሩት ወጣቶች አንዷ ናት፤ ከጓደኞቿ ጋር የምትኖረው ሳምራዊት ከእነሱ በእድሜ ከፍ ስለምትል ጓደኞቿን እንደ ልጆቿ ነበር የምትንከባከባቸው። እሷና እንደ ሳምራዊት አጠራር ልጆቿ የእለት እንጀራቸውን ለማግኘት አንዳንድ ስጋ ቤቶች ቅንጥብጣቢ በማምጣት እና ከሌሎች ሱቆችና አትክልት መሸጫዎች ደግሞ ሊበላሹ የደረሱ ሽንኩርትና ቲማቲም ለምነው አምጥተው እሳት አንድደው ምግብ በመስራት በጋራ ይኖራሉ።

ከምግቡም በላይ ትስስሩ አብሮ መኖሩን ተላምደውታል። አንዳቸው ለአንዳቸው ከለላ አንዳቸው ለአንዳቸው መከታ ናቸው። በእለቱ በአካባቢያቸው በሚገኘው ቀጨኔ መድሀኒዓለም ቤተክርስትያን የነፍስ ይማር ዝክር ስለነበር ሳምራዊትና ጓደኞቿ ሲበሉና ሲጠጡ ውለው ደክሟቸው ነበር በጊዜ መጥተው የተኙት።

ልጆቹ እንቅልፍ ጥሏቸው ነበር። በጥልቅ እንቅልፍ ወስጥ በመሆናቸው የተነሳ አጠገባቸውም ቦንብ ቢፈነዳ እንኳን አይነቁም በሚያስብል ደረጃ ጧ ብለው ተኝተዋል። ይህን አጋጣሚ ሲጠብቅ የነበረው ክፉ ሰው ከመካከላቸው ከፍ ብላ የምትታየውን ሳምራዊት በአይኑ ሙሉ ተመለከታት።

ያኔ ልጆቼ የምትላቸውን ጓደኞቿን ለመጠበቅ ስትል ዳር ላይ የተኛችው ሳምራዊት ቀን በጠጡት ጠላ ምክንያት ይሁን በሌላ ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ነበረች።

### ቀን ስጎደስባት የዋስ ቀነ ጎዶሎ

ዋልጌ ነው፤ ስነ ምግባር የሚባል ነገር ያልፈጠረበት። ያንንም ያንንም መዝለፍ መለያ ባህሪው ነበር። ነገሮችን በፍቃድ ከማድረግ ይልቅ ጉልበት የሚቀናው ሁሉን ነገር በሀይል ማግኘት የሚችል የሚመስለው አይነት ሰው ነው። ዝናው ተገኝ ይባላል።

በአካባቢው የተጠላም የተፈራም ሰው ነበረ። ከእሱጋ መቀራረበ አንድ ቀን ዋጋ እንደሚያስከፍል የተረዱ ሁሉ ቀስ በቀስ እየራቁት ሄደው ብቻውን ቀርቷል። በሰማኒያ ያገባት ሚስቱን እንኳን ሳይቀር በድብደባ አሰልችቶ ያባረረ ክፉ ሰው ነው።

በብቸኝነቱ የተነሳ ብስጭት እየጨመረ ቀኑን ሙሉ ሲጠጣ የሚውለው ይህ ሰው ሲመሽ ለክፋቱ ማረፊያ ሕፃናትን መመልከት ከጀመረ ሰነባብቷል። እስከ አሁን ድረስ ባይሳካለትም ለዛሬ ግን ወጥመዱ የያዘለት መስሏል።

ቀጨኔ መድሃኒዓለም አቅራቢያ ከሚገኝ አንድ ድልደይ ስር መጠለያቸውን ሰርተው ያረፉት ሕፃናት አይኑ ከገቡ ሰነባብተዋል። እነዚህ የጎዳና ልጆች ለወትሮው እርስ በእርስ መጠባበቅን መርሃቸው አድርገው ስለሚንቀሳቀሱ ክፉ ነገር ደርሶባቸው አያውቅም ነበር።

ዛሬ ግን ቤተክርስቲያን ለነፍስ ይማር የመጣ ምግብና መጠጥ ተትረፍርፎ ስላገኙ ያገኙትን በሙሉ በልተውና ጠጥተው ደክመው ስለነበር በጊዜ ነበር አንቅልፍ የጣላቸው። ይህንን የተረዳው ይህ ሰው ምሽቱ እስኪገፍና ሰው ሁሉ ቤቱ ገብቶ ጭር እስኪል አንድ ቦታ ተሸሽጎ መጠበቅ ጀመረ።

በግምት ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን ግራ ቀኙን ተመልክቶ ሰው አለመኖሩን ሲረዳ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች የጎዳና አዳሪ ልጅ ላይ አስገድዶ ወንድነቱን ላከባት። በሀይል የፈለገውን ሁሉ ማድረግ የሚችል የሚመስለው ይህ ሰው ይህች ቀን የጨለመባትን ወጣት ይበልጥ ተስፋዋን አጨለመባት።

### ፖሊስ

በማስፈራራት አፏን አፍኖ የፈለገውን ቢያደርግም፤ ቀድመው ጩኸቷን ሰምተው የነቁት ልጆቼ የምትላቸው ጓደኞቿ ከሸራ ቤቱ ሾልከው ወጥተው ፖሊስ በመጥራት ወደ ቦታው ይዘው መጡ። ያኔ ፖሊስ መምጣቱን የተመለከተው ተጠርጣሪ እግሬ አውጪኝ ብሎ ሊያመልጥ ቢሞክርም ፖሊስ ተከታትሎ በቁጥጥር ስር አውሎታል።

ፖሊስም ተጠርጣሪው ዝናው ተገኝ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ልዩ ቦታው ቀጨኔ መድሃኒዓለም ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሕዳር 4 ቀን 2015 ዓ/ም በግምት ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን ሆን ብሎ በመዘጋጀት ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰችን ሴት ደፍሯል በማለት ክስ መስርቶባታል።

በ1996 ዓ/ም የወጣዉን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2/ሀ ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ልጅ ላይ በፈጸመዉ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተከሰሰዉ ሰው የአይን እማኞች፤ የሕክምና ማስረጃና የተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃል የተጠናቀረበት መዝገብ አዘጋጅቶ ለአቃቤ ህግ አቀረበ።

### የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

አቃቤ ሕግም የክስ መዝገቡ እንደደረሰው ጉዳዩን መመልከት ጀመረ። ተከሳሽ ዝናው ተገኝ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 05 ልዩ ቦታው ቀጨኔ መድሃኒዓለም ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ህዳር 4 ቀን 2015 ዓ/ም በግምት ከምሽቱ 4፡00 ሰዓት ሲሆን በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2/ሀ ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ልጅ ላይ በፈጸመዉ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከሶ ፍርድ ቤት አቀረበው።

የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝሩ እንደሚያስረዳዉ የግል ተበዳይ ዕድሜዋ ከ16 እስከ 17 ዓመት እና የጎዳና ተዳዳሪ ስትሆን ከነበረችበት የሸራ ማረፊያ ቤት ውስጥ በማውጣት ተከሳሽ እጇን በመጠምዘዝ እና በመታገል ተበዳይ ስትጮህ መሬት ላይ ጣላት።

መሬቱ ላይ በሀይል ገፍቶ በመጣልና በኃይል በማስፈራራት ጩኸቷን ካስቆመ በኋላ አፏን አፍኖ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመባት። ይህ በመሆኑ ዐቃቤ ህግ በ1996 ዓ/ም የወጣዉን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 620/2/ሀ ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች ልጅ ላይ በፈጸመዉ በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ክስ መስርቶበታል፡፡

### ውሳኔ

**ተከሳሹም ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ዐቃቤ ሕግ የተከሳሸ ጥፋተኝነት ያስረዳሉ ያሳቸዉን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎችን በማቅረብ የተከራከረ ሲሆን ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ቢሠጥም ተከሳሽ ጥፋቱን ባለማስተባበሉ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ጥፋተኛ ብሎታል፡፡**

**በመጨረሻም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 1ኛ ወንጀል ችሎት የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ሁኔታዎችን በማየት ተከሳሹ በሰባት ዓመት ፅኑ እስራት እና ከሕዝባዊ መብቱ ለአምስት ዓመት ታግዶ ይቆይ በማለት ወስኖበታል፡፡**

# ስፖርት





## ውጤት መቀልበስ ለወጣት ቡድኑ የዓለም ዋንጫ ተሳትፎ

**ብርሃን ፈይሳ**

የዓለም ዋንጫ ተሳትፏቸው አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ሴቶች ብሔራዊ ቡድን ከነገ በስቲያ ወሳኙን ጨዋታ ያከናውናል። የወጣት ቡድኑ አበበ ቢቂላ ስታዲየም ላይ በሚያደርገው ጨዋታ የሞሮኮን ሽንፈት መቀልበስ ከቻለም አፍሪካን በዓለም ዋንጫው ከሚወክሉ አራት ቡድኖች መካከል ይካተታል። ቡድኑ ዕድሉን ለማቅናት ካዛብላንካ ላይ የታዩ ድክመቶቹን በማስተካከልና ስህተቶቹንም በማረም በሀገሩ አየርና ደጋፊው ፊት የሚኖረውን የ90 ደቂቃ ቆይታ መጠቀምም ይጠበቅበታል።

አራት ዙሮች ያሉትን የማጣሪያ ጨዋታ አልፎ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ የደረሰው የአሰልጣኝ ፍሬው ኃይለገብርኤል ቡድን ከሞሮኮ አቻው ጋር ካዛብላንካ ላይ ተጫውቶ 2 ለምንም በሆነ ውጤት ተሸንፎ መመለሱ ይታወቃል። ከጉዞ መልስ በኋላም የአንድ ቀን እረፍት ካደረገ በኋላ ወደ ዝግጅት የተመለሰ መሆኑን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን አስታውቋል። ቡድኑ ከሞሮኮ ጋር ለነበረበት የመጀመሪያ ጨዋታ ለሳምንታት ዝግጅት ሲያደርግ ቢቆይም የስልጠና ቡድኑ የጠየቀው የወዳጅነት ጨዋታ አለመመቻቸቱ በሚፈለገው ልክ እንዲገኝ እንቅፋት እንደሆነበት ተጠቁሞ ነበር። በጨዋታው ዕለትም ከፍተኛ የሆነ ያለመረጋጋት ችግር የተስተዋለበት ሲሆን፤ ይህም ለተጋጣሚያቸው ምቹ ሁኔታን ሊፈጥርላቸው ችሏል። የሰሜን አፍሪካዋ ሀገር ሞሮኮ ተጫዋቾች በኢትዮጵያዊያኑ በኩል የነበረውን ድክመት ተጠቅመውም በመጀመሪያዎቹ 15 ደቂቃዎች፤ እንዲሁም ከእረፍት መልስ ባሉት ደቂቃዎች በፍጥነት በማጥቃትና የግብ አጋጣሚዎችን በመፍጠር የበላይነቱን መያዝ ችለዋል።



ቡድኑ ለዓለም ዋንጫ ተሳትፎ በቀረው የ90 ደቂቃ ዕድል መጠቀም ይገባዋል፤

ከወጣት ቡድን አንጻር የደረሱበት ደረጃ እጅግ አበረታችና መልካም የሚባል ቢሆንም ባለፈው ጨዋታ በታዩት ክፍተቶች በኩል መሻሻል ሳይችል አዲስ አበባ ላይም በተመሳሳይ ብልጫ ከተወሰደበት ከዓለም ዋንጫ ጉዞው ሊገታ ይችላል። በመሆኑም በጥረቱ ከጫፍ የደረሰው ቡድኑ ተረጋግቶና ተናቦ በመጫወት እንዲሁም ተጋጣሚያቸው ልዩነት ለመፍጠር በሚጠቀምበት ወቅት ለይቶ መጠንቀቅና በርካታ የግብ እድሎችን መፍጠር የግድ ነው። ነገር ግን፣ በታዳጊና ወጣት ቡድኖች ለመጫወትና ለማሸነፍ በሚኖር ከፍተኛ ጉጉት የተነሳ ዋጋ መክፈል በተደጋጋሚ የታየ ነው። በመሆኑም ይኸው ሁኔታ በዚህ ጨዋታ ተደግሞ የቡድኑ ጉዞ እንዳይሰናከል በዝግጅት ወቅት ስህተቶችን ማረም ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። በሌላ በኩል ጨዋታው የሚደረገው በለመዱት የሀገራቸው አየርና በደጋፊዎቻቸው ፊት እንደመሆኑ ይህንን ዕድላቸውን በመጠቀም ተፎካካሪያቸው ላይ የበላይነቱን በመውሰድ እድሉን እንደሚጠቀሙም ይጠበቃል።

ኮሎምቢያ አስተናጋጅ የሆነችበት 11ኛው የሴቶች ከ20 ዓመት በታች ዓለም ዋንጫ ከወራት በኋላ ይጀመራል። በየሁለት ዓመቱ የሚደረገው ይህ ውድድር ቀድሞ 16 ቡድኖችን የሚያሳትፍ ቢሆንም ከዚህ ዓመት ጀምሮ ግን ቁጥሩን ወደ 24 በማሳደግ ይካሄዳል። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) በአራት ቡድኖች የሚወከል ሲሆን፤ በማጣሪያውም 35 ቡድኖችን ሲያጫውት ቆይቷል። በማጣሪያው እስከ አራተኛው ዙር የደረሱ ስምንት ቡድኖች የሚለዩበት ወሳኙን የመጨረሻ ጨዋታቸውን ነገ እና ከነገ በስቲያ የሚያከናውኑ ይሆናል። በዚህም መሠረት ነገ ግብጽ ከካሜሮን እንዲሁም ብሩንዲ ከናይጀሪያ ሲጫወቱ፤ ከነገ በስቲያ ደግሞ ኢትዮጵያ ከሞሮኮ እንዲሁም ሴኔጋል ከጋና በሚኖራቸው የደርሶ መልስ ግጥሚያ አሸናፊ የሚሆነው ቡድን የኮሎምቢያ ቲኬቱን የሚቆርጥ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ውጤቱን ቀልብሶ የዓለም ዋንጫ ተሳትፎውን ማረጋገጥ ከቻለ ከ22 ዓመታት በፊት በአርጀንቲና ከ20 ዓመት በታች የዓለም ዋንጫ ኢትዮጵያን የወከለውን የወንዶች ብሔራዊ ቡድን ታሪክ የሚጋራ ይሆናል። በዚህ ውድድር እንደ ናይጄሪያ እና ዴሞክራቲክ ኮንጎን የመሳሰሉ ሀገራት ተደጋጋሚ ተሳትፎ ያላቸው ሲሆን፤ የመድረኩ ብርቱ ተፎካካሪ የሆነው የናይጄሪያ ቡድን እአአ በ2004 እና 2006 አራተኛ ደረጃን ይዞ የተጠናቀቀበት ውጤት ቀዳሚው ነው። በርካታ ዋንጫዎችን በማንሳት ቀዳሚ የሆኑት ጀርመንና አሜሪካ ሶስት ሶስት ጊዜ ማሳካት ችለዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር አ/ኮ/ኢ/ኮ/001/2016

የአገና ኮንስትራክሽንና ኢንደስትሪያል ኮሌጅ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በጉራጌ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ኮሌጆች አንዱ ሲሆን ኮሌጁን ከወልቂጤ ከተማ 42 ኪ.ሜ፣ ከቡታጅራ 52 ኪሎ ሜትር፣ ከአዲስ አበባ 200 ኪ.ሜትር ርቀት ላይ በአገና ከተማ አስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡ኮሌጁ በ2016 በጀት ዓመት ለተለያዩ ስልጠና ክፍሎች እና ለቢሮ አገልግሎት የሚያሥፈልጉትን ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ስለዚህ መስፈርቱን የምታሟሉ አቅራቢዎች ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የስልጠና ክፍሎች ዕቃዎችን ለማቅረብ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

1. Hardware and Network Servicing (ICT)
2. Industrial Electrical Machin Derives Technology
3.Automotive Technology
4. Hotel and Tourism Management
5. General Metal Fabrication and Assembling Manufacturing (Mechanics)
6. Building Electrical Installation
7. Structural Construction work
8. Basic Electrical Equipment Service
9. Office Stationery and Vehicles Materials
10. Garment production technology
11. Wood work technology

**በመሆኑም ተጫራቾች**

1) በመስኩ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው አቅራቢዎች ማስረጃቸውን ማቅረብ የሚችሉና የዘመኑ ግብር የከፈሉ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ተመዝጋቢ የሆኑ፣
2) በመንግስት ግዢ ኤጀንሲ የዘመኑ አቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ
3) የዕቃውን ዋጋ የሚያቀርቡት በጨረታ ሰነዱ በተጠቀሰው ዝርዝር መግለጫ መሰረት ብቻ ይሆናል፣
4) ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር (350) ሶስት መቶ ብር ብቻ) በኮሌጁ አካውንት ቁጥር 1000168288248 በማስገባት ስሊፕ ይዘው በመምጣት በኮሌጁ ደረሰኝ በማስቆረጥ የጨረታ ሰነዱን በኮሌጁ ግዥና ንብረት አስተዳደር ቡድን መሪ ቢሮ ቁጥር 16 ዘወትር በስራ ሰዓት መግዛት ይችላሉ፣
5) የጨረታው ሙሉ ሰነድ ሞልተው ኦርጂናል እና ኮፒውን በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማሸግ የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦድ 1.5% በባንክ የተመሰከረለት (CPO) በኮሌጁ አቅራቢያ በሚገኙ በንብ ኢንተርናሽናል ባንክ፤ በብርሃን ባንክ፤ በአቢሲኒያ ባንክ፤ በአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ብቻ በአገና ኮንስትራክሽንና ኢንዱስትሪያል ኮሌጅ ስም በማሰራት ከኦርጅናል ዶክመንት በማያያዝ በፖስታ ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣
6) ሌላው ተጫራች ባቀረበው ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ ማቅረብ አይቻልም፣
7) የጨረታ አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ዕቃ ከማስገባታቸው በፊት ናሙና ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣
8) አሸናፊዎች ለሚያቀርቡት ዕቃ ህጉን በሚፈቅደው መሰረት 2%(Withholding) የመክፈል ግዴታ አለባቸው፣
9) የጨረታው አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ዕቃ ወደ ኮሌጁ ድረስ የማቅረብ ግዴታ ይኖርባቸዋል፣
10) ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 የስራ ቀናት አየር ላይ ከዋለ በኋላ በ15ኛው ቀን ከጠዋቱ 6፡00 ላይ የጨረታ ሳጥን ታሽጎ 8፡30 ተጫራቶች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፣
11) ኮሌጁ የተሻለ ዘዴ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፣

**ለተጨማሪ መረጃ**

**በስልክ ቁጥር፡- 011-329-0387/0626**

**በሞባይል ቁ.0911033784**

**Email: agenacon.indus.college@gmail.com**

**Website: https://agenacollege.edu.et**

## የአገና ኮንስትራክሽንና ኢንደስትሪያል ኮሌጅ